Ellen G. White Estate

# ወደ ክርስቶስ የሚመራ መንገድ



ኤለን ጂ ኋይት

# Aወደ ክርስቶስ የሚመራ መንገድ


ምዕራፍ **1 -** የእግዚአብሔር ፍቅርለሰዎች..............................**3**
ምዕራፍ **2 -** ኢየሱስ ለኃጢያተኛው ስስማስፈስጉ.................. **25**
ምዕራፍ **3 -** ንስሓ......................................................**42**
ምዕራፍ **4 -** ኃጢያትን መናዘዝ......................................... **86**
ምዕራፍ **5 -** ቅድስና..................................................... **101**
ምዕራፍ **6 -** እምነትና ተቀባይነት ማግኘት......................... **118**
ምዕራፍ **7 -** የደቀመዝሙርነት መፈተኛ............................**139**
ምዕራፍ **8 -** ወደክርስቶስ ሙላት ማደግ........................... **167**
ምዕራፍ **9 -** ሥራ እና ሕይወት..........................................**195**
ምዕራፍ **10 -** እግዚአብሔርን ማወምዕራፍቅ...................... **216**
ምዕራፍ **11 -** የጸሎት በረከት.............................................**238**
ምዕራፍ **12 -** ጥርጣሬን ማሸነፍ........................................**274**
ምዕራፍ **13 -** በጌታ መደሰት............................................ **299**


https://m.egwwritings.org/am/folders/1093

# ምዕራፍ 1 - የእግዚአብሔር ፍቅርለሰዎች

ተፈጥሮ እና እራሱን ለፍጡራኑ የገለጠበት መለኮታዊ መንገድ የእግዚአብሔርን ፍቅር ይመሰክራሉ። በሰማይ ያለው አባታችን የህይወት፣ የጥበብና የደስታ ምንጭ ነው.እስቲ አስደናቂና ውብ ወደሆነው ተፈጥሮ ይመልከቱ። ይኸው ወደር የማይገኝለት ተፈጥሮ ለሰብዓዊው ፍጡር ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ህይወት ላላቸው ፍጡራን እጅግ የተስማማና የደስታ ምንጭም መሆኑን ያስቡ። ምድርን ደስ የሚያሰኘው የፀሐይ ብርሃን እና መሬቱን የሚያረሰርሰው ዝናብ፣ ኮረብታው፣ ባሕሩናመስኩ ሁሉም በአንድነት ስለ ፈጣሪ ፍቅር ይናገራሉ። ለፍጡራኑ የሚያስፈልገውን ሁሉ በየዕለቱ የሚያሟላው እግዚአብሔር

ነው።ባለመዝሙሩ ባማሩ ቃላት እንዲህ ይላል፡-

«የሁሉ ዓይን አንተን በተስፋ ይጠብቃል፤ አንተም ምግባቸውን በወቅቱ ትሰጣቸዋለህ። አንተ እጅህን ትዘረጋለህ፤ የሕያዋን ፍጥረታትንም ሁሉ ፍላጎት ታረካለህ።»

(መዝ. 145: 15-16)

እግዚአብሔር ሰውን ፍጹም፣ ቅዱስ እና ደስተኛ አድርጎ ነበር የፈጠረው።ምድር በፈጣሪዋ እጅ በተሰራችበት ጊዜ ውብ ከመሆኗ ባሻገር የመበስበስ፣ የእንከንም ሆነ የእርግማን ጥላ አላጠላባትም ነበር። ነገር ግን የፍቅር ሕግ የሆነውን አምላካዊ ሕግ መተላለፍ በምድር ላይ ዋይታንና ሞትን አመጣ።ሆኖም ግን የኃጢአትን ውጤት

ተከትሎ በመጣው ሥቃይ መሃል እንኳ የእግዚአብሔር ፍቅር ተገልጾአል። በርግጥ እግዚአብሔር በሰው ምክንያት ምድርን እንደረገማት እናነባለን (ዘፍ. 3:17)። እሾህና አሜኬላ፤ ችግርና ፈተና የሰብዓዊውን ህይወት አድካሚና ጥንቃቄ የበዛበት ይሆን ዘንድ መንስዔ ቢሆንም ነገር ግን ይህ የሆነው ለበጎ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ይህን ዕቅድ የዘረጋው ሰብዓዊው ፍጡር ካወደቀሰት ኣባቅትወጥቶ ኃኣት ካጎበጠው ማንነት ቀና የሚልበት አንዱ ሥልጠና ይሆንለት ዘንድ በማሰብ ነው። ምንም እንኳ ምድር በኃጢአት ብትወድቅም ሁሉም ነገር በሐዛንና ምስቅልቅል ብቻ አልተዋጠም በራሷ በተፈጥሮ ውስጥ የተስፋ መልእክቶችንና መጽናናትን እናገኛለን። አሚካላው በአበባ እንዲሁም እሾሁ በጽጌረዳ ተሸፍኗል።

«እግዚኣብሔር ፍቅር ነው» የተሰኘው ቃል በእያንዳንዱ እንቡጥ ኣበባና አረጓዴው መስክ ላይ ይነበባል» በአስደሳች ድምፃቸው ልዩ ዝማሬ የሚያሰሙት ተወዳጅ አዕዋፍ፣ ፍጹም በሆነው መዓዛቸው አየሩን የሚያውዱ ውብ አበቦችና አረንጓዴ ቀለማትኝ የተላበሱ ግዙፎቹ የዱር ዛፎች፣ አፍቃሪና ጥንቃቄ የተሞላው አባት ልጆቹ ደስ ይሰኙ ዘንድ ያለውን ምኞት ይመሰክራሉ።

አሜኬላው በአበባ አንዲሁም እሾሁ በጽጌረዳ ተሸፍኗል።

የእግዚአብሔር ቃል አምላካዊውን ባህሪ ይገልጻል፡ ወሰን ስለሌለው ፍቅሩና ህዘኔታው ያወጀው እራሱ ይኸው አምላክ ነው» ሙሴ

ክብርህን አሳየኝ» ብሎ በጸለየ ጊዜ «መልካምነቴ ሁሉ በፊትህ እንዲያልፍ አደርጋለሁ። (ዘፀ. 33፥18-19) በማለት ነበር እግዚአብሔር የመለሰለት። ይህ የእርሱ ክብር ነው። ጌታ በሙሴ ፊት እያለፈ እንዲህ ሲል አወጀ፦ «እግዚአብሔር ርኅሩኅ ቸር አምላክ፣እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ፣ ፍቅሩና ታማኝነቱ የበዛ፣ ፍቅርን ለሺህዎች የሚጠብቅ፣ ክፋትኝ ዐመጽንና ኃጢአትን ይቅር የሚል» (ዘፀ. 34 6-7)። እርሱ ቸርና ርኅሩኅ፣ ከቁጣ የራቀ» «ምህረት በማድረግ ደስ የሚለው ነው (ዮናስ 420 ሚልክ. 7፥8)።

እግዚአብሄር ሊያተውለው በሚችለው በተፈጥርና ጥልቀት ባሳቸው ሰርሳሪኅ በተሞሉ ምድራዊ ትስስሮች አማካኝነት እራሱን ይገልጽልን ዘንድ ሽቶአል። ቢሆንም ግን አነዞህ ነገርች የአርሶኝ ፍቅር የጨካሉት

ፍጽምና በጎደለው መልኩ ነው። ምንም እንኳ እነዚህ ሁሉ ማ|ረጃዎች ቢሰጡም የመልካም ጠላት የሆነ ኃይል የሰዎች አእምሮ እንዲታሠር አደረገ። በዚህ ሁሉም እግዚኣብሄርን በፍርሃትና በመርበድበድ ከመመልከታቸው በተጨማሪ እርሱን እንደ ጨካኝና ይቅር እንደማይል አድርገው አሰቡት። እግዚኣብሔር አለልክ ጥብቅ ፣ ከባድ ፍርድ የሚሰጥ፡ እንዲሁም ጨካኝ ፈራጅና ርህሪሄ ቢስ ዓይነተኛ ባህሪይው እንደሆነ አድርጎ ሰይጣን በአእምሮአቸው ውስጥ በመሳል አሳታቸው። እግዚኣብሄር በሰዎች ሳይ መፍረድ ሲል በቅናት ዓይነት ስህተታቸውን ብቻ የሚፈልግ አምሳክ ተደርጎ ተሳለ። ይህን ጽልመት የተሞላ ጥሳ ለመግፈፍ እና ዘላለማዊውን አምላካዊ ፍቅር ለማሳየት ሲል ኢየሱሰ ከሰዎች ጋር ሊኖር ወደዚህ ምድር መጣ።

የእግዚኣብሔር ልጅ ኣባቱን ሊገልጥ ከሶማይ ወረደ «ከቶንም እግዚኣብሔርን ያየ ማንም የለም፥ ነገር ግን በአብ እቅፍ ያለው ኣንድያ ልጁ የሆነ አምላክ አርሶ ገለጠው (ዮሐ 1:18):: «ከአብ ሌላ ወልድን የሚያውቅ የለም ከወልድና ወልድ ራሱ ፈቅዶ ካሚገልጥላቸው ሌላ ኣብ የሚያውቅ የለም» (ማቴ l:17)። ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አብን አሳየን ብሎ ኢየሱሰኝ በጠየቀ ጊዜ «አንተ ፊልጶስ! ይህን ያህል ጊዜ ከኣንታ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴት አብን አሳየኝ ትሳለህ?» (ዮሐ. 14:8-9) በማለት ነበር የመሰሶሰት።

ኢየሱሰ ስለምድራዊ አገልግሎቱ ሲገልጽ እንዲህ ነበር ያለው “የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆች ወንጌልን እንድሰብክ፣ እርሱ

ሰቶኛልና፤ ለታሰሩት መፈታት፡ ለታወሩትም ማየት፥ እንዳውጅ፡ የተጨቆኑትን ነጻ አንዳወጣ፡ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዲወጅ ልኮኛል። (ሉቃ 4፡18)። ይህ እንግዲህ የእርሱ ስራ ነበር። እርሱ መልካም እያደረገና በሰይጣን ግዞት ስር ወድቀው የነበሩትን እየፈወሰ በየስፍራው ተንቀሳቀሰ። እርሱ በመሃላቸው እየፈወሰ ያልፍ ስለነበረ፡ የህመምና የማቃሰት ድምጽ የሚሰማበት አንድም መንደር አልተገኘም ነበር። ሥራዎቹ በመለኮት ለመቀባቱ ማረጋገጫ በመሆን ፍቅር፣ ምህረትና ርኅራኄ በእያንዳንዱ የህይወቱ እንቅስቃሴ ተገልጾ ይታይ ነበር። ልቡ ለሰዎች ልጆች በፍቅርና በርኅራኄ ይፈስ ነበር። እርሱ የሰዎችን ፍላጎት ለመድረስ ይችል ዘንድሰብዓዊውን ተፈጥሮ ወሰደ:: እጅግ ድኾችና እራሳቸውን ዝቅ ያደረጉ እርሱን ቀርቦ ለማናገር ፍርሃት

አልነበራቸውም። እንዲያውም ትናንሽ ብላቴናዎች ሳይቀሩ በእርሱ ተስበው ነበር። ህጻናት እንኳን ሳይቀሩ በጭኖቹ ላይ በመውጣት፣ በፍቅር የተሞላ ቾርና ርኅሩኅ እንዲሁም አስተዋይ የሆነውን የፊቱን ገጽታ ለመመልከት ችለው ነበር።

ኢየሱስ የእውነትን ቃል ሁልጊዜ በፍቅር ይናገር ነበር:: እርሱ ከሰዎች ጋር ለሚኖረው ግንኙነት ትኩረት የሚሰጥ፣ ደግ፣ አሳቢና አስተዋይ ነበር።ኢየሱስ ግትር አልነበረም፣ ለሆደ ባሻው አላስፈላጊ ጠንካራ ቃላትን በመሰንዘር እንዲታወክ አድርጎ አያውቅም፣ ሰብዓዊውን ደካማነትም አልተቸም። እውነትን በግልጽ ይናገር ነበር፤ ይህንን ያደርግ የነበረው ግን ሁልጊዜ በፍቅር ነበር። ግብዝነትን፣ አለማመንን እንዲሁም ታማኝ አለመሆንን ቢያወግዝም፣ ግሳጼ ሲያደርግ

ሳለ ግን በድምፁ ላይ ሳግ ይሰማ ነበር። መንገድ፣ እውነትና ህይወት የሆነውን ኢየሱስ ለመቀበል አሻፈረኝ ላለችው ለሚወዳት ከተማ ኢየሩሳሌም አልቅሶአል። ሕዝቡ አዳኙን ቢቃወምም እርሱ ይመለከት የነበረው በህዘኔታና በፍቅር ዓይን ነበር።የእርሱ ህይወት እራስን በመካድና ለሌሎች ደግ በማሰብ የተሞላ ነበር።እያንዳንዱ ነፍስ በእርሱ ዘንድ የከበረ ነበር። መለኮታዊውን ክብር ከምንም ሳይቆጥር ነገር ግን ከፍ ባለ ፍቅር እራሱን ለእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ዝቅ ያደረገው አዳኝ፤ እያንዳንዱን ሰው ሊያድነው ዓላማው የሆነውን የወደቀ ነፍስ በመመልከት ነበር።

ይህ በክርስቶስ ህይወት የተገለጠው ባሕርይ የራሱ ባህሪይ ነው።ደግሞም የእግዚአብሔር

ባህሪይ ነው። ከአብ ልብ በመመንጨት በክርስቶስ የተገለጠው መለኮታዊው ርኅራኄ ወደ ሰው ልጆች ይፈሳል። አፍቃሪና ርኅሩኅ የሆነው አዳኝ «በሥጋ የተገለጠ» (1ኛ ጢሞቴ. 3:16) እግዚአብሔር ነበር።

ኢየሱስ እኛን ለመዋጀት ሲል በዚህ ምድር ላይ ኖረ፣ ሥቃይ ተቀበለ፤እንዲሁም ሞተ። እኛ የዘላለማዊው ደስታ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ እርሱ «የሐዘን ሰው» ሆነ። በጸጋና በእውነት የተሞላው የተወደደ ልጁ ቃላት ሊገልጹት ከማይችል ክብር ወጥቶ በኃጢአት ወደ ረከሰው፣ በሞት ጥላ ሸለቆና በእርግማን ጽልመት ወደ ተዋዋጠው ወደዚህ ምድር ይመጣዘንድ እግዚአብሔር ፈቀደ።የእግዚአብሔርን የፍቅር እቅፍ፣የመላእክትን ክብርና አምልኮ ትቶ ሥቃይ፣ ሐፍረት፣ ስድብ፣ ውርደት፣ጥላቻና

ሞት ወደ መቀበል ያመራ ዘንድ የአባቱ ፈቃድ ሆነ። «በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን» (ኢሳ. 53:5)። እነሆ እርሱን በምድረበዳ፣ በጌተሰማኔ፣ በመስቀል ላይ ተመልከቱት! እንከን የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ የኃጢአትን ቀንበር እርሱ ራሱ ወሰደ፥ ኃጢአት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚያደርገው አስፈሪ መለያየት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ በሆነው በእርሱ ነፍስ ውስጥ ዘልቆ ተሰማው።ይህን ተከትሎ «አምላኬ፣ አምላኬ፣ ለምን ተውኸኝ» (ማቴ. 27፡46) የሚል ታላቅ የሕማም ጩኸት ከአንደበቱ ወጣ። ይህ እንግዲህ የእግዚአብሔርን ልጅ ልብ የሰበረውና አስፈሪ ተፈጥሮ የተላበሰው፣ ነፍስን ከእግዚአብሔር የሚነጥለው የኃጢአት ሸክም ነበር።

ኢየሱስ የእውነትን ቃል ሁልጊዜ በፍቅር ይናገር ነበር።

ነገር ግን ይህ ታላቅ መስዋዕትነት የተከፈለበት ምክንያት በአብ ልብ ውስጥ ሰውን የመውደድ ስሜት በመፍጠር እኛን ለማዳን ፈቃደኛ ለማድረግ አልነበረም:: በጭራሽ! «እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ. 3:16)። አብ እኛን የወደደበት ምክንያት ቁጣውን ለማብረድ መስዋዕት በመከፈሉ አይደለም:: ነገር ግን እርሱ ራሱ ስለሚወደን የሚከፈለውን መስዋዕት አዘጋጀ:: ክርስቶስ አማላጅ በመሆን ዘላለማዊ ፍቅሩን በኃጢአት ለወደቀው ዓለም አፈሰሰ «እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር» አስታረቀ (2ኛ ቆሮ. 5:19)። እግዚአብሔር ከልጁ ጋር ሥቃይ

ተቀበለ። በጌተሰማኒ ህማም እንዲሁም በቀራኒዮ መስቀል ሞት ዘላለማዊው አፍቃሪ ልብ የመዋጀታችንን ዋጋ ከፈለ።

«መልሼ ለማንሳት ህይወቴን አሳልፌ ስለምሰጥ አባቴ ይወደኛል» ዮሐ.10፡17) በማለት ኢየሱስ ተናግሮአል። ይህ ማለት «አባቴ ይወዳችኋል፤ እኔ ደግሞ እናንተን ለመዋጀት ህይወቴን አሳልፌ በመስጠቴ አብልጦ ይወደኛል። በእናንተ ምትክ በመሞቴ፣ የደኅንነታችሁ ዋስትና በመሆኔ፤ ህይወቴን በመስጠቴ፣ ዕዳችሁንና መተላለፋችሁን በመውሰዴ በእርግጥም እኔ የአባቴ ነኝ:: በእኔ መስዋዕትነት እግዚአብሔር ጻድቅ ይሆናል፤ በእርግጥም እርሱ

በኢየሱስ የሚያምነውን ሁሉ ያጸድቃል።»ከእግዚአብሔር ልጅ በቀር ደኅንነት ሊያስገኝልን የሚችል አንዳችም ሌላ የለም። በአባቱ እቅፍ ያለው እርሱ ብቻ ነው እግዚአብሔርን መተረክ የሚችለው፡፡ የእግዚአብሔርን ፍቅር ከፍታና ጥልቀት የሚያውቀው እርሱ ብቻ ነው ሊገልጽልን የሚችል። የአብን ፍቅር በክርስቶስ ከተፈጸመው ዘላለማዊ መስዋዕት ውጪ በኃጢአት ለወደቀውና ለጠፋው ሰብዓዊ ፍጡር ሌላ ማንም ሊገልጽ አይችልም።

«እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና» እርሱ ልጁን የሰጠው ከሰዎች ጋር አብሮ እንዲኖር ብቻ ሳይሆን ኃጢአታቸውን እንዲሸከምና ለእነርሱ መስዋዕት ሆኖ እንዲሞት ጭምር ነው፡፡ በዚህ መልኩ እግዚአብሔር ልጁን

በኃጢአት ለወደቀው ሰብዓዊ ዘር መረጠ። ክርስቶስ እራሱን ከሰዎች ፍላጎትና አንገብጋቢ ችግራቸው ጋር አዛመደ:: ከአብ ጋር አንድ የነበረው አምላክ እራሱን በማይበጠስ ገመድ ከሰው ልጆች ጋር አስተሳሰረ:: ኢየሱስ «ወንድሞች ብሎ ሊጠራን አያፍርም» (ዕብ. 2:11)። መስዋዕታችን፣ ጠበቃችንና ወንድማችን የሆነው ኢየሱስ የእኛን ሰብዓዊ ተፈጥሮ በመጋራት በአባቱ ዙፋን ፊት የሚገኝ ሲሆን፤ በተጨማሪም እርሱ ፍጻሜ ለሌላቸው ዘመናት ከዋጀው የሰው ልጆች ዘር ጋር አንድ ነው:: ይህ ሁሉ የሆነው ሰብዓዊው ፍጡር ከውድቀት ተነስቶ እንዲሁም ከኃጢአት አዘቅት ወጥቶ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ያንጸባርቅና የቅድስናን ክብር ይጋራ ዘንድ ነው።

የደኅንነታችንን ዋጋ በመክፈል ዘላለማዊው አባት ልጁ ይሞት ዘንድ በመስጠት የከፈለው ዘላለማዊ መስዋዕት፤ እኛ በክርስቶስ ምን ልንሆን እንደምንችል ከፍ ያለ ግንዛቤ ሊያስጨብጠን ይገባል። በመንፈስ የተነካው ሐዋርያው ዮሐንስ እግዚአብሔር አብ ለጠፋው ዘር ያለውን ፍቅር ከፍታ፣ ጥልቀትና ስፋት ባስተዋለ ጊዜ፣ በታላቅ አምልኮና አክብሮት ተሞልቶ ነበር። የዚህን ፍቅር ታላቅነትና ርኅሩኅነት ያስተዋለው ዮሐንስ፣ ይህን እንዴት እንደሚገልጸው ተስማሚ የሆነ ቋንቋ በማጣት፡- ‹‹የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው!» (1ኛ ዮሐ. 3:1) በማለት ይናገራል። ይህ ለሰዎች የተሰጠው ዋጋ እንዴት ያለ የከበረ ነው! የሰው ልጆች በመተላለፋቸው ጠንቅ የሰይጣን ተገዢዎች

ለመሆን በቁ። በክርስቶስ መስዋዕትነት ላይ በሚኖር እምነት ግን የአዳም ልጆች የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ቻሉ። ክርስቶስ ሰብዓዊውን ተፈጥሮ በመውሰድ በኃጢአት የወደቀውን ሰብዓዊ ፍጡር ከፍ ከፍ አደረገው፡፡ ኃጢአተኞችም ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት በመፍጠራቸው ምክንያት በእርግጥ «የእግዚአብሔር ልጆች» ለመባል የሚገባቸው ሆነ፡፡

እንዲህ ያለው ፍቅር አቻ የለውም። የሰማያዊው ንጉሥ ልጆች! የከበረ ተስፋ! ይህ ሁልጊዜ ልናሰላስለው የሚገባን ተስፋ ነው! እርሱን ላልወደደው ዓለም የተበረከተ አቻ የሌለው ፍቅር! ይህ ሐቅ ነፍሳችንን በሐሴት የመሙላት ኃይል ያለው ሲሆን፤ ደግሞም ራሳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንድናስገዛ የሚያደርግ ነው፡፡ መለኮታዊውን ባህሪ

በመስቀሉ ብርሃን ባጠናን ቁጥር፥ ምህረት፣ አፍቃሪነትና ይቅር ባይነት ከፍትሕና ከአድልዎ ነፃ ከመሆን ጋር ሕብረት ሲፈጥሩ እንመለከታለን። እንዲሁም እናት መንገዱን ለሳተው ልጇ ካላት ናፍቆትና ርኅራኄ ጋር ሲነጻጸር እጅግ የላቁትን ሊቆጠሩ የማይችሉትን ዘላለማዊ የፍቅሩን መረጃዎች አብልጠንና ለይተን እናያለን።

## ምዕራፍ 2 - ኢየሱስ ለኃጢያተኛው ስስማስፈስጉ

ሰው በመጀመሪያ ከፍ ያለ ማዕረግና ችሎታ እንዲሁም ሚዛኑን የጠበቀ አስተሳሰባዊ ዉበት ነበረው። ሰው በፍጡርነቱም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በነበረው ኅብረት ፍጹም ነበር። አስተሳሰቡ በንጽህና የተሞላ ዓላማውም ቅዱስ ነበር። ሆኖም በአለመታዘዝ ጠንቅ የነበረውን ችሎታ አጣ፣ እራስ ወዳድነት በፍቅር ቦታ ተተካ። ሰብዓዊው ተፈጥሮ የተሰጠውን ትእዛዝ በመተላለፉ ደካማ ሆነ። ይህን ተከትሎም በራሱ ብርታትና ጥንካሬ ክፋውን መቋቋም የማይችል ሆነ። ሰው በሰይጣን ግዞት ስር ወደቀ። እግዚአብሔር በተለየ መልኩ ጣልቃ ባይገባ ኖሮ ለዘላለም በዚህ ሁኔታ በቀጠለ ነበር።ፈጣሪ ለሰዎች የነበረውን መለኮታዊ

ዕቅድ ማሰናከል፣ ምድርን በሥቃይና መከራ መሙላት የፈታኙ ዓላማ ነበር። ይህ ሥቃይና መከራ እግዚአብሔር ሰው መፍጠሩን ተከትሎ የመጣ ውጤት እንደሆነም አድርጎ ያቀርባል።

ሰው በኃጢአት ከመውደቁ አስቀድሞ «የተሰወረ የጥበብና የዕውቀት ሐብት ሁሉ በእርሱ ዘንድ…» (ቆላ. 2፡3) ከሆነው ከአምላኩ ጋር በደስታ የተሞላ ግንኙነት ነበረው። ነገር ግን ኃጢአት ከሠራ በኋላ በቅድስናው ያገኝ የነበረውን ደስታ አጣ፤ ይህን ተከትሎም ከእግዚአብሔር ፊት መደበቅ ፍላጎቱ ሆነ። ይህ ሁናቴ ዛሬም ዳግም ባልተወለደ ልብ ውስጥ ይስተዋላል።እንዲህ ዓይነቱ ልብ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ስለሌለው ከእርሱ ጋር አንድነት በመፍጠር ደስታ

አያገኝም።ኃጢአተኛው እግዚአብሔር ባለበት ቦታ በመገኘቱ አይደሰትም፤ ከቅዱሳን ጋር ሕብረት ከማድረግ ይሸሻል። ይህ ሰው ሰማይ እንዲገባ ቢፈቀድለት እንኳ ሰማይ አስደሳች ስፍራ ሊሆንለት አይችልም። ከክርስቶስ ጋር በሰማይ የሚነግሠው እያንዳንዱ እራስ ወዳድነት ያልተጠናወተው አፍቃሪ ልብ ፍጹም ከሆነው አምላክ ጋር ልብ ለልብ የተሳሰረ አንድነት ሲፈጥር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የሌላት ልብ ግን ከፈጣሪዋ ጋር የሚያገናኛት መስመር በመበጠሱ ምላሽ መስጠትም ሆነ መቀበል አትችልም:: የግለሰቡ አስተሳሰብም ሆነ ፍላጎት በዚያ ስፍራ ከሚኖሩ ጻድቃን ጋር የሚጻረር ይሆናል። ግሩም ጣዕም በተላበሰው በሰማያዊው ዜማ መሃል እርሱ ግን ምላሽ የማይሰጥ የተበጠሰ የሙዚቃ ክር ይሆናል። ለእንዲህ ያለው ሰው ሰማይ የሥቃይ ስፍራ

ይሆንበታል።ለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እንደ ጸሐይ ከሚያበራላትና የደስታዋ ማዕከል ከሆነው ጌታ ለመደበቅ ይናፍቃል። የኃጢአተኛው ከሰማይ መቅረት በእግዚአብሔር በኩል ያለ በቂ ምክንያት በችኮላ የታወጀ ውሳኔ አይደለም።ነገር ግን መጀመሪያውኑ ግለሰቡ ራሱ ከዚህ አምላክ ጋር ወዳጅነት ለመመስረት ፈቃደኛ አልነበረም። አምላካዊው ክብር ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች እንደሚፋጅ እሳት ነው:: እነርሱን ለማዳን ሲል የሞተውን ጌታ ፊት ላለማየት ሲሉ መደበቅን በመምረጥ ጥፋት በላያቸው ላይ እንዲመጣ ይመኛሉ።

ከሰመጥንበት የኃጢያት አረንቋ በራሳችን አምልጠን በመውጣት አንችልም።

ከሰመጥንበት የኃጢአት አረንቋ በራሳችን
አምልጠን መውጣት አንችልም፡ልባችን
በክፋት ተሞልቶአል ልንለውጠውም
አንችልም።ለመሆኑ «ከርኩስ ነገር ውስጥ
ንጹህን ማን ሊያወጣ ይችላል? አንድ እንኳ
የሚችል የለም!» (ኢዮ. 14፡4)። «ለኃጢአት
የተገዛ አእምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ
ነው» (ሮሜ 8፡1)። ትምህርት፣
ባህል፣መልካም ውሳኔ መወሰን ፣ የአእምሮን
አቅም አሟጦ መጠቀም፣ እንዲሁም
ሰብዓዊው ጥረት እኚህ ሁሉ የራሳቸው
አግባብና ጠቀሜታ ያላቸው ቢሆኑም ነገር
ግን እዚህ ላይ አቅመቢስ ሆነው
እናገኛቸዋለን። እነዚህ ነገሮች ምናልባት
የታረመ ውጫዊ ባህሪ ማፍራት ቢችሉም
ልብን መቀየር ግን አይሆንላቸውም ፤
የህይወትን ምንጮች ሊያነጹ አይችሉም።
ሰዎች ከኃጢአተኝነት ወደ ቅድስና

ከመለወጣቸው አስቀድሞ፣አዲስ ህይወት ሊሰጣቸው የሚችል ከላይ የተላከ ኃይል በውስጣቸው ሊሠራ የግድ ነው:: ያ ኃይል ደግሞ ክርስቶስ ነው:: የእርሱ ጸጋ ብቻውን ለደረቀችው ነፍስ የለመለመ ህይወት በመስጠት በቅድስና ወደ እግዚአብሔር ሊስባት ይችላል።

ማንም ከላይ «ካልተወለደ»፣ አዲስ ልብ፣ አዲስ መሻት፣ አዲስ ዓላማ ወይም አዲስ ተነሳሽነት ካልተቀበለ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» ዮሐ 3:3) በማለት አዳኙ ተናግሮአል። «ሰው በተፈጥሮው የተላበሰውን መልካም ነገር ማጎልበት ብቻውን በቂ ነው» የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ለሞት የሚያደርስ ማታለያ መንገድ ነው። «መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር

ሊቀበል አይችልም፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊረዳው አይችልም» (1ኛ ቆሮ. 2:14)። «ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ ስላልሁህ አትገረም» ዮሐ. 3:7)። ስለ ክርስቶስ እንደሚከተለው ተጽፎአል (ህይወት በእርሱ ነበረች ፤ ይህች ህይወት የሰው ብርሃን ነበረች» (ዮሐ. 1፡4)። «እንድንበት ዘንድ ለሰዎች ከሰማይ በታች የለምና» (ሐዋ. 4፡12)።

የእግዚአብሔርን አፍቃሪነትና ደግነቱን፣ ርኅራኄውንና አባታዊ ጥንቃቄውን መገንዘብ ብቻውን በቂ አይደለም። እንዲሁም በዘላለማዊው የፍቅር መርኅ ላይ የተመሰረተውን አምላካዊውን ጥበብና የሕጉን ፍትሐዊነት መረዳት ብቻውን የትም አያደርስም:: ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን

በማወቁ ነበር እንዲህ የተናገረው፡- «ሕጉ በጎ እንደሆነ እመሰክራለሁ» «ስለዚህ ሕጉ በራሱ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዙም ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው» (ሮሜ 7፡12)። ሐዋርያው ነፍሱን ዘልቆ ይሰማው ከነበረ ታላቅ ሥቃይና ተስፋ መቁረጥ በመነሳት «እኔ ግን ለኃጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥኩ ሥጋዊ ነኝ» (ሮሜ 7፡14) በማለት ጨምሮ ይናገራል።

ሐዋርያው ሊደርስበት ያልቻ ለውን ንጽህናና ጽድቅ በመናፈቅ «እኔ ምን ዓይነት ጎስቋላ ሰው ነኝ! ከዚህ ለሞት ከሰተጠ ሰውነት ማን ሊያድነኝ ይችላል? » (ሮሜ 7:24) በማለት ሲጮኽ ይደመጣል። እንዲህ ያለው ለቅሶ በዘመናት ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ኃጢአት ከተጫናቸው ልቦች ወደ ሰማይ ሲተም ኖሮአል። ለእነዚህ ወገኖች መልሱ አንድ ሲሆን ይኸውም «እነሆ! የዓለምን ኃጢአት

የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ዮሐ. 1:29) የተሰኘ ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ በተለያዩ ብዙ ምሳሌዎች ይህን እውነት ግልጽ ሲያደርግ እንመለከታለን። ይህን የሚያደርግበት ምክንያትም ከኃጢአት የጸጸት ሸክም ነጻ ለመሆን ለሚናፍቁ ነፍሳት የእግዚአብሔርን ዓላማ ግልጽ ለማድረግ ነው። ኤሳውን የማታለል ኃጢአት ከፈጸመ በኋላ ያዕቆብ ከአባቱ ቤት ሲኮበልል የጸጸት ስሜት አደቀቀው። በብቸኝነት የተዋጠውና ነቀፌታየደረሰበት ያዕቆብ ከደከመባቸውና መላ ህይወቱን የከበረ አድርገውለት ከነበሩ ነገሮች ተለየ፥ነገር ግን ከሁሉ በላይ ነፍሱን የተጫነው ነገር ቢኖር ሰማይ እንዳይተወውና ኃጢአቱ ከእግዚአብሔር እንዳይለየው ያደረበት ስጋት ነበር።ፀሐይዋ ስትጠልቅ

ዙሪያውን በኮረብቶች የተከበበውና ልቡ በሐዘን የተሞላው ያዕቆብ፤ በብሩህ ከዋክብት በደመቀው ሰማይ ስር እንቅልፍ ወሰደው:: እንግዳ ብርሃን በሕልሙ ያየው ያዕቆብ እርሱ ተኝቶ ከነበረበት ስፍራ አንስቶ ጫፉ ሰማይ ደጃፍ የሚደርስ በረጅሙ የተዘረጋ መሰላል አየ።በዚህ መሰላል ላይ የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡና ይወርዱ ነበር። ይህ ሰማያዊ ክብር እየተገለጸ እያለ፤ ማጽናኛና ተስፋ የያዘ መለኮታዊ ድምፅ ተሰማ። በዚህም አዳኙን ነፍሱ አጥብቃ ለናፈቀችው ለያዕቆብ ሁሉም ነገር ግልጽ ሆነለት። ያዕቆብ ኃጢአተኛም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንዲኖረው የሚያስችለው ሰማያዊ መንገድ ተገልጾለት በደስታና በምስጋና ተመለከተ። ያዕቆብ በሕልሙ የተመለከተው ምስጢራዊ መሰላል

ሰውንና እግዚአብሔርን በብቸኝነት የሚያገናኘውን ኢየሱስን የሚወክል ነበር።

ይህ የመሰላል ተምሳሌት ክርስቶስ ከናትናኤል ጋር ካደረገው ንግግር ጋር ተመሳሳይ ነው «ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ» (ዮሐ. 1:51)። ሰው በአምላኩ ላይ ክህደት በመፈጸም እራሱን ከእግዚአብሔር ነጠለ፤ ይህን ተከትሎም ምድር ከሰማይ ተለያየች። በሰማይና በምድር መሃል ግዙፍ ሸለቆ ቢከሰትም ነገር ግን በክርስቶስ አማካኝነት ምድር ዳግመኛ ከሰማይ ጋር ተገናኘች። ኃጢአት የፈጠረውን ሸለቆ ክርስቶስ አገናኘው። አገልጋዮች መላእክትም ከሰዎች ጋር ዳግመኛ ግንኙነት ሊኖራቸው ቻለ። ደካማና ረዳተቢስ የሆነውንና በኃጢአት

የወደቀውን ሰው ክርስቶስ ከዘላለማዊው የኃይል ምንጭ ጋር አገናኘው፡፡

በምድር ያሉትን ልጆቹን እግዚአብሔር የሚወድበት ፍቅር ከሞት የበረታ ፍቅር ነው።

ሰዎች በኃጢአት ለወደቀው ሰብዓዊ ዘር ብቸኛ የተስፋና የእርዳታ ምንጭ የሆነውን ችላ ብለው ለማምጣት የሚያልሙት ዕድገትም ሆነ የሰብዓዊውን ፍጡር ባህርይ ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት ሁሉ ከንቱ ነው። «በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ» (ያዕ. 1:17) ከእግዚአብሔር ናቸው።ከእርሱ ውጪ ማንም በእውነት የከበረን ባህሪ ማግኘት አይችልም።ወደእግዚአብሔር ለመድረስ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ደግሞ ክርስቶስ ነው። «መንገዱ እኔው ነኝ፤

እውነትና ህይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» በማለት ስለ እራሱ ይናገራል (ዮሐ. 14፡6)።

በምድር ያሉትን ልጆቹን እግዚአብሔር የሚወድበት ፍቅር ከሞት የበረታ ፍቅር ነው። ልጁን ለእኛ መስዋእት እንዲሆን በመስጠት መላውን ሰማይ በአንድ ስጦታ አጠቃልሎ ሰጥቶናል። የአዳኙ ህይወት፣ ሞት ትንሳኤና አማላጅነት፣ እንዲሁም የመላእክት አገልግሎት፣ የመንፈስ ቅዱስ ተማጽኖ፣ አብ ከላይ ሆኖ መሥራቱ እነዚህ ሁሉ የማያቋርጡ ሰማያዊ ጥረቶች በኃጢአት ለወደቀው ለሰው ልጅ ደኅንነት በኣንድነት የሚሠሩ ናቸው።

ለእኛ ሲል ስለ ተከፈለው አስደናቂ መስዋዕት ዘወትር እናስብ! ሰማይ የጠፉትን ዳግም

የራሱ ለማድረግና መኖሪያቸው እንደገና በአብ ዘንድ እንዲሆን የሚሠራውን የማያቋርጥ ሥራና የሚያፈሰውን ጉልበት በመመልከት አድናቆታችንን ለመግለጽ እንጣር። ከዚህ የሚበልጥ ኀይል የትም አይገኝም፤ የሚጠብቀን ሽልማት፣ በሰማይ ያለው ደስታ ከመላእክት ጋር የሚኖረን ህብረት፣ የእግዚአብሔር አብና የልጁ የፍቅር ህብረት፣ ለዘላለም ለሚዘልቅ ነገር ጉልበታችንን ማፍሰስ መቻል፣ እነዚህ ሁሉ ከልባዊ ፍቅር የሚመነጨውን አገልግሎታችንን ለፈጣሪያችንና ለአዳኛችን እንድንሰጥ ግድ የሚሉን ጠንካራ ማደፋፈሪያዎች አይደሉምን?

በሌላ በኩል ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው፣ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ የሚሰጠውን ፍርድ የሚያሳየው፣

አይቀሬውን ቅጣት፣ የባህርያችንን ማሽቆልቆል እንዲሁም የመጨረሻውን ዘላለማዊ ጥፋትና ሰይጣንን ከማገልገል እንድንቆጠብ ለማስጠንቀቅ ነው።

ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ምህረት አጥብቀን መመልከት አይገባንም? ለመሆኑ እርሱ ከዚህ በላይ ምን ማድረግ ይችላል? በአስደናቂ ፍቅሩ ከወደደን ከዚህ አምላክ ጋር እራሳችንን በቀጥተኛ ግንኙነት ላይ እናስቀምጥ።ወደ እርሱ አምሳል እንለወጥ ዘንድ የተዘጋጀልንን መንገድ ለመጠቀም በመትጋት ከአገልጋይ መላእክቱ ጋር ባለን ህብረት በመደሰት ከአብና ከወልድ ጋር የሰመረ ግንኙነት ይኑረን።

# ምዕራፍ 3 - ንስሓ

አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ መቆም የሚችለው እንዴት ነው? ኃጢአተኛው በምን መልኩ ነው ጻድቅ መሆን የሚችለው? ከእግዚአብሔር ጋር በቅድስና የተስማማን መሆን የምንችልበት ብቸኛው መንገድ በክርስቶስ በኩል ነው ካልን ወደዚህ አዳኝ የምንመጣው እንዴት ነው? በጴንጤቆስጤ ቀን በአንድነት ተሰብስበው የነበሩ ሰዎች ኃጢአታቸው በታወቃቸው ጊዜ «ምን እናድርግ?» (ሐዋ. 2:37-38) ብለው በመጮኽ የጠየቁት ዓይነት ጥያቄ ብዙዎች እየጠየቁ ይገኛሉ። ይህን አስመልክቶ ጴጥሮስ የሰጠው ቀዳሚ ምላሽ «ንስሓ ግቡ. . . ከመንገዳችሁም ተመለሱ» (ሐዋ. 3:19) የሚል ነበር።

ንስሓ መግባት ለሠሩት ኃጢአት ማዘንና ከኃጢአት መራቅን ያጠቃልላል። የኃጢአትን ከፉነት ካልተመለከትን በቀር ኃጢአትን ማውገዝ አንችልም:: ከልባችን ከኃጢያት እስካልራቅን ድረስ እውነተኛ መለወጥ በሕይወታችን አይኖርም።

የንስሐን ትክክለኛ ትርጉም ባግባቡ ያልተረዱ ብዙ ሰዎች አሉ። ግዙፍ ቁጥር ያላቸው ሕዝቦች «ኃጢአት መሥራታችን በራሳችን ላይ መከራ ያመጣብናል» ብለው ስለሚፈሩ ላይ ላዩን ብቻ የሚታይ ለውጥ ያደርጋሉ።እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል ይህ ንስሓ አይደለም:: ምክንያቱም እነርሱ የሚያለቅሱት ለኃጢአታቸው ሳይሆን ይመጣብናል ብለው ለሚፈሩት መከራ ነው:: ይህ ደግሞ ኤሳው በኩርነቱ ለዘላለም እንደተወሰደበት ባየ ጊዜ የተሰማው ዓይነት

ሐዘን መሆኑ ነው። በለዓም በመንገዱ ላይ ሠይፍ ይዞ የቆመውን መልአክ በተመለከተ ጊዜ ነፍሱን እንዳያጣ ፈርቶ ኃጢአቱን ያስታወቀ ቢሆንም እርሱ ይህን ያደረገው ከፉውን ተጸይፎ ከኃጢአቱ በመመለስ ትክክለኛ ንስሓ በመግባት የመለወጥ ዓላማ ኖሮት አልነበረም። የአስቆርቱ ይሁዳም ጌታውን ከካደ በኋላ «ንጹሁን ሰው አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ» (ማቴ. 27፡4) በማለት ነበር የጮኸው:: በኋለኛው የፍርድ ቀን የሚያስፈራ ኩነኔ እንደሚጠብቀው ስላወቀ ነው የበደለኝነት ስሜት ተሰምቶት መናዘዝ ግድ የሆነበት:: ይሁዳ ኋላ የሚከተለውን ስላሰበ ፍርሐት ውስጡን ናጠው እንጂ አንዳችም ነውር የሌለበትን የእግዚአብሔር ልጅ አሳልፎ በመስጠቱና የእስራኤልን ቅዱስ በመካዳቱ ልቡ አልተሰበረም ወይም የጠለቀ ሐዘን በነፍሱ ውስጥ አልተሰማውም ነበር።

ፈርዖንም እንዲሁ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ሆኖ መከራ በደረሰበት ጊዜ ከሚመጣው ቅጣት ለማምለጥ ኃጢአቱን ያስታወቀ ቢሆንም ነገር ግን መቅሰፍቱ መውረዱን ባቋረጠ ጊዜ በሰማያዊው ንጉሥ ላይ መታበዩን ቀጠለ። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ኃጢአት ላመጣው ውጤት እንጂ ስለ ኃጢአታቸው አላዘኑም።

ነገር ግን ሰብዓዊው ልብ በእግዚአብሔር መንፈስ በተማረከ ጊዜ፤ ሕሊናው ንቁ ሆኖ በሰማይና በምድር ለመንግሥቱ መሰረት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ ጥልቀትና ቅድስና ለይቶ መመልከት ይችላል «ለሰው ሁሉ ብርሃን ሰጪ የሆነው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም እየመጣ ነበር።» ዮሐ. 1:9)። ይህ ብርሃን በምስጢራዊውና በተደበቀው ልብ ላይ

የብርሃን ጨረሩን ስለሚፈነጥቅ በጨለማ የተሰወረው ሁሉ ይገለጣል። ያኔ አእምሮና ልብ በኃጢአት የተሞሉ መሆናቸውን ያምናሉ (ይቀበላሉ)።ኃጢአተኛው የእግዚአብሔርን ጻድቅነት ስለሚያስተውልና ልብን ከሚመረምረው አምላክ ፊት ለመቅረብ የኃጢአተኝነትና የመጉደፍ ስሜት ስለሚኖረው በአምላክ ፊት ለመቅረብ ፍርሃት ያድርበታል። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ የቅድስናውን ውበትና ንጽህና ባስተዋለ ጊዜ ከኃጢአቱ ለመንጻትና ከሰማይ ጋር ዳግም አንድ ለመሆን ይናፍቃል።

ዳዊት በኃጢአት ከወደቀ በኋላ የጸለየው ጸሎት የእውነተኛ ንስሓን ትርጉም ያሳያል። የእርሱ ንስሐ እውነተኛ፣ ልባዊና ጥልቅ ነበር። ዳዊት በጸሎቱ መተላለፉን ለመሸፈን ምንም

ዓይነት ጥረት ካለማድረጉ ባሻገር ከአስፈሪው ፍርድ ለማምለጥም ምኞት አልነበረውም። ዳዊት የመተላለፉን ግዝፈትና የነፍሱን መርከስ በተመለከተ ጊዜ የሠራውን ኃጢአት ጠላ። እርሱ ጸሎት ያደረገው ይቅር እንዲባል ብቻ አልነበረም የልብ ንጽሕናንም ጭምር ያገኝ ዘንድ እንጂ! በዚህም ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና አንድ ሆኖ የቅድስናን ደስታ ለማግኘት ናፈቀ፤ ይህም የሕይወቱ ቋንቋ ነበር።

«መተላለፉ ይቅር የተባለለት፥
ኃጢአቱም የተሸፈነለት፣እንዴት ብሩክ ነው!
እግዚአብሔር ኃጢአቱን የማይቆጥርበት፣
በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው፣

እርሱ ብሩክ ነው፡፡» መዝ 32:1-2

«እግዚአብሔር ሆይ እንደ ቸርነትህ መጠን
ምህረትን አድርግልኝ፤
እንደ ርህራሄህም ብዛት፣መተላለፌን
ደምስስ።
በደሌን ፈጽሞ እጠብልኝ፤
ከኃጢአቴም አንፃኝ።እኔ መተላለፌን
አውቃለሁና፤
ኃጢአቴም ዘወትር በፊቴ ነው፡፡
በሂሶጵ እርጨኝ እኔም እነፃለሁ፤
እጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ ..
አምላኬ ሆይ ንጹህ ልብ ፍጠርልኝ፤
ቀና የሆነውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።
ከፊትህ አትጣለኝ፤ ቅዱስ መንፈስህንም
ከእኔ ላይ አትውሰድ።
የማዳንህንም ደስታ መልስልኝ፤ በእሺታ
መንፈስም ደግፈህ ያዘኝ።. ..
የደህንነቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤

ደም ከማፍሰስ አድነኝ፤
እንደበቴም ስለ ጽድቅህ በእልልታ
ይዘምራል»

(መዝ. 51፡1-14)

እንደዚህ አይነቱን ንስሓ ማንም ከራሱ
ሊያመነጨው አይችልም። ነገር ግን ወደ ላይ
ከፍ ብሎ ባረገውና ለሰዎች ስጦታን በሰጠው
በክርስቶስ ብቻ ነው የሚገኘው።

ስለ ንስሃ ብዙዎች በትክክል ያላስተዋሉት
ነገር አለ። ከዚህም የተነሳ ክርስቶስ
ሊሰጣቸው የሚመኘውን እርዳታ ሳይቀበሉ
ይቀራሉ። በቅድሚያ ንስሓ ካልገቡ በቀር ወደ
ክርስቶስ መምጣትእንደማይችሉና
ንስሓውም ለኃጢአታቸው ይቅር መባል
ራሳቸውን ማዘጋጀት የሚችል እንደሆነ

አድርገው ያስባሉ። እርግጥ ነው በቅደም ተከተሉ መሰረት ከኃጢአት ይቅርታ በፊት ንስሓ ይቀድማል። አዳኝ እንደሚያስፈልገው የሚሰማው የተደቆሰውና የተሰበረው ልብ ብቻ ነው።ለመሆኑ ኃጢአተኛው ወደ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት አስቀድሞ ንስሓ እስኪገባ ድረስ መጠበቅ አለበት? ንስሓ አለመግባት ኃጢአተኛውና በአዳኙ መካከል ዕንቅፋት መሆን አለበትን?

«ኃጢተኛው የክርስቶስን ግብዣ ከመቀበሉ በፊት ንስሓ መግባት አለበት!»ብሉ መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም «እናንት ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም እረፍት እሰጣችኋለሁ» (ማቴ. 11:28) ከክርስቶስ የሚወጣው ኃይል ሰዎችን ወደ ትክክለኛ ንስሓ ይመራል። ጴጥሮስ ለእስራኤሎች «እርሱም

ለእስራኤል ንስሓንና የኃጢአትን ስርየት ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔር የሁሉ ራስና አዳኝ አድርጎ በቀን ከፍ ከፍ አደረገው»(ሐዋ. 5:31) ብሎ በተናገረ ጊዜ ነገሩን ግልጽ አደረገላቸው።ያለ ክርስቶስ መንፈስ ንስሃ ልንገባ አንችልም። ያለ ክርስቶስም ይቅር መባል አንችልም።

ክርስቶስ ትክክለኛውን ነገር እንድናደርግ ለሚገፋፋን ስሜት ሁሉ ምንጭ ነው።ኃጢአትን እንድንጠላ የሚያስችለንን ኃይል በልባችን ውስጥ መትከልም የሚችለው እርሱ ብቻ ነው። በደልና መተላለፋችንን በማመን እውነትና ንጽህናን ለማግኘት ያለን መሻት የእርሱ መንፈስ በልባችን ውስጥ እየሰራ ለመሆኑ በቂ መረጃ ነው።

«እኔ ግን ከምድር ከፍ ከፍ ባልሁ ጊዜ ሰውን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ» በማለት ኢየሱስ ተናግሮ ነበር ዮሐ. 12፡32)። ክርስቶስ ለዓለም ኃጢአት ሲል የሞተ አዳኝ መሆኑ፣ ለኃጢአተኛ ሰው ግልጽ ሊሆንለት ይገባል።የእግዚአብሔርን በግ በቀራኒዮ መስቀል ላይ ስንመለከት የደህንነት ምስጢር በአዕምሮአችን እየተገለጠ ይመጣል፤የአምላክ መልካምነትም ወደ ንስሓ ይመራናል። ክርስቶስ ለኃጢአተኞች በመሞት አዕምሮ ሊያስተውል ከሚችለው በላይ የሆነ ፍቅሩን ገለጸ፡፡ኃጢአተኛው ይህን ፍቅር በሚመለከትበት ጊዜ፣ ልቡን አለስልሶና አዕምሮውን ማርኮ ነፍሱ መንፈሳዊ ትህትና እንድታገኝ ያደርጋታል።

“ኃጢያተኛው የክርስቶስን ግብዣ ከመቀበሉ በፊት ንስሓ መግባት አለበት» ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም።

በርግጥ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ወደ ክርስቶስ የሚስባቸው ኃይል እንዳለ ከማስተዋላቸው በፊት፣ በኃጢአት ስለተሞላው መንገዳቸው ሃፍረት ተሰምቷቸው ክፉ ባህርያቸውን ይተዋሉ። ነገር ግን እውነተኛና ልባዊ ከሆነ ምኞት በመነሳት ለመለወጥ ጥረት እንዲያደርጉ የሚስባቸው ኃይል የክርስቶስ ኃይል ነው፡፡ እነርሱ ያላሰቡት ኃይል በነፍሳቸው ውስጥ አድሮ ሥራውን ይሠራል። ህሊናቸው የሚያመዛዝንና ንቁ፣ ውጪያዊ ሕይወታቸውም ያማረና የተስተካከለ ይሆናል። ኃጢአታቸው የወጋው እርሱን እንደሆነ ይመለከቱ ዘንድ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ወደ መስቀሉ እንዲመለከቱ

ሲያደርጋቸው፣ ትዕዛዛቱ ወደ እሳቤያቸው ይመጣሉ። ያን ጊዜ የሕይወታቸው ክፋትና ጠማማነት፤ እንዲሁም በነፍሳቸው ውስጥ በጥልቀት የተንሰራፋው ኃጢአት ግልጽ ሆኖ ይታያቸዋል። ስለ ክርስቶስ ጽድቅ በጥቂቱ ማስተዋል በመጀመር ራሳቸውን እንዲህ ብለው ይጠይቃሉ፡-«የሰውን ልጅ ለማዳን ይህን ያህል መስዋዕትነት ያስከፈለው ለመሆኑ ይህ "ኃጢአት» የሚባል ነገር ምንድነው? ይህ ሁሉ ፍቅር፣ ሥቃይና ውርደት የደረሰው እኛ እንዳንጠፋ ነገር ግን የዘላለም ሕይወት እናገኝ ዘንድ ነውን?»

ኃጢአተኛው ይህን የክርስቶስ ፍቅር አሻፈረኝ ብሎ ሊቃወም ይችላል።ነገር ግን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆነ ክርስቶስ ወደ ራሱ ይስበዋል። በተወደደው የእግዚአብሔር ልጅ ላይ ሥቃይ እንዲደርስ ምክንያት ለሆነው

ለኃጢአቱ ንስሓ ይገባ ዘንድ ዘላለማዊው የድነት እቅድ ወደ መስቀሉ ግርጌ ይመራዋል።

በሥነ ፍጥረት ውስጥ እየሠራ ያለው ያው መለኮታዊ አዕምሮ የሰው ልጆችን ለልቦናቸው ይናገራቸዋል። ገና ያላገኙትን ነገርም ይለምኑ ዘንድ ሊገለጽ በማይቻል መልኩ የማግኘት ጉጉት በውስጣቸው ያሳድራል። በዓለም ያሉ ቁሳዊ ነገሮች የሰዎችን ፍላጎት ማርካት አይችሉም:: የቅድስና የሆነው ደስታ የክርስቶስ ጸጋ፤ ሰላምና እረፍትን ያመጣላቸው ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ይማጸናቸዋል:: እርካታ በማይገኝበት የኃጢአት ደስታ ውስጥ ተዘፍቆ የሚገኘውን ሰብዓዊ አዕምሮ አዳኛችን በሚታየውና በማይታየው አምላካዊ እጁ እየመራ ወደ ዘላለማዊ ባርኮት ለመሳብ ያለማቋረጥ እየሠራ ይገኛል። ከዚህ

ዓለም ቀዳዳ ጉድጓዶች ውሃ ለመጠጣት በከንቱ ለሚደክሙት ሰዎች ሁሉ እንዲህ የሚል መለኮታዊ መልእክት ተልኮላቸዋል፡- «የተጠማም ሁሉ ይምጣ፤ የሚፈልግም ሁሉ የሕይወትን ውሃ በነጻ ይውሰድ» (ራእ.22:17)

ይህ ዓለም ከሚሰጠው ይልቅ የተሻለ ነገር ለማግኘት በልባችሁ የምትናፍቁ ከሆነ በውስጣችሁ የሚሰማችሁ ናፍቆት የእግዚአብሔር ድምፅ መሆኑን አስተውሉ። የንስሃ መንፈስ እንዲሰጣችሁና ክርስቶስም በማያልቀው ፍቅሩና ፍጹም በሆነው ንጽሕናው እንዲገለጽላችሁ ለምኑ። «ፍቅር ለእግዚአብሔር እና ፍቅር ለሰው» የተሰኙት የእግዚአብሔር ሕግ መርሆ ዎች ፍጹም ሆነው በአዳኙ ሕይወት ውስጥ ታይተዋል። ለሌሎች በጎ ማድረግና እራስን አለመውደድ

የክርስቶስ ሕይወት ነበር። የገዛ ራሳችንን ልብ ኃጢአተኝነት መረዳት የምንችለው፣ ወደ እርሱ ስንመለከትና ከእርሱም የሚፈነጥቀው ብርሃን በእኛ ላይ ሲያርፍ ነው:: ኒቆዲሞስ እንዳደረገው ሁሉ «ኑሮአችንና አካሄዳችን የቀና ነው፤ ባህሪያችንም የታረመ ነው» በማለት እንደ ማንኛውም ኃጢአተኛ ልባችንን በእግዚአብሔር ፊት ማዋረድ እንደሌለብን አድርገን በማሰብ እራሳችንን እናታልል ይሆናል። ነገር ግን የክርስቶስ ብርሃን በነፍሳችን ላይ በፈነጠቀ ጊዜ ምን ያህል እንደ ጎደፍን እራሳችንን በመመልከት፤ ምኞታችን ሁሉ በራስ ወዳድነት ላይ የተመሰረተመሆኑን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ጠላት እንደሆንን፣ በዚህም እያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴያችን እንደተበከለ ለይተን እንረዳለን። ታዲያ በዚህ ጊዜ የእኛ የራሳችን ጽድቅ በእርግጥም የመርገም

ጨርቅ መሆኑን በመረዳት ከዚያ በኃጢአት ከረከሰ ሕይወት ሊያነጻንና በእርሱ አምሳያ ልባችንን ሊያድሰው የሚችለው የክርስቶስ ደም ብቻ መሆኑን ለይተን እናውቃለን።

ከእግዚአብሔር ክብር የሚወጣው ጨረርና ከክርስቶስ ንጽሕና የሚፈነጠቀው ብርሃን፤ ወደ ሰብዓዊው ነፍስ ዘልቆ በመግባትና እያንዳንዱን የርኩሰት ነቁጥ ላይቶ በማውጣት፤ በእክል የተሞላውንና የተበላሸውን ሰብዓዊ ባህሪ በገሃድ ያሳያል። ቅዱስ ያልሆነውን የሰው ምኞት፣ የልብን ክህደትና የከንፈርን መርከስ ግልጽ ያደርጋል። ኃጢአተኛው ታማኝ ባለመሆን የእግዚአብሔርን ሕግ ዋጋ ቢስ ማድረጉን በማስተዋል ኃጢአትና ጉድፍ የሌለበትን ንጹሁን የክርስቶስን ባሕርይ በሚመለከትበት

ጊዜ እራሱን ይጸየፋል፤ መንፈሱ የተጎዳና የተሰቃየም ይሆናል።

ነቢዩ ዳንኤል ወደ እርሱ ተልኮ የነበረው የሰማይ መልእክተኛ የተከበበበትን ክብር ባየ ጊዜ የራሱ ደካማነትና ፍጹም አለመሆን ታወቀው።ነቢዩ በአዕምሮው ውስጥ የቀረውን ድንቅ ስሜት ሲገልጽ «ስለዚህ ይህን ታላቅ ራእይ እያየሁ ብቻዬን ቀረሁ፤ ምንም ጉልበት አልነበረኝም፤ መልኬ እጅጉን ገረጣ፤ ኃይልም አጣሁ» (ዳን 10፡8) በማለት ነበር የተናገረው:: በዚህ መልኩ የተዳሰሰች ነፍስ በውስጧ ያለውን ራስ ወዳድነት በመጥላትና በመጸየፍ፣ በክርስቶስ ጽድቅ በኩል፣ ከእግዚአብሔር ሕግና ከክርስቶስ ባሕርይ ጋር የተስማማውን የልብ ንጽሕና ለማግኘት ትመኛለች።

ጳውሎስ በሕግ የሚገኘውን ጽድቅ አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ነበር ያለው«ሕግን በመፈጸም ስለሚገኝ ጽድቅ ያለ ነቀፋ ነበርኩ» (ፊሊ. 3:6)። ነገር ግን መንፈሳዊ የሆነውን የሕጉን ባህርይ ባስተዋለ ጊዜ የራሱን ኃጢአተኝነት ተመለከተ። የሕጉን ፊደል አይተው ሰዎች ለውጫዊ ሕይወታቸው በሚሰጡት ደረጃ መሠረት፣ ጳውሎስ ከኃጢአት የታቀበ ሕይወት ነበረው ማለት ይቻላል። ነገር ግን ወደ ጠለቀው ቅዱስ ሕግ በተመለከተ ጊዜና በእግዚአብሔር እንደታየው እርሱም ራሱን ሲያይ፣ በተዋረደ መንፈስ አጎንብሶ እንዲህ ሲል ኃጢአቱን ተናዘዘ፦ «ሕጉ ሳይኖር ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ ከመጣ በኋላ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ፤ እኔም ሞትኩ» (ሮሜ 7:9)። ሐዋርያው የሕጉን መንፈሳዊ ትርጉም በተመለከተ ጊዜ የኃጢአትን አስከፊነት ለማስተዋል ቻለ።

በዚያን ጊዜ የሚመካበት የራሱ ክብር ከእርሱ ራቀ።

እግዚአብሔር ለሁሉም ኃጢአት እኩል ሚዛንና ደረጃ አይሰጠውም፡፡በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ዓይን በበደሎች መካከል የደረጃ ልዩነት አለ።ሁን እንጂ፣ በሰዎች ዓይን አንዳንድ በደሎች እንደ ቀላል የሚታዩ ሲሆን፣ በእግዚአብሔር ዓይኖች ግን ቀላል የሚባል ኃጢአት የለም። የሰው ፍርድ አድሎአዊና ፍጽምና የጎደለው ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን ነገሮችን ካሉበት ተጨባጭ ሁናቴ አኳያ ይመለከታል። የሚሰክርን ሰው ሰዎች ይንቁታል ደግሞም ይህ ኃጢአቱ ከሰማይ እንደሚያስቀረው ይነግሩታል። ይሁንና ትእቢትን፣ ራስ ወዳድነትንና የሌላውን መመኘትን ግን ሳይገስጹ ያልፉዋቸዋል። ነገር

ግን እግዚአብሔርን በእጅጉ የሚያስቆጡት ኃጢአቶች እነዚህ ናቸው። ምክንያቱም ከእርሱ ባሕርይና በኃጢአት ያልተነካው ዩንቨርስ ከባቢ አየር ከሆነው ራስ ወዳድነት ከሌለበት ፍቅር ጋር ተጻራሪ ናቸውና። በእነዚህ ከባድ ኃጢአቶች ውስጥ የወደቀ ሰው ሃፍረትና ባዶነት ተሰምቶት ወደ ክርስቶስ ጸጋ መምጣት እንዳለበት ቢያስተውልም፤ክርስቶስ ለመስጠት የሚፈልገውን በረከት እንዳይቀበል ትዕቢት ልቡን ይደፍንበታል።

«አቤቱ እኔን ኃጢአተኛውን ይቅር በለኝ» (ሉቃ. 8፡13) ብሎ ምስኪኑ ቀረጥ ሰብሳቢ በጸለየ ጊዜ የእራሱን ክፉነትና ኃጢአተኝነት መመልከት ቻለ።ሌሎችም በዚሁ መልክ ያዩት ነበር። እርሱ ግን ምን እንደሚያስፈልገው ስለተሰማው ምህረትን

እየለመነ ከበደል፣ ከሃፍረትና ከሸክሙ ጋር ወደ እግዚአብሔር ፊት መጣ። ልቡም ከኃጢአት ኃይል ነጻ ለሚያወጣው ለእግዚአብሔር መንፈስ ክፍት ነበር። በአንጻሩ ደግሞ፣ የፈሪሳዊው በትዕቢት የተሞላና ራስን ጻድቅ ያደረገ ጸሎት መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ገብቶ እንዳይሠራ ልቡን ያደነደነ ሰው መሆኑን ያሳያል። ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ከነበረው ርቀት የተነሳ ፍጹም ከሆነው መለኮታዊ ቅድስና ጋር ራሱን ስላላስተያየ ምን ያህል በኃጢአት መርከሱ ሊሰማው አልቻለም ነበር። በመሆኑም እርዳታን ማግኘት አልቻለም።

ሰው ኃጢአተኝነቱን ማየት ከቻለ እራሱን እስኪያስተካክል ድረስ መቆየት የለበትም:: «ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ብቁ አይደለንም» ብለው የሚያስቡ ስንቶች

ናቸው? ለመሆኑ እርስዎ በራስዎ ጥረት የተሻሉ ሰው መሆን እንደሚችሉ አድርገው ያስባሉ? «ኢትዮጵያዊ መልኩን፤ ነብርስ ዥንጉርጉርነቱን መለወጥ ይችላልን? እናንት ክፉ ማድረግ የለመዳችሁም መልካም ማድረግ አትችሉም» (ኤር 13:23)። ለእኛ እርዳታ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው:: ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ጠንከር ያለ አሳማኝ ነገር እስክናገኝ፣ የተሻለ ዕድል እስኪገጥመን ወይም በውስጣችን ቅዱስ ስሜት እስኪሰማን ድረስ መጠበቅ የለብንም:: እኛ በራሳችን ልናደርግ የምንችለው አንዳች ነገር ባለመኖሩ፤ ከእኛ የሚጠበቀው ባለንበት ሁኔታ ወደ ክርስቶስ መምጣት ብቻ ነው።

ነገር ግን እግዚአብሔር ከታላቅ ፍቅሩና ምህረቱ የተነሳ የእርሱን የማዳን ጸጋ

የሚቃወሙትን እንኳ ሳይቀር ያድናቸዋል በማለት ማንም ራሱን አያታል። የኃጢአት እጅግ አስከፊነት ሊለካ የሚችለው በመስቀሉ ብርሃን ብቻ ነው። «እግዚአብሔር እጅግ መልካም ስለሆነ ኃጢአተኞችን ወደ ውጪ አይጥልም» ብለው የሚያደፋፍሩ ሁሉ ወደ ቀራኒዮ ይመልከቱ። ክርስቶስ በመስቀል ላይ መስዋዕት የሆነበት ምክንያት ከዚያ ውጪ ሰዎች ከሚያረክሰው የኃጢአት ኃይል ሊድኑ የሚችሉበት፣ ከቅዱሱ ጋር ሕብረታቸው የሚታደስበትና እንደገና የመንፈሳዊ ሕይወት ተካፋይ የሚሆኑበት ሌላ መንገድ ስላልነበረ ነው። በመሆኑም ያልታዘዘውን ሰው ኃጢአት በመውሰድ አዳኛችን በኃጢአተኛው ምትክ መከራና ሥቃይ ተቀበለ። የእግዚአብሔር ልጅ ፍቅር፣ ሥቃይና ሞት በአንድነት የኃጢአትን አስፈሪነት ከመመስከራቸው ባሻገር ከዚያ

ለመውጣትና ከፍ ያለውን ሕይወት ተስፋ ለማድረግ ያለው ማምለጫ መንገድ ነፍስን ለክርስቶስ አሳልፎ መስጠት ብቻ መሆኑን በግልጽ ያስረዳሉ።

አንዳንድ ጊዜ ስለ ኃጢአታቸው ያላዘኑና ሃፍረት ያልተሰማቸው ሰዎች፤በስም ክርስቲያን ነን ከሚሉት ጋር ራሳቸውን በማወዳደር «እነርሱ በባህሪያቸው እራሳቸውን ያልካዱ፣ ያልሰከኑ እና ጥንቃቄ የጎደላቸው በመሆናቸው ከእኔ የሚሻሉ አይደሉም:: እንደ እኔ ፌሽታና ፈንጠዝያ ይወዳሉ» በማለት የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ ወደ ጎን በመተው፤ ለትክክለኛነታቸው የሌሎችን ስህተት እንደ መረጃ ለማሳየት ይሞክራሉ። ጌታ የሚስቱትን ሰዎች ምሳሌ አድርጎ አልሰጠንም! በመሆኑም የሌሎች ኃጢአትና ስህተት ለማንም ሰው ምክንያት

ሊሆን አይችልም። ነውር የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ ለእኛ ምሳሌ ሆኖ ተሰጥቶናል። ውጪያዊው ክርስትና ብቻ የሚታይባቸውን ሰዎች ስለ እምነታቸው ደካማነት የሚከሱና የሚተቹ ሁሉየተሻለ ሕይወት ሊያሳዩዋቸውና የከበረ ምሳሌ ሊሆኗቸው ይገባል። አንድ ክርስቲያን እንዴት ዓይነት ሕይወት ሊኖረው እንደሚገባ ላቅ ያለ ግንዛቤ እስካላቸው ድረስ የበለጠው ኃጢአት የእነርሱ አይደለምን? ሊያደርጉ የሚገባቸውን ትክክለኛ ነገር ያውቃሉ ነገር ግን አያደርጉትም፡፡

የእግዚአብሔር ልጅ ፍቅር፣ ሥቃይና ሞት በአንድነት የኃጢአትን አስፈሪነት ይመሰክራሉ።

በክርስቶስ የሚገኘውን ንጽህና በመሻት «ለነገ» ማለትን ትታችሁ ኃጢአታችሁን ሊያስተሰርይ የሚችለውን ውሳኔ ከመተግበር ወደ ኋላ አትበሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በብዙ ሺህ ሚቆጠሩ ሰዎች ለዘላለም ጥፋት የሚያደርሰውን ስህተት ፈጽመዋል።ዘመኑ አጭር በሆነ ኑሮና ባልተረጋገጠ ሕይወት ለመኖር መምረጥ የለብንም። የሚማጸነንን የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ ድምፅ ለመታዘዝ መዘግየትና በኃጢአት ለመኖር መምረጥ በሚገባ ያልተስተዋለና አስፈሪ አደጋ ያለው ነው:: ለኃጢአት ምንም ያህል ትንሽ ግምት ቢሰጠውም ነገር ግን ተደጋግሞ በተደረገ ቁጥር እየገዘፈ በመሄድ አደጋው ዘላለማዊ ጥፋትን የሚያስከትል ይሆናል። እኛ ኃጢአትን ካላሸነፍን እርሱ ያሸንፈናል፤ ለዘላለም ጥፋታችንም መንስዔ ይሆናል።

አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ መብላትን እንደ ትንሽ ነገር በመቁጠር ራሳቸውን ባይሸነግሉ ኖሮ እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ዓይነቱ አስፈሪና አሳዛኝ ውጤት ባልተከሰተ ነበር። ነገር ግን ይህ ትንሽ ነገር የማይለወጠውን የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕግ መተላለፍ ስላመጣ፣ ስብዓዊውን ፍጡር ከእግዚአብሔር ጋር አለያየው፡፡ የሞትንም ደጃፍ በመክፈት ሊነገር የማይቻል ዋይታን በዓለማችን ላይ አመጣ። ከሰው አለመታዘዝ የተነሳ ከዘመን ወደ ዘመን የማያቋርጥ የጣር ልቅሶ ከምድራችን ሽቅብ ወደ ላይ ወጣ ኖሯል። ኃጢአት ባስከተለው ውጤት የተነሳ እነሆ ፍጥረታት ሁሉ በአንድነት ሲያቃስቱና የሕመም ሥቃይ ሲደርስባቸው ይስተዋላል። ሰማይ እንኳ ሳይቀር ሰው በእግዚአብሔር ላይ ያደረገው የአመፃ ውጤት ተሰምቶታል። በዚህም ቀራንዮ መለኮታዊውን ሕግ

ለተላለፉ ማስታረቂያ ይሆን ዘንድ ለተጠየቀው አስደናቂ መስዋዕት መታሰቢያ ሆኖ ይኖራል።ስለዚህ ኃጢአትን በጭራሽ እንደ ትንሽ ነገር አንቁጠረው።

በሰው ውስጥ የሚከሰተው እያንዳንዱ ሕግን የመተላለፍ ድርጊትና የክርስቶስን ጸጋ ችላ የማለት ወይም የመቃወም ተግባር፤ ልብን ያደነድናል፤ፈቃድንም ያዳክማል፤ አእምሮንም ብልሹ እያደረገ ማስተዋልን ያደነዝዛል።ይህም አንድ ነፍስ በክርስቶስ ለመማረክ ያላትን ዝንባሌ ዝቅተኛ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሩህሩህ ለሆነው መንፈስ ተማጽኖ ራስዋን ለመስጠት ያላትን ችሎታ በእጅጉ አናሳ ያደርገዋል።

ብዙዎች የቀረበላቸውን የምህረት ግብዣ በማቅለል የሚመርጡትን ክፉና የተሳሳተ

አቅጣጫ በማንኛውም ጊዜ መለወጥ እንደሚችሉ አድርገው ያስባሉ። በዚህም የተረበሸ ህሊናቸውንና አስተሳሰባቸውን ለማረጋጋት ይሞክራሉ። ስሜታቸው ግን አሁንም ገና በዚያው ሁናቴ ውስጥ ተማርኮ ይገኛል። የጸጋን መንፈስ ንቀው ሁለንተናቸውን ለሰይጣን ካስገዙ በኋላ አስፈሪ ነገር በገጠማቸው ጊዜ በቅጽበት ክፉ መንገዳቸውን መለወጥ የሚችሉ ይመስላቸዋል። ይህ ግን በዋዛ የሚሆን አይደለም። በሕይወት ዘመናቸው ያካበቷቸው የሕይወት ልምምዶችና ትምህርቶች ባህርያቸውን በክፉ መንገድ ስለቀረጹት የክርስቶስን ባህርይ ሕይወታቸው ለመቀበል የሚሹ ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

አንድም ቢሆን የተሳሳተ ባህሪን ወይም የኃጢአት ምኞትን አጽንተን የምንይዝ

ከሆነ፤ በውስጣችን የነበረውን የወንጌል ኃይል ቀስ በቀስ እየሸረሸ ረው ይሄዳል። እያንዳንዱ የኃጢአት ተግባር፣ ነፍስ በእግዚአብሔር ላይ ያላትን ጥላቻ ይበልጥ እያጠናከረች እንድትሄድ ያደርጋታል። ባለማመኑ የሚጸና ወይም ለመለኮታዊው እውነት አንዳችም ምላሽ የማይሰጥ ሰው ያንኑ የዘራውን ያጭዳል። በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ከፉው እንደ ዋዛ መታየት እንደሌለበት ጠቢቡ ሰሎሞን የተናገረውን ያህል የሚያስፈራ ማስጠንቀቂያ የለም «ኃጥዕን ኃጢአቱ ታጠምደዋለች፤ በኃጢአቱም ገመድ ይታሰራል» ምሳ. 5:22

ክርስቶስ እኛን ከኃጢአት ነፃ ለማውጣት ዝግጁ ቢሆንም የእኛን ፈቃድ መጋፋት አይፈልግም:: ጽኑ በሆነ መተላለፍ ፈቃዳችን ሁሉ ለክፉው የተንበረከከ ከሆነ፣ ነጻ

የመውጣት ምኞት ከሌለንና ጸጋውን ለመቀበል የማንፈልግ ከሆነ ከዚህ የበለጠ ምን ማድረግ ይቻለዋል? ፍቅሩን ለመቃወም በወሰንነው ውሳኔ ራሳችንን አጠፋን ማለት ነው:: በተወደደ ቀን ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ» (2ኛ ቆሮ. 6:2) «ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፤ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣ በምድረ በዳ በፈተና ቀን፣ በዐመጽ እንዳደረጋችሁት፣ልባችሁን አታደንድኑ» (ዕብ. 3:7-8)።

«ሰው የውጪውን ገጽታ ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል› (1ኛ ሳሙ. 16፡7)። ይህ ልብ ደስታና ሃዘን የሚፈራረቁበት፣ የሚሳሳት፣ ስሜታዊ፣ ርኩሰትና አታላይነት የተሞሉበት ልብ ነው:: እግዚአብሔር የሰውን ሃሳብ እንዲሁም ሊያደርግ ያቀደውን ሁሉ ያውቃል።

በመሆኑም ባሉበት ሁናቴ ከእነ ጉድፍዎ ወደ እርሱ ይሂዱ ፤ እንደ ባለ መዝሙሩም ሁሉን ለሚያይ አምላክ ልቦናዎን ከፍተው እንዲህ ይበሉት «እግዚአብሐር ሆይ መርምረኝ ልቤንም እወቅ፤ ፈትነኝ ሃሳቤንም እወቅ፤ የክፋት መንገድ በውስጤ ቢኖር እይ፤ በዘላለምም መንገድ ምራኝ።» (መዝ. 139:23-24)

ብዙዎች ገና ልባቸው ሳይነጻ በአእምሮ እውቀት ላይ ብቻ የተመሰረተ ሃይማኖትና የአምልኮ መልክ ያለው ውጪያዊ ሃይማኖተኝነትን ይዘው ይኖራሉ። ጸሎትዎ እንዲህ ይሁን «አምላኬ ሆይ ንጹህ ልብ ፍጠርልኝ፤ ቀና የሆነውንም መንፈስ በውስጤ አድስ» (መዝ. 51፡10)። ከነፍስዎ ጋር በሐቀኝነት ይነጋገሩ፣ ይህ የሕይወትና የሞት ጥያቄ ስለሆነ በቆራጥነትና በጽናት

ይቁሙ፤ ይህ በእርስዎና በእግዚአብሔር መካከል ዘላለማዊ መፍትሔ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል በጸሎት መንፈስ ያጥኑ። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ በእግዚአብሔር ሕግና ክርስቶስ ሕይወት ውስጥ የተገለጠውን ያለ ቅድስና «ማንም ጌታን ማየት አይችልም የሚለውን ታላቅ መርህ ይመለከታሉ (ዕብ. 12፡14)።የእግዚአብሔር ቃል ኃጢአተኝነታችንን እንድናምን ይረዳናል፣ የድነትንም መንገድ ግልጽና ቀጥተኛ አድርጎ ያሳየናል። የእግዚአብሔር ቃል ለነፍስዎ ሲናገር ሳለ ተገቢውን ትኩረት ይስጡ፡

ኃጢአትን ካሳሸነፍን እርሱ ያሸንፈናል፣ ለዘላለም ጥፋታችንም መንስዔ ይሆናል።

ክርስቶስ የመጣው ኃጢአተኞችን ሁሉ ሊያድን እንደመሆኑ የኃጢአትን ግዝፈትና እርስዎ የሚገኙበትን ሁናቴ በመመልከት ተስፋ አይቁረጡ፡ እኛ እግዚአብሔርን ከራሳችን ጋር አላስታረቅነውም ነገር ግን ድንቅ በሆነ ፍቅር እግዚአብሔር በክርስቶስ «ዓለምን ከራሱ ጋር አስታረቀ» (2ኛ ቆሮ. 5:19)።የሳቱት ልጆቹን ልብ ወደ እርሱ ለመመለስ ሩህሩህ በሆነው ፍቅሩ ይለምናቸዋል። እግዚአብሔር ሊያድናቸው የሚፈልገውን ሕዝቦቹን የሚታገሰውን ያህል ምድራዊ ወላጆች የልጆቻቸውን ስህተትና በደል ሊታገሱ አይችሉም:: በደለኞችን የእርሱን ያህል በርህራሄ የሚማጸን የለም::ከቀናው መንገድ ላፈነገጠው ነፍስ እንደ እርሱ ዓይነት የርህራሄ ልመና ያፈሰሰ አንዳችም ሰብዓዊ ከንፈር የለም:: እርሱ

የሰጠን ተስፋና ማስጠንቀቂያ ሁሉ ሊነገር የማይችል የፍቅር እስትንፋስ ነው።

ትልቁ ኃጢአተኛ እርስዎ መሆንዎን ሰይጣን ሊነግርዎ በመጣ ጊዜ ሽቅብ ወደ አዳኝዎ ኢየሱስ በመመልከት ስለከፈለልዎ ዋጋ ይናገሩ። ይህም ወደ እርሱ የብርሃን ጨረር እንዲመለከቱ ይረዳዎታል። ኃጢአትዎን ይመኑ፤ለጠላትም «ክርስቶስ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደ ዓለም መጣ» (1ኛጢሞቴ. 1፡15) ብለው ይንገሩ። እርስዎ የሚድኑት ወደር በሌለው ፍቅሩ ነው፡፡ ኢየሱስ ሁለት ተበዳሪዎችን አስመልክቶ ስምዖንን እንዲህ ሲል ጠየቀው፡- «አንድ ሰው ከጌታው ጥቂት ገንዘብ ተበደረ፤ ሌላው ደግሞ ብዙ ገንዘብ ተበደረው እናም አበዳሪያቸው ሁለቱንም ይቅር አላቸው። ታዲያ የትኛው ተበዳሪ ይበልጥ ጌታውን

ይወድ ይመስልሃል?» ስምዖንም ሲመልስ «ብዙው ዕዳ የተተወለት ይመስለኛል» አለው (ሉቃ. 7፡43)። የኃጢአተኞች ቁንጮ ሆነን ሳለ ይቅር እንባል ዘንድ ክርስቶስ ለእኛ ሞተ። ክርስቶስ ስለ እኛ በአብ ፊት ይታይ ዘንድ የከፈለልን መስዋዕትነት ብቁ ነው፡፡ አብልጦ ይቅር ያላቸው ሁሉ አብልጠው ይወዱታል። ለዘላለማዊ መስዋዕቱና ለታላቅ ፍቅሩ ከዙፋኑ አጠገብ ቆመው ያወድሱታል። የእግዚአብሔርን ፍቅር በሙላት በምናስተውልበት ጊዜ የኃጢአትን አስከፊነት በሚገባ እንረዳለን፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለ እኛ የተዘረጋውን የፍቅር ሰንሰለት ስናይ፣ ክርስቶስ ለእኛ ሲል የከፈለውን ዘላለማዊ መስዋዕትነት ስንረዳ፣ ሻክሮ የነበረው ልባችን እነሆ በፍቅሩ ይቀልጣል።

# ምዕራፍ 4 - ኃጢያትን መናዘዝ

ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝና የሚተው ግን ምህረትን ያገኛል» (ምሳ. 28፡13) ከእግዚአብሔር ምህረትን የማግኛው መንገድ ቀላልና ቀና ብቻ ሳይሆን ለማገናዘብም አስቸጋሪ አይደለም። ለኃጢአታች ይቅርታ እናገኝ ዘንድ ከባድና ራሳችንን የሚጎዳ ነገር እንድናደርግ ጌታ አይፈልግብንም:: መተላለፋችን እንዲደመሰስና ነፍሳችንን ለሰማይ አምላክ አደራ ለመስጠት ረጅምና አድካሚ የምናኔ ጉዞ ማድረግ ወይም ህመም ያለው የንስሐ ቅጣት መቀበል አያሻንም። ነገር ግን ኃጢአቱን የተናዘዘ ጠተዋትም ምህረትን ያገኛል።

በዚህ ዙሪያ ሐዋርያው «ስለዚህ ኃጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፤ትፈወሱም ዘንድ አንዱ ለሌላው ይጸልይ» (ያዕ. 5:16 በማለት ይናገራል።ኃጢአታችሁን ሁሉ ይቅር ሊል ለሚችለው ለእግዚአብሔር ብቻ ተናዘዙ፤ስህተታችሁንም እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ። ጓደኞችሁን ወይም ጎረቤታችሁን ቅር ብታሰኙ ጥፋታችሁን አምናችሁ ተቀበሉ:: የበደላችሁትም ሰው በነጻ ይቅር ሊላችሁ ይገባዋል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ይቅር ይላችሁ ዘንድ ለምኑት:: ምክንያቱም ያ ያቆሰላችሁት ወንድም የእግዚአብሔር ንብረት በመሆኑ እርሱን በመጉዳታችሁ ፈጣሪ እና አዳኝ የሆነው ጌታ ላይ ኃጢአትን ሠርታችኋል። ጉዳዩ የሚቀርበው ብቸኛና እውነተኛ አማላጅ የሆነው ሊቀ ካህናችን ፊት ሲሆን እርሱም

«እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ይሁን እንጂ ምንም ኃጢአት አልሠራም» (ዕብ. 4:15)።

እርሱ እያንዳንዱን የኃጢአት ጉድፍ ለማንጻት ይቻለዋል። መተ ላለፋቸውን በማሳወቅ ነፍሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት በትህትና ዝቅ አድርገው ያላቀረቡት፣ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ለማግኘት ገና ይቀራቸዋል። ንስሓ መግባት ስላለብን ነገር፣ ንስሓ መግባት ካልተ ለማመድን፣ በእውነተኛው መንገድ ነፍሳችንን ካላዋረድንና በተሰበረ መንፈስ ኃጢአታችንን ካልተናዘዝን መተላለፋችን በእውነት ይቅር ይባል ዘንድ አንፈልግም ማለት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሰላም ለማግኘት ፈጽሞ አንችልም። የኃጢአት ይቅርታ ለማግኘት ያልቻልንበት ብቸኛው

ምክንያት ልባችንን በትህትና ለእግዚአብሔር ዝቅ ለማድረግ ፈቃደኞች አለመሆናችንና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መስማማት አለመቻላችን ነው፡፡ እርሱ ይህን አስመልክቶ ግልጽ መመሪያ ሰጥቷል። በግልም ሆነ በሕብረት ኃጢአታችንን ስንናዘዝ ሳለ ከልብ በመነጨ እና በነፃነት መንፈስ ልናደርገው ይገባል እንጂ በግፊት መሆን የለበትም፡፡ ከልብ የሚደረግ ንስሐ ርኅራኄው ወደማያልቅበት አምላክ በቀጥታ ያመራል። ይህንንም አስመልክቶ ባለ መዝሙሩ እንዲህ ይላል «እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፤ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል» (መዝ. 34፡18)።

እውነተኛ ኑዛዜ ሁል ጊዜ ጠቅለል ተደርጎ የሚቀርብ ሳይሆን እያንዳንዷን ኃጢአት በዝርዝር ማውሳትን ይጠይቃል።

ምናልባትም የሠራነው ኃጢአት
በእግዚአብሔር ፊት ብቻ መቅረብ ያለበት
ሊሆን ይችላል። ሰውን ጎድተን ከሆነ ወደዚያ
ሰው ቀርበን ድርጊታችንን ማመን ተገቢ ነው
በሕዝብ ፊት መናዘዝ የሚያስፈልገው
ኃጢአት ሠርተንም ከሆነ መድረክ ላይ
መናዘዝ ይጠበቅብናል። ይሁን እንጂ
የትኛውም አይነት ኑዛዜ ግልጽና ቀጥተኛ
ከመሆኑ በተጨማሪ በደለኛ የሆንበት ጥፋት
የቱ እንደሆነ የሚገልጽ መሆን አለበት ።

ለኃጢአታችን ይቅርታ እናገኝ ዘንድ ከባድና
ራሳችንን የሚጎዳ ነገር እንድናደርግ ጌታ
አይፈልግብንም።

በሳሙኤል ዘመን የእስራኤል ልጆች
ከእግዚአብሔር መንገድ ተቅበዝብዘው
በመውጣታቸው በእርሱ ላይ የነበራቸውን

እምነት አጡ። ይህን ተከትሎም ኃጢአት ባመጣው መዘዝ ይሰቃዩ ጀመር። ክፉና ደጉን ለመለየት የሚያስችላቸውን የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ ያጡት እነዚህ ሕዝቦች፤ ከታላቁ የዩኒቨርስ ገዢ ፊታቸውን በማዞር በአካባቢያቸው እንደነበሩት አሕዛብ ሊገዙ ተመኙ። እስራኤላውያኑ ሰላም ከማግኘታቸው አስቀድሞ «ንጉሥ እንዲነግሥልን በመጠየቃችን ተጨማሪ ጥፋት አደረግን» (1ኛ ሳሙ. 12:19) በማለት ግልፅ ኃጢያታቸውን ተናዘዙ። የሰሩትን ኃጢያት ስሙን በመጥቀስ መናዘዝ ነበረባቸው። የእነዚህ ሕዝቦች ምስጋናቢስነት የገዛ ነፍሳቸውን ደቆሰው፣ ከእግዚአብሔርም ለያቸው።

ኃጢአትን መናዘዝ ከልብ የመነጨ መጸጸትና መለወጥ ከሌለው በእግዚአብሔር ዘንድ

ተቀባይነት አይኖረውም። በሕይወት ውስጥ ለውጦች እንዲመጡ በመወሰን እያንዳንዱ ለእግዚአብሔር አጸያፊ የሆነው ነገር መወገድ ይኖርበታል። ይህም በእውነት ስለ ኃጢታችን የማዘናችን ውጤት ይሆናል። በእኛ በኩል ምን ማድረግ እንዳለብን ግልጽ ሆኖ ተቀምጦአል «ታጠቡ፤ ራሳችሁንም አንጹ፤ ክፉ ሥራችሁን ከፊቴ አርቁ፤ ክፉ ማድረጋችሁን ተዉ መልካም ማድረግን ተማሩ፤ ፍትህን እሹ፤ የተገፉትን አጽናኑ፤ አባት ለሌላቸው ቁሙላቸው፤ ለመበለቶችም ተሟገቱ» (ኢሳ. 1፡16 17)። «ለሰጠው ብድር የተቀበለውን መያዣ ቢመልስ፣ የሰረቀውንም መልሶ ቢሰጥ፣ ሕይወት የሚሰጡትን ትእዛዛት ቢከተል፣ ክፉ ነገርንም ባያደርግ፣በእርግጥ እርሱ በሕይወት ይኖራል፤ አይሞትምም» (ሕዝ. 33:15)።ጳውሎስ ስለ ንስሓ ሲናገር «ይህ

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነው ሐዘን እንዴት ያለ ትጋት፤ እንዴት ያለ መልስ የመስጠት ችሎታ፣ እንዴት ያለ ቁጣ፣ እንዴት ያለ ፍርሃት፣ እንዴት ያለ ናፍቆት፣ እንዴት ያለ በጎ ቅናት፣እንዴት ያለ ተግሳጽ እንዳስገኘላችሁ ተመልከቱ። በዚህም ጉዳይ ንጹሃን መሆናችሁን በሁሉ ረገድ አስመስክራችኋል» (2ኛ ቆሮ. 7:11)።

ኃጢአት ግብረገባዊውን አመለካከት ሙት በሚያደርገው ጊዜ በደለኛው የባህሪውን ጉድለት ለይቶ መመልከት አይችልም ወይም የሠራው ክፋት ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ መገንዘብ ይቸግረዋል:: ጥፋተኝነቱን ሊያመላክተ ው ለሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መንገድ ካልከፈተ በቀር በከፊል ታውሮ ኃጢአቱን ሳያይ ይቀራል። የእንዲህ ዓይነቱ ግለሰብ ንስሐ ከልብ የመነጨና ፅኑ ዓላማ ላይ

የተመሰረተ ባለመሆኑ «ይህ ባይደርስብኝ ኖሮ እንዲህ ባላረኩ ነበር» በማለት ለሠራው ስህተትና ለኃጢአቱ ሁሉ ምክንያት ይደረድራል።

አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ ከበሉ በኋላ በፍርሃትና በሐፍረት ስሜት ተዋጡ። በመጀመሪያ ወደ አዕምሮአቸው የመጣው ሃሳብ፣ ለሠሩት ኃጢአት ምክንያት በማቅረብ ከአስከፊው የሞት ቅጣት ማምለጥ የሚችሉበትን መንገድ መቀየስ ነበር። የሠሩትን ኃጢአት አስመልክቶ እግዚአብሔር ጥያቄ ባቀረበላቸው ጊዜ አዳም ሲመልስ ለኃጢአቱ በከፊል ተጠያቂ ያደረገው እራሱን እግዚአብሔርን በከፊል ደግሞ ረዳቱን ነበር «ይህች ከእኔ ጋር እንድትኖር የሰጠኸኝ ሴት፤ እርሷ ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝና በላሁ» (ዘፍ. 3:12)። ሴቲቱ

ደግሞ በእባቡ በማመካኘት እባብ አሳተኝና በላሁ» (ዘፍ. 3:13) ስትል መልስ ሰጠች። ሔዋን ለኃጢአቷ የሰጠችው ምክንያት «እባቡን ለምን ፈጠርክ? ለምንስ ወደ ገነት ይመጣ ዘንድ ፈቀድክለት?» የሚል ጥያቄ ያዘለ ሲሆን በዚህም በኃጢአት መውደቃቸው እግዚአብሔርን ተጠያቂ ሲያደርጉት ይስተዋላሉ። እራስን ፃድቅ አድርጎ የማቅረብ መንፈስ በመጀመሪያ የተጠነሰሰው በሐሰት አባት ልብ ውስጥ ሲሆን፤ ከዚያም በሁሉም የአዳም ወንድና ሴት ልጆች በጉልህ ለመታየት ቻለ። ይህ ዓይነቱ የኃጢአት ኑዛዜ ከመለኮታዊው መንፈስ ምሪት አይመነጭም በእግዚአብሔርም አዳምና ሔዋን ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡እውነተኛ ንስሐ ሰው የራሱን ስህተት ያለ ምንም ማታለልና ግብዝነት አምኖ ይቀበል ዘንድ ይመራል። ልክ

እንደዚያ ዓይኑን እንኳን ወደ ሰማይ ለማንሳት እንዳልደፈረው ምስኪን ቀረጥ ሰብሳቢ «እግዚአብሔር አምላክ ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን ይቅር በል» በማለት የልቅሶን ድምፅ ያሰማል። ንስሓ ለገባችው ነፍስ ክርስቶስ በደሙ ልመና ስለሚያቀርብላት እነሆ ስህተቱን አምኖ የሚቀበል ሁሉ ይጸድቃል።

አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ ከበሉ በኋላ በፍርሃትና በሐፍረት ስሜት ተዋጡ።

በእግዚአብሔር ቃል ላይ በምሳሌ የቀረበው ከልብ የመነጨ ንስሐና እራስን ማዋረድ ለኃጢአት አንዳችም ምክንያት ለመስጠት የማይሞክሩበትን ወይም እራስን ጻድቅ የማያደርጉበትን የኑዛዜ መንፈስ ይገልጽልናል፡፡ጳውሎስ ላደረገው ጥፋት

ምክንያት በመደርደር እራሱን ለመከላከል አልፈለገም፤ ነገር ግን መተላለፉን ሳያሳንስ እንዳለ በጥቁር ቀለም አሰፈረው «ከካህናት አለቆች ሥልጣን ተቀብዬ ብዙ ቅዱሳንን አሳስሬአለሁ፤በመገደላቸውም ተስማምቼአለሁ፤ ላስቀጣቸውም ብዙ ጊዜ ከምኩራብ ምኩራብ እየተዘዋወርሁ፣ የስድብ ቃል እንዲናገሩ አስገድዳቸው ነበር፤ በቁጣም ተሞልቼ በውጭ አገር እስከሚገኙ ከተሞች ድረስ ተከታትዬ አሳደድኳቸው» (ሐዋ. 26፡10-11)። ሐዋርያው እንዲህ ብሎ ከማወጅም ወደ ኋላ አላለም «ክርስቶስ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል እውነተኛና ሰው ሁሉ ሊቀበለው የሚገባ ነው፤ ከኃጢያተኞችም ዋና እኔ ነኝ» (1ኛ ጢሞ. 1፡15)።

በእውነተኛ ንስሐ ስር የሚገዛው ትህትናን የተላበሰውና የተሰበረው ልብ፤ለእግዚአብሔር ፍቅር እና ለከበረው ቀራኒዮ ያለውን አድናቆት ይቸራል።ልጅ ለአፍቃሪው ወላጅ አባቱ ስህተቱን እንደሚያስታውቅ ሁሉ በእውነት ንስሐ የሚገባውም ሰው ኃጢአቱን በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት ያቀርባል «ኃጢአታችንን ብንናዘዝ፤ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመጻ ሁሉ ሊያነፃን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው፡፡› (1ኛ ዮሐ. 1:9)።

## ምዕራፍ 5 - ቅድስና

እግዚአብሔር የሚከተለውን ተስፋ ሰጥቶናል «እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፤ በፍጹም ልባችሁም ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ» (ኤር.29:13)።

ሰብዓዊው ልብ ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር እስካልተማረከ ድረስ፣ በአምላካዊው አምሳል እየተቀረጽንና እርሱን እየመሰልን መሄድ አንችልም።እኛ በተፈጥሯችን ከእግዚአብሔር ተነጥለናል። እኛ የምንገኝበትን ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ እንደሚከተለው ይገልጸዋል:- «በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ» (ኤፌ. 2:1) «ራስ ሁሉ ለሕመም፤ ልብም ሁሉ ለድካም ሆኗል» (ኢሳ. 1፡5)። «በዲያብሎስ ወጥመድ» አጥብቀን ተይዘናል (2ኛጢሞ.

2:26)። እግዚአብሔር እኛን ለመፈወስና ነጻ ለማውጣት በብርቱ ይመኛል። ነገር ግን ይህ ሙሉ ለሙሉ መለወጥንና የተፈጥሮአችንን መታደስ የሚጠይቅ እስከሆነ ድረስ መላው እኛነታችንን ለእርሱ ማስረከብ ይኖርብናል።

ከጦርነቶች ሁሉ የላቀው ጦርነት ከራስ ጋር የሚደረገው ፍልሚያ ነው።እኔነት መላው ፈቃዱን ለእግዚአብሔር በማስገዛት እጁን በምርኮ ይሰጥ ዘንድ ብርቱ ፍልሚያ ይጠይቃል። በመሆኑም አንዲት ነፍስ ከመታደሷና ከመቀደሷ አስቀድሞ እራሷን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ማስገዛቷ የግድ ነው፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት ሰይጣን አስመስሎ ሊያቀርብ እንደሚሞክረው በጭፍን መገዛት እና ምክንያታዊነት

የሌለበት ኢፍትሐዊ የባርነት ሥርዓት አይደለም። በተቃራኒው እግዚአብሔር ወደ አዕምሮአችንና ህሊናችን በመምጣት «ኑና እንዋቀስ» (ኢሳ. 1:18) በማለት ለፍጡሩ ሁሉ የፍቅር ግብዣውን ያቀርባል። እግዚአብሔር ፍጡራኑን አስገድዶ ፈቃዱን የሚያደርግ አምላክ ባለመሆኑ በፈቃደኝነትና በማስተዋል ላይ ያልተመሰረተን አምልኮ መቀበል አይችልም። በግዳጅነት የተመሰረተ እራስን መስጠት እውነተኛውን የአዕምሮአዊ ዕድገትና የባህሪ መጎልበት በማገድ ሰብዓዊውን ፍጡር ከአንድ ግዑዝ ማሽን ያልተለየ ያደርገዋል። ይህ ደግሞ የፈጣሪ ዓላማ አይደለም:: እርሱ የሚመኘው የፍጥረት ሥራው አክሊል የሆነው ሰብዓዊው ፍጡር ዘወትር እያደገ በመሄድ ሊደርስ ወደ ሚችለው ከፍ ያለ ማዕረግ ላይ እንዲደርስ ነው:: እርሱ በጸጋው ወደ ራሱ ሊያመጣን

በመመኘት የተትረፈረፈ ባርኮቱን ከፊት ለፊታችን በመዘርጋት ሥራውን በእኛ ውስጥ መሥራት ይቻለው ዘንድ እራሳችንን ለእርሱ እንድናስረክብ ይጋብዘናል። ከኃጢአት እሥራት ተፈትተን የእግዚአብሔር ልጆች የሚያገኙትን በክብር የተሞላ ነጻነት እንካፈል ዘንድ እነሆ ምርጫውን ለእኛ ትቶአል። እራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ስንሰጥ፤ ከእርሱ የሚለዩንን ነገሮች ሁሉ ፍጹም መተው ይኖርብናል። ይህን አስመልክቶ አዳኙ እንዲህ ይላል «እንደዚሁም ከእናንተ ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም» (ሉቃ. 14፡33)። ልባችንን ከእግዚአብሔር የሚያርቀውን ነገር ሁሉ መተው ይገባናል። ለሐብት ቅድሚያ መስጠት የብዙዎች ጣዖት ነው:: የንዋይ ፍቅርና የተትረፈረፈ ሐብት የማግኘት አባዜ

ለሰይጣን ጠፍንጎ የሚሰጥ የወርቅ ሰንሰለት ነው፡፡ መልካም ስም ማግኘትና ዓለማዊ ክብርን መጎናጸፍ የብዙዎች ጣኦት ሲሆን፤ በንፉግነት የታጠረ የምቾት ኑሮ እየኖሩ ሌሎችን በመርዳት የሚገባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ አለመወጣት እንዲሁ ሌላው ጣዖት ነው፡፡ በመሆኑም ሙሉ በሙሉ ካልሆነ በስተቀር በከፊል የእግዚአብሔር ልጆች መሆን አንችልም፡፡

የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ፣ ትክክለኛውን ባህሪ በውስጣቸው ለመፍጠርና ድነትን ለማግኘት በራሳቸው ጥረት ብቻ እየተመኩ እግዚአብሔርን እያገለገሉ እንደሆነ አድርገው የሚያስቡ አሉ። ልባቸው ጥልቅ በሆነው የክርስቶስ ፍቅር ያልተነካ፣ «አንድ ክርስቲያን ወደ ሰማይ ለመግባት በሕይወቱ መፈጸም አለበት» ብለው

የሚያምኗቸውን ተግባራት ሁሉ ለማከናወን ይፈልጋሉ። ይህ ዓይነቱ ኃይማኖት ከንቱ ነው፡፡ ክርስቶስ በልብ ውስጥ ሲያድር ያቺ ነፍስ ከእርሱ ጋር በሚኖራት ግንኙነት አብልጣ በፍቅሩ ትሞላለች፣ ከእርሱ ጋር ትጣበቃለች እንዲሁም እርሱን ብቻ በማሰላሰል እኔነትን ትዘነጋለች። ለክርስቶስ የሚኖረን ፍቅር ለታላቅ ሥራ የሚያነሳሳ ኃይል ይሆነናል። የእግዚአብሔርን ብርቱና ግድ የሚል ፍቅር የሚለማመዱ ሁሉ «የእግዚአብሔርን መጠይቅ አሟላ ዘንድ አሳልፌ መስጠት ያለብኝ አነስተኛው ነገር ምን ይሆን?» ብለው አይጠይቁም። ከልብ በሆነ መሻት ሁሉንም ለእርሱ በማስገዛት ለዚያ ዋጋ ላለው ነገር ያላቸውን ፍላጎት ያሳያሉ። የክርስቶስን ጥልቅ ፍቅር ሳይረዱና ሳያስተውሉ እርሱን አገለግለዋለሁ ማለት

ከባዶ ወሬና ከደረቅ ሥርዓት እንዲሁም ከአድካሚ ተግባር የዘለለ አይሆንም።

ያለንን ነገር ሁሉ ለክርስቶስ መስዋዕት አድርገን መስጠታችንን እንደ ትልቅ ነገር እንቆጥረው ይሆን? «ክርስቶስ ለእኔ የሰጠው ስጦታ ምንድን ነው?» ብላችሁ እስቲ እራሳችሁን ጠይቁ። የእግዚአብሔር ልጅ መላ ሕይወቱንና ፍቅሩን በመስጠት ለእኛ ድነት ሥቃይ ተቀበለ። ይህ ታላቅ ፍቅር የማይገባን ሆኖ ሳለ እንዲህ ላደረገልን ጌታ ልባችንን መንፈግ ይቻ ለናል? የሕይወታችን እያንዳንዱ ደቂቃ የጸጋው ባርኮት ተካፋይ መሆኑን ከልብ ስለማናስተውል፤ የዳንነው ከእንዴት ያለ የከፋ አለማወቅና ሥቃይ አዘቅት ውስጥ እንደሆነ ብዙ ጊዜ እንዘነጋለን። ኃጢአታችን ወደ ወጋው ጌታ በመመልከት ስለ ፍቅሩና ስለ ከፈለው

መስዋዕትነት ስንል ማድረግ የሚገባንን ለመሥራት ፈቃደኞች ነን? የክብር ጌታ ላይ ከደረሰው ይህ ነው ተብሎ ሊገለጽ ከማይችል መጠነ ሰፊ ውርደት አኳያ ወደ ዘላለም ህይወት የምንገባው በትግልና እራስን ዝቅ በማድረግ ብቻ በመሆኑ ልናጉረመርም ይገባል?

ብዙዎች ልባቸው የታበየ «እግዚአብሔር የሚቀበለኝ መሆኑን እርግጠኛ ሳልሆን ለምን ብዬ ነው ራሴን የማዋርደው?» ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ እስቲ ወደ ክርስቶስ እንመልከት፣ እርሱ ኃጢአት የሌለበት ብቻ ሳይሆን የሰማይ ልዑልም ነበር። ይህም ሆኖ ግን ለሰብዓዊው ዘር ሲል ኃጢአት ሆነ «ከክፉ አድራጊዎችም ጋር በመቆጠሩ፣ የብዙዎችን ኃጢአት ተሸከመ፤ ስለ አመጸኞችም ማለደ» (ኢሳ. 53:12)።

ሁሉን ለእርሱ ስናስረክብ የትኛውን ነው ለራሳችን የምናስቀረው? ኢየሱስ በኃጢአት የተበከለውን ልብ በደሙ ሲያነጻ፣ ሲያጠራና ወደር በሌለው ፍቅሩ ሲያድን፤ ሰብአዊ ፍጡር ግን ሁለንተናውን ለእርሱ ማስረከቡ አስቸጋሪ እንደሆነ አድርጎ ሲያስብ ይስተዋላል። ይህ ሲነገር ስሰማም ሆነ ስጽፈው ያሳፍረኛል!

እግዚአብሔር አስፈላጊያችን የሆነውን ማንኛውንም ነገር እንተው ዘንድ አይጠይቀንም:: እርሱ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ለልጆቹ ደህንነት የሚበጀውን ነው:: ክርስቶስን ያልመረጡት ነፍሳት ሁሉ ለራሳቸው ጥቅም ከሚሹት ነገር ሁሉ በእጅጉ የላቀውን እርሱ ሊሰጣቸው የሚችል መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል። ሰው

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ የሆነውን ነገር ሲያስብና ሲያደርግ ታላቅ ጉዳትና ኢፍትሐዊነት በገዛ ነፍሱ ላይ ያደርጋል። ለፍጡሮቹ የበለጠውን የሚያውቀውና የሚያቅደው አምላክ በከለከለው ጎዳና ላይ ምንም ዓይነት እውነተኛ ደስታ ሊገኝ አይችልም። የኃጢአት ጎዳና የሥቃይና የጥፋት መንገድ ነው፡፡

የተሰጠንን የመምረጥ ኃይል በመለማመድ በሕይወት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለውጥ ማምጣት ይቻላል።

የሰው ልጅ ደስ ይሰኝ ዘንድ የሰማይ ሁሉ ፍላጎት እንደመሆኑ፤ እግዚአብሔር ልጆቹ ሲሰቃዩ በማየት ይደሰታል ብሎ ማሰብ ስህተት ነው።ሰማያዊው አባታችን በማንኛውም ፍጡር ላይ የደስታን ጎዳና

አይዘጋም።መለኮት ለእኛ የሚያቀርበው ጥሪ፣ ደስታን ከእኛ አርቀው ሥቃይና ተስፋ መቁረጥን በማምጣት ሰማያዊውን ደጃፍ ከሚያዘጉብን ኃጢአቶች እንድንርቅ ነው:: የዓለም አዳኝ የሆነው አምላክ ሰዎችን ከነመሻታቸው፣ከነጉድለታቸውና ከነድካማቸው በመቀበል ኃጢአታቸውን በደሙ በማንጻት ይቅርታን ማሰጠት ብቻ ሳይሆን ቀንበሩን ሊሸከም የሚናፍቀውን ልብ ሁሉ ያረካዋል። የሕይወት እንጀራን ፈልገው ወደ እርሱ ለሚመጡ ሁሉ ሰላምና እረፍት ሊያካፍላቸው ፈቃደኛ ነው:: እኛ እናከናውነው ዘንድ የሚጠይቀን ተግባር ሰው በራሱ ጥረት ሊደርስበት ወደ ማይችለው፣ ከፍ ያለ ደስታ ወደምናገኝበት ደረጃ እንድንወጣ ነው:: ሕይወት በእውነተኛ ደስታ የተሞላ የሚሆነው የክብር ተስፋ የሆነው

ክርስቶስ በዚያች ነፍስ ውስጥ ሲኖር ብቻ ነው፡፡

ብዙዎች «እንዴት አድርጌ ራሴን ለእግዚአብሔር ማስገዛት እችላለሁ?» ብለው ሲጠይቁ ይደመጣሉ። ራስዎን ለእርሱ ለመስጠት ቢመኙም ነገር ግን ያን ለማድረግ ወኔ ቢስና የጥርጣሬ ባሪያ በመሆንዎ በሚሠሯቸው ልማዳዊ ኃጢአቶች ቁጥጥር ስር ውለው ይሆናል። የእርስዎ ቃል ኪዳንና ቆራጥነት እንደ አሸዋ ገመድ ሊሆንም ይችላል። አጉል ሃሳብና ምኞትዎን በመቆጣጠር መሻትዎን መግዛት አልሆነልዎትም ይሆናል። ያፈረሱት ቃል ኪዳን በራስዎ ላይ ሊኖርዎ የሚገባውን ከልብ የመነጨ መተማመን ስለሚያዳክምብዎ እግዚአብሔር አይቀበለኝም የሚል ስሜት ሊሰማዎም ይችላል። ቢሆንም ግን ተስፋ

ሳይቆርጡ የፈቃድን ኃይል የተሰጠንን የመምረጥ ኃይል) ምንነት ሊያስተውሉ ይገባል። ይህ ኃይል ሰብዓዊውን ተፈጥሮ የሚገዛ፣ ውሳኔውን ወይም ምርጫውን የሚቆጣጠር ነው:: እያንዳንዱ ነገር ፈቃዳችንን ተመርኩዞን በምንወስደው እርምጃ ይወሰናል፥እግዚአብሔር የመምረጥን ኃይል ለሰዎች ስለሰጠ፣ ስጦታውን መለማመድ ደግሞ የሰዎች ድርሻ ይሆናል። ልብዎን ሊለውጡም ሆነ በልብዎ ውስጥ ያለውን ፍቅር ለእግዚአብሔር መስጠት አይችሉም:: ነገር ግን እርሱን ለማገልገል ምርጫ ዎ በማድረግ ፈቃድዎን ለእርሱ ማስገዛት ይችላሉ። ይህን ሲያደርጉ ሳለ ፈቃዱን በእርስዎ ውስጥ የሚያደርገው አምላክ እርሱ እንደሚወድና እንደሚፈቅድ መሥራት ይጀምራል። በውጤቱም መላው ተፈጥሮዎ በክርስቶስ መንፈስ ቁጥጥር ሥር

ይውላል። በልብዎ ውስጥ ለሚኖረው ፍቅር እርሱ ማዕከል በመሆን ከሃሳብዎ ጋር ውህደት ይፈጥራል።

መልካሙን መመኘትና ቅድስናን መሻት ተገቢ ቢሆንም፤ ነገር ግን በምኞት ብቻ መቅረቱ ከንቱ ነው:: ብዙዎች እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆን ተስፋ ሲያደርጉና ሲመኙ ጠፍተው ይቀራሉ። ለዚህ መንስዔው እነዚህ ሰዎች እራሳቸውን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ወደሚያስረክቡበት መንገድ ለመምጣት ባለመምረጣቸው ነው::

የተሰጠንን የመምረጥ ኃይል በመለማመድ በሕይወት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለውጥ ማምጣት ይቻላል:: ፈቃድዎን ለክርስቶስ በማስገዛት ከአለቆችና ከኃይላት በላይ ከሆነው ኃያል ጋር ራስዎን ተባባሪ ያድርጉ።

ታማኝና የማይለወጥ ሆነው ሲቆሙ፤ ብርታትን ከላይ ያገኛሉ። ያለማቋረጥ ራስዎን ለእግዚአብሔር አሳልፈው ሲሰጡ አዲስ ሕይወት መኖር ይጀምራሉ ያውም የእምነት ህይወት፡፡

## ምዕራፍ 6 - እምነትና ተቀባይነት ማግኘት

ህሊናዎ በመንፈስ ቅዱስ ሲነቃቃ የኃጢአትን ክፋት፣ ኃይል፣ ክስ እንዲሁም ዋይታውን ማስተዋል ይችላሉ:: ኃጢአትንም መጸየፍ ይመለከቱታል። ኃጢአት ከእግዚአብሔር የለየዎት መሆኑንና በክፉው ኃይል ግዞት ስር መውደቅዎን ያስተውላሉ። ከዚህ ግዞት ለማምለጥ በታገሉ ቁጥር ረዳት አልባነትዎን አብልጠው ያስተውላሉ። የሃሳብዎ መነሻም ሆነ በልብዎ ያሉት ነገሮች ንጽህና የጎደላቸው እንደሆኑና። ህይወትዎ በስስትና በኃጢአት የተሞላ መሆኑን ይመለከታሉ። በመሆኑም ይቅር ለመባል፣ ከበደል ለመንጻት እንዲሁም ነጻ ለመውጣት ይናፍቃሉ። ታዲያ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት የመፍጠርና ዳግም በአምሳሉ የመቀረጽ ዕድል ያገኙ ዘንድ ምን ማድረግ ይችላሉ?

አጥብቀው የሚሹት ነገር ቢኖር ሰማያዊውን ይቅርታና ሰላም እንዲሁም ፍቅርን ነው:: ይህን ነገር ገንዘብ ሊገዛው፣ አእምሮ በጥረቱ የግሉ ሊያደርገው ወይም ጥበብ ሊያገኘው አይችልም። እነዚህን ነገሮች ከእግዚአብሔር በስጦታ መልክ ይቀበሏቸዋል እንጂ በግል ጥረትዎ የራስዎ ለማድረግ በፍጹም ተስፋ ማድረግ አይችሉም:: እግዚአብሔር ግን «ያለገንዘብ ያለ ዋጋ» (ኢሳ. 1:18) በስጦታ መልክ ያበረክትልዎታል በመሆኑም እጆችዎን ዘርግተው መቀበል እስከ ቻሉ ድረስ በእርግጥም የእርስዎ ናቸው:: ጌታ አምላክ እንዲህ ይላል «ኃጢአታችሁ እንደ ዐለላ ቢቀላ እንደ በረዶ ይነጻል» (ኢሳ. 1፡18)። «አዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስ መንፈስም በውስጣችሁ አሳድራለሁ» (ሕዝ. 36:26)።

ኃጢአትዎን ተናዝዘዋል፤ ከልብዎም አርቀውታል። እራስዎን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ወስነዋል። ከዚህ በኋላ ወደ እርሱ በመሄድ ኃጢአትዎን እንዲያጥብልዎና አዲስ ልብ እንዲሰጥዎ ይጠይቁት። ከዚያም በገባው የተስፋ ቃል መሠረት የጠየቁትን እንደተቀበሉ ይመኑ። እግዚአብሔር ቃል የገባልንን ስጦታ የራሳችን ለማድረግ፣ እንደተቀበልነው መቁጠር እንዳለብን ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ ያስተምር የነበረው ትምህርት ነበር።

ሕዝቡ በኢየሱስ ኃይል ባመነ ጊዜ ከደዌአቸው ይፈውሳቸው ነበር። ማየት የሚችሉትን ነገር በማሳየት (አካላቸውን በመፈወስ) ፤ ማየት የማይችሉትን ይኼውም የኃጢአት ይቅርታን ለመስጠት

የሚችልበት ኃይል እርሱ እንዳለው እንዲያምኑ ይረዳቸው ነበር። ኢየሱስ ሽባውን በፈወሰ ጊዜ ይህን ሁኔታ በግልጽ ጠቅሶታል፦ «ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን የማስተሰረይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ነው» በማለት ሽባውን «ተነሳ! ቃሬዛህንም ይዘህ ወደ ቤትህ ሂድ» አለው» (ማቴ. 9:6። እንዲሁም ኢየሱስ ያደረገውን አስመልክቶ ወንጌላዊው ዮሐንስ ሲናገር «ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔርም ልጅ እንደሆነ እንድታምኑ ዘንድ፤ አምናችሁም በስሙ ህይወት እንዲኖራችሁ ይህ ተጽፎአል» (ዮሐ. 20፡31)።

የኃጢአትን ይቅርታ እናገኝ ዘንድ እንዴት በእርሱ ማመን እንዳለብን፣ኢየሱስ የታመሙትን እንዴት እንደፈወሰ ከሚገልጹ

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንኳን ሳይቀር መማር እንችላለን። በቤተሳይዳ ወደ ነበረው ሽባ ሰው ታሪክ እንመለስ። ይህ በሥቃይ ላይ የነበረ ምስኪን አንዳችም የሚረዳው ሰው አልነበረውም፤ እንዲሁም ላለፉት 38 ዓመታት አንዴም እንኳ እግሮቹን ተጠቅሞባቸው አያውቅም:: ነገር ግን ኢየሱስ «ተነሳ ቃሬዛህንም ይዘህ ሂድ» ሲል ተናገረው:: ምናልባትም ይህ ህመም የደቆሰው ሰው «ጌታ ሆይ የምታድነኝ ከሆነ ለቃልህ እታዘዛለሁ» ማለት ይችል ነበር። ምስኪኑ ሰው በዚህ ፋንታ ከክርስቶስ አንደበት በወጡት ቃላት በማመን ወዲያውኑ ማድረግ ያለበትን አደረገ። ለመራመድ ፈቃደኛ ሆነ ተራመደም፡ክርስቶስ የተናገረውን ቃል ተከትሎ ተንቀሳቀሰ፤እግዚአብሔርም ኃይል ሰጠው:: ከህመሙም ተፈወሰ።

ከዚህ ሽባ ጋር የሚያመሳስልዎት ነገር ቢኖር፣ እርስዎም እንደ እርሱ ኃጢአተኛ መሆንዎ ነው። ላለፈው ኃጢአትዎ ስርየት ማግኘት ወይም በራስዎ ብርታት ልብዎን ማንጻት አይችሉም:: ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል እነዚህን ሁሉ ያደርግልዎ ዘንድ ቃል ገብቶአል። በዚህ ተስፋ በማመን ኃጢአትዎን ይናዘዙ፣ እራስዎንም ለእግዚአብሔር ያስረክቡ። እርሱንም ለማገልገል ፈቃደኛ ይሁኑ:: እርስዎ ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ፣ እግዚአብሔርም ቃል የገባውን ለእርስዎ ይፈጽማል። ይቅር እንደተባሉና እንደነጹ በማመን የተስፋው ቃል በእርስዎ ሕይወት እንደተፈጸመ ቢያምኑ፣እግዚአብሔር ደግሞ ይህንን እምነትዎን እውን ያደርገዋል:: ልክ ኢየሱስ ለሽባው ሰው እንደተፈወሰ ባመነ ጊዜ

የሚራመድበትን ኃይል እንደሰጠው፣ እርስዎም ይድናሉ።

እንደዳኑ እስኪሰማዎት ድረስ አይጠባበቁ፤ ይልቁንም «አምናለሁ፤ ድኛለሁ፤ ይህንንም የምለው ስሜቴ መስክሮልኝ ሳይሆን እግዚአብሔር ቃል ስለገባልኝ ነው፡፡» ይበሉ።

ላለፈው ኃጢአትዎ ስርየት ማግኘት ወይም ደግሞ በራስዎ ብርታት ልብዎን ማንጻት አይችሉም።

ኢየሱስ «ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል» (ማር. 11:24) በማለት ይናገራል።ይህን ተስፋ ለመቀበል የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ ያለ ሲሆን ይኼውም በጸሎት የምንለምነው ነገር

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የተስማማ እንደሆነ ነው። በመሆኑም እነዚህን በረከቶች መጠየቅና እንደተቀበልናቸው ማመን እንዲሁም ስለተደረገልን ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን የእኛ

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የተስማማ እንደሆነ ነው። በመሆኑም እነዚህን በረከቶች መጠየቅና እንደተቀበልናቸው ማመን እንዲሁም ስለተደረገልን ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን የእኛ ፋንታ ነው። ወደ ኢየሱስ በመቅረብ ከኃጢአት እንድንነጻ እንዲሁም ከሕጉ ፊት ያለ ጸጸት ወይም ሐዘን እንቆም ዘንድ ዕድል ተሰጥቶናል «ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» (ሮሜ 8፡1)። እንደ ሥጋ ፈቃድ ሳይሆን እንደ መንፈስ ፈቃድ ይመላለሳሉና።

ስለዚህ እናንተ የራሳችሁ አይደላችሁም፤ በዋጋ ተገዝታችኋልና።« . . . የተዋጀችሁት በሚጠፋ ነገር በብር ወይም በወርቅ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ:: ነገር ግን እናንተ የተዋጀችሁት ነውርና እንከን እንደሌለበት በግ ደም፤ በክርስቶስ ክቡር ደም ነው።» (1ኛ ጴጥ. 18-19)፡እንዲህ እግዚአብሔርን በማመን ብቻ፣ መንፈስ ቅዱስ በልብዎ ውስጥ አዲስ ሕይወት እንዲወለድ አድርጓል። በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እንደተወለደ አዲስ ሕጻን ይቆጠራሉ:: እግዚአብሔርም አንድያ ልጁን በሚወድበት ፍቅር እርስዎንም ይወድዎታል።

እራስዎን ለኢየሱስ ከሰጡ በኋላ ወደ ኋላ መመለስ ወይም እራስዎን ከእርሱ መነጠል የለብዎትም። ይልቁንም በየቀኑ «እኔ የክርስቶስ ነኝ፤እራሴን ለእርሱ አሳልፌ

ሰጥቼዋለሁ» በማለት እርሱ መንፈሱን እንዲሰጥዎና በጸጋው ዙሪያ ይጠብቅዎ ዘንድ ይጠይቁት:: የእግዚአብሔር ልጅየሆኑት ራስዎን ለእርሱ በመስጠትና በእርሱ በማመን እንደሆነ፣ በእርሱ መኖርንም መቀጠል ይኖርብዎታል። ሐዋርያው እንዲህ ይላል፡- «እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ» (ቆላ. 2፡6)።

አንዳንዶች ‹የእርሱን በረከት ከመጠየቃችን በፊት ሕይወታችን የተለወጠ መሆኑን ለእግዚአብሔር ለማሳየት ለተወሰነ ጊዜ ልንፈተሽ ይገባናል» ብለው ያስባሉ። ነገር ግን የጌታን በረከት አሁኑኑ መጠየቅና የግላቸው ማድረግ ይችላሉ። ድካማቸውን ለማሸነፍ የእግዚአብሔር ጸጋና የክርስቶስም መንፈስ ያስፈልጋቸዋል። ካልሆነ ግን ክፉን

ማሸነፍ አይችሉም። ኢየሱስ ከነኃጢአታችን፣ ረዳተቢስና ጥገኛ እንደሆንን፣ ባለንበት ሁኔታ ወደ እርሱ እንድንመጣ ይወዳል። ከነደካማነታችንና መተላለፋችን በንስሓ እግሮቹ ስር መውደቅ እንችላለን። እርሱም በፍቅር እጆቹ ያቅፈናል፤ ቁስላችንን ይጠርግልናል፤ ከእርኩሰታችንም ሁሉ ያጠራናል፤ ይህንንም ማድረግ ለእርሱ ክብሩ ነው፡፡

በሺህ ለሚቆጠሩ ሰዎች ውድቀት አንዱ መንስዔ ኢየሱስ በግል ይቅር እንደሚላቸው አለማመናቸው ነው። እግዚአብሔር ቃል የገባውን በቀጥታ አይቀበሉትም። ይቅርታ ለእያንዳንዱ ኃጢአት በነጻ የመሰጠቱን ዕድል ሁሉም ለራሱ ሊያውቅና ሊቀበል ይገባል። እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ለሌሎች እንጂ እርስዎን እንደማይጨምር አድርጎ የማሰቡን

ጥርጣሬ ያስወግዱ፡ተስፋዎቹ የተሰጡት
በንስሓ በፊቱ ለሚቀርቡ ሁሉ ነውና!
በክርስቶስ አማካኝነት ብርታትና ጸጋ
በአገልጋይ መላእክቱ በኩል ለእያንዳንዱ
አማኝ ነፍስ እንዲሰጡ ተደርጎአል።
በመሆኑም በሞተለት በኢየሱስ በኩል
ብርታትን፣ ንጽህናንና ጽድቅን ማግኘት
የማይችል አንድም ኃጢአተኛ የለም፡፡
እንዲኖሩ እንጂ እንዳይሞቱ ልመናውን
የሚያቀርበው ጌታ በኃጢአት የተበከለውን
ልብሳቸውን አውልቆ ነጩን የጽድቅ ሸማ
ሊያለብሳቸው እየጠበቃቸው ይገኛል።

ሰብአዊ ፍጡራን አንዳቸው ሌላቸውን
በሚያስተናግዱበት አይነት መንገድ
እግዚአብሔር እኛን አያስተናግደንም።
የእርሱ ሐሳብ የምህረት፣ የፍቅርና በርህራሄ
የተሞላ አሳብ ነው፡፡ እንዲህም ይላል «ከፉ

ሰው መንገዱን፣ በደለኛም ሐሳቡን ይተው። ወደ እግዚአብሔር ይመለስ፤ እርሱም ምሕረት ይደረግለታል፤ ወደ አምላካችን ይመለስ፤ ይቅርታው ብዙ ነውና» (ኢሳ.55:7) «መተላለፍህን እንደ ደመና፣ ኃጢአትህን እንደ ማለዳ ጭጋግ ጠርጌ አስወግጃለሁ፤ ተቤዥቼሃለሁና ወደ እኔ ተመለስ» (ኢሳ. 44 :22)

«ማንም እንዲሞት አልሻምና፤ ይላል እግዚአብሔር፤ ወደ እኔ ተመለሱና ሕይወት ኑሩ» (ሕዝ. 18:32)። ሰይጣን ከእግዚአብሔር የተሰጠንን የተረጋገጠ በረከት ለመስረቅ ዝግጁ ነው። እርሱ እያንዳንዱን የተስፋ ጭላንጭልና የብርሃን ጨረር ከነፍሳችን ሊወስድ ይመኛል። በመሆኑም ይህ ምኞቱ እውን ይሆን ዘንድ ልንፈቅድለት አይገባም። ጆሮዎችዎን ለፈታኙ በመስጠት

ፋንታ እንዲህ ይበሉት «እኔ ህያው እሆን ዘንድ ኢየሱስ ሞተልኝ! ይወደኛል፣ እንድጠፋ የእርሱ ምኞት አይደለም። በርኅራኄ የተሞላ ሰማያዊ አባት አለኝ። ምንም እንኳ ፍቅሩን ባበላሽና በረከቱን ባባክንም ነገር ግን ተነስቼ ወደ አባቴ ቤት በመሄድ እንዲህ እለዋለሁ "አባቴ ሆይ በሰማይና በአንተ ፊት በድያለሁ፤ ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም፤ ከተቀጠሩት አገልጋዮችህ እንደ አንዱ ቁጠረኝ»። ይህ ተምሳሌት ተቅበዝብዞ የነበረው ልጅ እንዴት ተቀባይነት እንዳገኘ ያወሳል። «ነገር ግን እርሱ ገና ሩቅ ሳለ፤ አባቱ አይቶት ራራለት ወደ እርሱም እየሮጠ ሄዶ አቅፎ ሳመው» (ሉቃ. 15፡18-20)።

ይህ ልብ የሚነካ ምሳሌ እንኳ፣ የሰማያዊውን አባት ወደር የለሽ ርኅራኄ ለመግለጽ ብቁ አይደለም:: ጌታ በነቢያቱ አማካኝነት

«በዘላለማዊ ፍቅር ወድጄሻለሁ፤ ስለዚህም በርኅራኄ ሳብሁሽ» (ኤር. 31:3) በማለት ይናገራል። የጠፋው ልጅ ከአባቱ ቤት ርቆ በባዕድ አገር የነበረውን ሁሉ ያባከን በነበረበት ጊዜ የአባቱ ልብ እርሱን ይናፍቅ ነበር። ይህ የአባቱ መናፈቅ ልጁ ወደ እግዚአብሔር ይመለስ ዘንድ ነፍሱን ያነቃ፣ ያባብል እንዲሁም በፍቅር ወደ ተሞላው የአባቱ ልብ ይስበው ነበር።

ይህ ሲነገር በማይቻል ፍቅር የተሞላው ልብ፣ ስፍር ቁጥር በሌለው ግዙፉ አምላካዊ ርኅራሄ ኃጢአተኛውን ወደ ራሱ ይስባል።

በተስፋ የተሞሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ከፊትዎ ተገልጠው እያሉ ለጥርጥር ቦታ ሊኖርዎ ይችላል? ኃጢአቱን ለመተውና ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ የሚናፍቀው

ምስኪኑ ኃጢአተኛ በንስሐ ወደ እግሮቹ ስር እንዳይመጣ ጌታ ይከለክለዋል ብለው ያምናሉ? ከእንዲህ ያለው አስተሳሰብ አጥብቀው ይራቁ! ሰማያዊውን አባትዎን በዚህ መልኩ ከማሰብ በላይ ነፍስዎን ሊጎዳ የሚችል አንዳች ነገር የለም። ኃጢአትን የሚጠላውና ኃጢአተኛውን የሚወደው አምላክ ሁሉም ይድኑና በክብር መንግሥት ዘላለማዊ በረከት ያገኙ ዘንድ በክርስቶስ ውስጥ ሆኖ እራሱን ሰጠ። እርሱ ለእኛ ያለውን ፍቅር ለማሳየት ከመረጠበት መንገድ ውጪ ምን ዓይነት የጠነከረ ወይም ይበልጥ በርኅራኄ የተሞላ ቋንቋ መጠቀም ይችል ነበር? «እናት የምታጠባውን ልጇን ልትረሳ ትችላለችን? ለወለደችውስ ልጅ አትራራለትምን? ምናልባት እርሷ ትረሳ ይሆናል፤ እኔ ግን አልረሳሽም» (ኢሳ. 49፡15)።

በጥርጣሬና በፍርሃት ወጀብ ውስጥ እየዋለሉ ከሆነ ቀና ብለው ይመልከቱ እነሆ አማላጃችን ኢየሱስ ህያው ሆኖ ይኖራል። እግዚአብሔር የተወደደውን ልጁን ስለሰጠ ያመስግኑት፡፡ ደግሞም የእርሱ መሞት በእርስዎ ሕይወት ዋጋ እንዳያጣ ይጸልዩ። መንፈስ ቅዱስ ዛሬውኑ ግብዣውን ያቀርብልዎታል፤ በሙሉ ልብዎ ወደ ኢየሱስ ይምጡና በረከቱን ይውሰዱ።

የተስፋ ቃሎቹን ሲያነቡ እነዚህ ቃላት ሊገለጽ በማይቻል ፍቅርና ርኅራኄ እንደተሞሉ ያስታውሱ፡፡ ይህ ሊነገር በማይቻል ፍቅር የተሞላው ግዙፉ አምላካዊ ልብ፤ ስፍር ቁጥር በሌለው ርኅራኄ ኃጢአተኛውን ወደ ራሱ ይስባል «በደሙ በተደረገ ቤዛነት የኃጢአትን ይቅርታ አገኘን»

(ኤፌ. 1፡7)።አዎ እግዚአብሔር ረዳትዎ መሆኑን ብቻ ይመኑ። እርሱ አምላካዊውን ግብረገባዊ አምሳል በሰብዓዊው ፍጡር ውስጥ ሊያኖር ይሻል። ኃጢአትዎን በመናዘዝና በንስሓ ወደ እርሱ ሲመጡ፤ በምህረትና በይቅርታ ይቀርቦታል።

## ምዕራፍ 7 - የደቀመዝሙርነት መፈተኛ

ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፋል እነሆ፣ ሁሉም አዲስ ሆኗል።» (2ኛ ቆሮ. 5:17)

አንድ ሰው የተለወጠበትን ትክክለኛ ጊዜ ወይም ቦታ ወይም መለወጡ ሂደት ውስጥ የነበሩ አጠቃላይ ሁናቴዎችን አያይዞ አንድ በአንድ መናገር አይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ መናገር አልቻለም ማለት አለመለወጡን ያሳያል ማለት አይደለም። ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ቁጥር 8 ላይ እንዲህ ብሎት ነበር «ንፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፣ድምጹንም ትሰማለህ፣ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉም እንዲሁ ነው፡፡» ንፋስ

በዓይን አይታይም፤ ይሁን እንጂ ንፋሱ ያስከተለው ውጤት ይታያል፣ ይሰማል። ልክ እንደ ንፋሱ የእግዚአብሔር መንፈስም በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚሠራው ሥራ በጉልህ ከመታየቱና ከመሰማቱ ውጭ መንፈሱ በዓይን አይታይም:: ያ የሰው ዓይን የማያየው ውስጣችንን ዳግም የሚያድሰው ኃይል በነፍሳችን ውስጥ አዲስ ሕይወትን ይዘራል፤ በእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን አዲስ ማንነትን ይፈጥራል። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ፀጥ ያለና ሲሠራ የማይታይ ቢሆንም ውጤቱ ግን ይታያል። ልባችን እግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ከታደሰና ከተለወጠ፤ ሕይወታችን እውነትን ይመሰክራል። በራሳችን ልባችንን መለወጥም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ራሳችንን ማስማማት አንችልም። በመሆኑም በራሳችንም ሆነ በመልካም ሥራችን ላይ ሙሉ ለሙሉ

መታመናችንን ስናቆም፤ ያኔ የእግዚአብሔር ጸጋ በውስጣችን ማደሩን ህይወታችን ይገልጻል። ይህን ተከትሎ በባህሪያችንና በልማዳዊ ድርጊቶቻችን ለውጥ መስተዋል ይጀምራል። በእነዚህ በሁለት የተለያዩ ነገሮች መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ ስለሚሆን በቀድሞው ሁናቴና በአሁኑ መሃል ያለው ልዩነት ምን እንደ ሆነ ለይቶ ለማወቅና ለመወሰን ይቻላል።ባህርይ የሚገለጸው አልፎ አልፎ በሚደረጉ ጥሩ ወይም መጥፎ ሥራዎች ሳይሆን አዘውትረው በሚነገሩ ቃላትና ድርጊቶች ነው።

እርግጥ ነው፤ ያለ ክርስቶስ ለዋጭ ኃይል ውጫዊ የባህርይ መልካምነት ሊኖር እንደሚችል አይካድም። በሌሎች ለመታየትና ለመወደስ ያለን ፍላጎት የተስተካከለ ሕይወት የምንለውን

እንድንቀዳጅ ሊያተጋን ይችላል። ለራሳችን ያለን አክብሮት የክፋት መገለጫ እንዳንሆን ሊያግዘን ይችል ይሆናል።ምናልባትም እራስ ወዳድ ልብ ለሌሎች መልካምን ነገር ሊያደርግ ይችል ይሆናል። ታዲያ ከማን ወገን እንደሆንን የሚወሰነው በምን መንገድ ነው? አዕምሯችንን የተቆጣጠረው ማን ነው? ሃሳባችን ከማን ጋር ነው? ማውራት ደስ የሚለን ስለማን ነው? የሞቀ ፍቅራችንን እና ከፍተኛውን አቅማችንን ለማን እያዋልነው ነው? የክርስቶስ ከሆንን ሃሳባችን ሁሉ ከእርሱ ጋር ነው።ጣፋጭ አስተሳሰባችን ሁሉ ስለ እርሱ ነው። እንዲሁም እኛ ያለንንና የእኛ የሆነውን ነገር ሁሉ ለእርሱ ብቻ እንቀድሳለን። እርሱን ለመምሰል፣መንፈሱን ለመተንፈስና ፈቃዱን ለማድረግ በሁሉም ነገራችን እርሱን ለማስደሰት እንናፍቃለን።

በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት የሆኑ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ያፈራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በገላትያ ምዕራፍ 5 ቁጥር 22 እና 23 ላይ ስለመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሲናገር «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ሰላም፣ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ እራስን መግዛት ነው»ይላል። እነዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት የሆኑ ሰዎች በቀድሞው የሥጋ ፍላጎታቸው መነዳት ያቆሙና በእግዚአብሔር ልጅ በሚገኝ እምነት ምክንያት የእርሱን ዱካ ይከተላሉ፣ የእርሱን ባህሪ ያንፀባርቃሉ፤ እርሱ ንፁህ እንደሆነ እራሳቸውን ያጠራሉ። ቀድሞ ይጠሏቸው የነበሩ ነገሮችን አሁን ይወዳሉ፤ ቀድሞ ይወዷቸው የነበሩ ነገሮችን አሁን ይጠላሉ።በራሳቸው ብቻ የሚታመኑ ልበ ደንዳኖች የነበሩ ትሁትና የተሰበረ ልብ

ባለቤት ይሆናሉ:: ግብዝነትና ልታይ ባይነት በእውነተኛነት እና በጭምትነት ይተካል። የመጠጥ ሱሰኛው ከነበረበት የመጠጥ ሱስ ይላቀቃል፣ አባካኞች ከማባከን ይታቀባሉ። የዓለም የግብዝነት ልማዶች እና ፋሽኖች ወልቀው ይጣላሉ። ክርስቲያን «ውጫዊ ጌጥን» መፈለግ በማቆም «ነገር ግን . . .የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው» ይሆን ዘንድ (1ኛ ጴጥ. 3:3-4) ይፈልጋል።

በሕይወት ላይ የሚታይ ለውጥን የማያመጣ ንስሃ እውነተኛ ንስሃ አይደለም። አንድ ሰው ቃል ኪዳኑን ካፀና፣ ዘርፎ የነበረውን ሲመልስ፣ኃጢአቱን ከተናዘዘ እንዲሁም እግዚአብሔርንና በአጠገቡ ያሉ ሰዎችን ከወደደ ይህ ኃጢአተኛ የነበረ ሰው ከሞት

ወደ ሕይወት መሸጋገሩን እርግጠኛ ሊሆን ይችላል።

በደለኞችና በኃጢአት የረከስን መሆናችንን አምነን ወደ ክርስቶስ በመቅረብ የፀጋ ምህረቱ ተቋዳሾች ስንሆን ፍቅር ከልባችን ይፈልቃል። የክርስቶስ ቀንበር ቀላል ከመሆኑ የተነሳ አንድ ሰው በእርሱ ሲሆን ሸክሙ ሁሉ ይቀለዋል። በጨለማ የተዋጠ ይመስል የነበረው መንገድ በፅድቅ ብርሃን ወገግታ ፍንትው ብሎ ይበራል።

የክርስቶስ የአፍቃሪነት ባሕርይ በተከታዮቹ ላይም ይታያል። የእርሱ ደስታ የእግዚአብሔር አብን ፈቃድ ማድረግ ነበር። የአዳኛችንን ሕይወት የተቆጣጠረው ኃይል የአብ ፍቅርና ለአብ ክብር ማምጣት ነበር። የክርስቶስ ሥራዎች ሁሉ ያማሩና የከበሩ

የሆኑት በፍቅር ስለተሠሩ ነው፡፡እግዚአብሔር ፍቅር ነው ፤ ፍቅርም ከእግዚአብሔር ነው፡፡ በንስሓ ያልታደሰ ልብ ንፁሕ ፍቅር ሊያፈልቅ አይችልም። ይህ ንፁሕ ፍቅር ሊገኝ የሚችለው ኢየሱስ ከነገሠበት ልብ ብቻ ነው፡፡ «አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንዋደዳለን።»(1ኛ ዮሐ 4፡19)። ልባችን በመለኮታዊ ፀጋ ከታደሰ፤ የድርጊቶች ሁሉ መሠረት የሆነው ፍቅር ባህርያችንን ይለውጣል፤ አስተሳሰባችንን ይመራል፤ምኞታችንን ይቆጣጠራል፤ ጥላቻችንን ያስወግዳል፤ መንፈሳችንን ይቀድሳል።ይህንን ፍቅር ዘወትር ስንለማመደው፤ ሕይወታችን ይጣፍጣል እንዲሁም በአካባቢያችን ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ እናሳድራለን።

የእግዚአብሔር ልጆች በተለይም ጌታን በቅርቡ የግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉ ሊርቋቸው የሚገቡ ሁለት ስህተቶች አሉ፦ የመጀመሪያው እና ከዚህ በፊት የጠቀስነው «በራሳችን መልካም ስራና ተግባር ከእግዚአብሔር ጋር መስማማት እንችላለን» የሚለው እምነት ነው። ይሁን እንጂ፣ በራሱ ጥረት ሕግን በመጠበቅ ቅዱስ ለመሆን የሚጥር ማንኛውም ሰው የማይቻል ነገር እየሞከረ ነው:: ምክንያቱም አንድ ሰው ከክርስቶስ ውጪ የሚያደርገው ነገር ሁሉ በእራስ ወዳድነትና በኃጢአት በተበከለ ማንነት የሚያደርገው ነው:: ምክንያቱም ቅዱስ የሚያደርገን በእምነት የምንቀበለው የክርስቶስ ፀጋ ብቻ ነውና።

ከዚህ ተቀራኒውና ቀላል የማይባለው አደገኛ ስህተት ደግሞ የክርስቶስ ጸጋ ተካፋዮች

የምንሆነው በእምነት በመሆኑና የእኛ መልካም ሥራዎች ከመዳናችን ጋር ምንም ግንኙነት ስለሌላቸው ክርስቶስ ሰዎችን የእግዚአብሔርን ሕግ ከመጠበቅ ነጻ አውጥቶአቸዋል» የሚለው እምነት ነው፡፡

ድነት በእምነት ብቻ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ስለሆነ፣ በመታዘዛችን ብዛት ልናገኘው አንችልም።

እዚህም ጋር አብሮ መታሰብ ያለበት ነገር ታዛዥነት ማለት ዝም ብሎ ሕጉን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የፍቅር አገልግሎት መሆኑን ነው። የእግዚአብሔር ሕግ የራሱ የእግዚአብሔር፣ የማንነቱ መገለጫ ነው፤ ሕጉ የፍቅርን ባሕርይ ያቀፈ ከመሆኑ የተነሳ በሰማይና በምድር የመንግሥቱ መሠረት ነው፡፡ ሕይወታችን በእግዚአብሔር አምሳል

ከተለወጠ፤መለኮታዊው ፍቅርም በልባችን ውስጥ ከሰረጸ እግዚአብሔርን ሕግ ተግባራዊ እናደርጋለን። የፍቅር መርሆ በልባችን ውስጥ ሲሰርጽ እኛም የፈጠረንን አምላክ አምሳል ስንይዝ «ሕጌን በልቦናቸው አኖራለሁ በልባቸውም የምንቀበለው እጽፈዋለሁ. . .» (ዕብ. 10፡16) የሚለው የአዲሱ ኪዳን ተስፋ ቃል ይፈጸማል። ሕግም በልባችን ውስጥ ሲጻፍ ሕይወታችን በእርሱ ይመራል። በፍቅር እና ታማኝ አገልግሎት የተመሰረተው ታዛዥነት እውነተኛ የደቀ መዝሙርነት ምልክት ነው:: በዚህ ምክንያት ነው መጽሐፍ ቅዱስ «ትዕዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና» (1ኛ ዮሐ 5፡3)። «(የእግዚአብሔርን) አውቄዋለሁ የሚል ትዕዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም።»(1ኛ ዮሐ 2:4) በማለት የሚነግረን። እምነት እኛን

ከታዛዥነት ነፃ ከማውጣት ይልቅ የክርስቶስ ጸጋ ተካፋይ እንድንሆንና እንድንታዘዝ የሚያደርገን ያው እምነት ብቻ ነው።

ድነት በእምነት ብቻ የምንቀበለው የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ስለሆነ፣ በመታዘዛችን ብዛት ልናገኘው አንችልም:: ነገር ግን መታዘዝ የእምነት ፍሬ ነው:: «እርሱም ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደተገለጠ ታውቃላችሁ፣ በእርሱም ኃጢአት የለም። በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውምም» (ዮሐ. 3:5-6። እዚህ ላይ ነው እውነተኛው ፈተና ያለው። በክርስቶስ የምንኖር ከሆነ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችን ካለ፤ የእኛ ስሜት፣ አስተሳሰብ፣ ዓላማና ድርጊት ሁሉ በእግዚአብሔር ሕግ ውስጥ እንደተጠቀሰው

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ይጣጣማል። «ልጆች ሆይ፡ ማንም አያስታችሁ፤እርሱም ፃድቅ እንደሆነ ፅድቅን የሚያደርግ ፃድቅ ነው።› (1ኛ ዮሐ. 3:7)። «ጽድቅ» የሚለው ቃል የሚመዘነው በእግዚአብሔር ቅዱስ ሕግ ነው:: ይህም ሕግ በሲና ተራራ በተሰጡት አስር ሕጎች ተገልጾአል።

«በክርስቶስ ማመን ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ነፃ ያወጣል» የሚለው አስተሳሰብ «እምነት» ሳይሆን፣ እምነት የሚመስል ስህተት ነው። በርግጥ «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና።» ይላል (ኤፌ.2፡8)። ነገር ግን «እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።» (ያዕ. 2:17) ይላል።ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ለራሱ እንዲህ ብሎ ነበር፡- «አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ» (መዝ.

40፡8)። ተመልሶ ወደ አባቱ ቀኝ ከማረጉም በፊት «እኔ የአባቴን ትዕዛዝ እንደጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፣ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ።» (ዮሐ. 15:10) በማለት ተናግሮአል። እንደዚሁ መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ዮሐ. 3:6 እና በ1ኛ ጴጥ. 2:21 «በእርሱ የሚኖር ኃጢአትን አያደርግም ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውምም» «ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን ልትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለእናንተ መከራን ተቀብሏልና» ይላል። «ምክንያቱም ክርስቶስ ስለ እናንተ መከራን የተቀበለው የእርሱን ፈለግ እንድትከተሉ ምሳሌን ሊተውላችሁ ነው» (1ኛ ጴጥ. 2:21)።

ይህ የዘለዓለም ሕይወትን ለማግኘት የሚጠየቀው መስፈርት አሁንም ሆነ ጥንት

ወላጆቻችን በገነት ውስጥ በኃጢአት ከመውደቃቸው በፊት ተመሳሳይ ነው:: ይኼውም ለእግዚአብሔር ሕግ በፍጽምና መገዛትና የጽድቅ ህይወትን መኖር ነው። የዘለዓለም ሕይወት ከእነዚህ ውጪ የሚሰጥ ቢሆን ኖሮ የመላው ፍጥረት ደስታ አደጋ ላይ በወደቀ ነበር። ይህ ቢሆን ኑሮ፤የኃጢአት መንገድ ከነግሳንግሱና ሰቆቃው፣ ዋይታውና ምሬቱ ጋር ለዘላለም በተከፈተ ነበር።

አዳም በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ለእግዚአብሔር ሕግ በመታዘዝ ፃድቅ ባሕርይን ማሳየት ይችል ነበር። ነገር ግን እርሱ ይህን ስላላደረገና ከእርሱም ውድቀት የተነሳ የእኛ ተፈጥሮ በኃጢአት ስለ ጎደፈ እራሳችንን ልናጸድቅ አልቻልንም:: ኃጢአተኞች ፣ ቅድስና የጎደለንና በኃጢአት የረከስን እንደመሆናችን፣ ቅዱሱን ሕግ

በፍጹምነት ልንታዘዘው አንችልም፡ የእግዚአብሔር ሕግ የሚጠይቀውን ለማሟላት የራሳችን የሆነ ጽድቅ ባይኖረንም ክርስቶስ ግን የማምለጫውን መንገድ አዘጋጀልን። እርሱ በኖረው ምድራዊ ህይወቱ እኛ በምናልፍበት ፈተናና መከራ ውስጥ አልፏል።ይሁንና ኃጢአት የሌለበትን ሕይወት ኖረ። ስለዚህም ስለኛ ሞቶ ኃጢአታችንን ለመውሰድ እራሱን በመስጠት ጽድቁን አወረሰን። እራሳችሁንለእርሱ ብትሰጡና እንደ አዳኛችሁ ብትቀበሉት የፈለገውን ያህል ኃጢአተኛ የነበራችሁ ቢመስላችሁም፤ ስለ ራሱ ሲል እንደ ጻድቅ ይቆጥራችኋል።የክርስቶስ ባሕርይ በእናንተ ምትክ ተቆጥሮ በእግዚአብሔር አብ ፊት ምንምኃጢአት እንዳልሠራ ሰው ሆናችሁ እንድትታዩ ያደርጋችኋል።

ከዚህ በተጨማሪም ክርስቶስ ልባችሁን ይቀይራል፤ በእምነትም በልባችሁ ውስጥ ይኖራል። ታዲያ ይህንን ከክርስቶስ ጋር ያለ ግንኙነት በእምነት እየጠበቃችሁ ፈቃዳችሁን ያለ ማቋረጥ ለእርሱ እየሰጣችሁ እስከኖራችሁ ድረስ እርሱም መልካም ፈቃዱን የመፈለግ እና የማድረግን ነገር በእናንተ ውስጥ ይሠራል። ስለዚህ እናንተም «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል:: አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝ እና ስለእኔ እራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።» (ገላ. 2:20) ትላላችሁ። ስለዚህ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ «በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና» (ማቴ. 10:20) ብሏቸዋል። በእናንተ

በሚሠራው ክርስቶስ ምክንያት የእርሱን አይነት መንፈስ ትገልጻላችሁ፤እንደ እርሱም መልካም ሥራን ታደርጋላችሁ። ሥራዎቹም የፅድቅና የመታዘዝ ናቸው።

ስለዚህ የምንኩራራበት የራሳችን የሆነ ምንም ነገር የለንም:: እራሳችንን ከፍ አድርገን የምናይበት ምንም መሠረት የለንም:: ብቸኛው የተስፋችን መሠረት ለእኛ የተቆጠረልን የክርስቶስ ጽድቅና በእኛ ውስጥ እንዲሁም በእኛ በኩል በመሥራት ለውጥ የሚያመጣው የእርሱ መንፈስ ብቻ ነው::ስለ እምነት በምንናገርበት ጊዜ መዘንጋት የሌለብን ነገር አለ። ከእውነተኛው እምነት ፍጹም የተለየ የእምነት አይነት አለ። የእግዚአብሔር ሕልውናና ኃያልነት እንዲሁም የቃሉ እውነትነት ሰይጣንና ጭፍሮቹ እንኳ በልባቸው ሊክዱት

የማይችሉት ተጨባጭ እውነታ ነው፡፡
ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ በያዕ. 2:19 ላይ፡-
«እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ መልካም ታደርጋለህ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።» ይላል።
ስለዚህ ይህ አይነት እምነት እውነተኛ እምነት አይደለም። እውነተኛ እምነት በእግዚአብሔር ቃል ማመን ብቻ ሳይሆን፤ ፈቃዳችንን ለእርሱ ማስገዛትንም ይጨምራል። አንድ ሰው ልቡን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሲያስገዛ፤ በዚያ ሰው ልብ ውስጥ ነፍስን የሚያነጻ በፍቅር የሚሠራ እምነት አለ ማለት ነው።

በዚህም እምነት አማካኝነት ነው ልባችን በእግዚአብሔር አምሳል የሚታደሰው፡፡ ያልታደሰ ልብ ለቅዱሱ የእግዚአብሔር ሕግ በተግባርም ሆነ በፍላጎት ሊገዛ አይችልም።

የተለወጠ ልብ ያለው ሰው ግን በቅዱሱ የእግዚአብሔር ሕግ በመደሰት ከመዝሙረኛው ጋር፡- «አቤቱ፣ ሕግህን እንደ ምን እጅግ ወደድሁ ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው።» (መዝ. 119:97)፣«እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ» የሕግ ፅድቅ ይፈጸማል በማለት ይናገራል (ሮሜ 8:3)።

የክርስቶስን ይቅር ባይ ፍቅር የሚያውቁና በእርግጥም የእግዚአብሔር ልጅ መሆን የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። ይሁንና እነዚህ ሰዎች ባሕርያቸው ፍጽምና የጎደለው፣ ህይወታቸውም እንከን ያለው መሆኑን ስለሚረዱ ልባቸው በመንፈስ ቅዱስ መታደሱን ይጠራጠራሉ:: እነዚህን ሰዎች «ተስፋ በመቁረጥ ወደ ኋላ አታፈግፍጉ!» ማለት እፈልጋለሁ። እኛ በተደጋጋሚ

በኢየሱስ እግር ስር በመውደቅ ስለ ጉድለታችንና ኃጢአታችን ማንባት ቢኖርብንም ተስፋ መቁረጥ ግን አይገባንም። ምንም እንኳ በጠላት ብንሸነፍም፤ በእግዚአብሔር የተረሳን፣ የተጣልን እና የተተውን አይደለንም።እርሱ ከቶ አይተወንም። ክርስቶስ በአብ ቀኝ ተቀምጦ ስለ እኛ ይማልድልናል። የተወደደው ሐዋርያ ዮሐንስ በ1ኛ ዮሐ. ምዕ. 2 ቁጥር 1 «ልጆቼ ሆይ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህንን ጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡» ብሏል። «አብ እራሱ ወድዷችኋል።» ዮሐ. 16:27 ያለውን የክርስቶስን ቃል አትርሱ፡፡ እርሱ በእናንተ ውስጥ ተሃድሶ በማድረግ በውስጣችሁ የሚንጸባረቀውን የራሱን ንጽህናና ቅዱስነት ለማየት ይመኛል።እናንተም ይህ እንዲሆን

የምትፈልጉ እና እራሳችሁን ለእርሱ የምትሰጡ ከሆነ በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እርሱ እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ ይፈጽመዋል። በትጋት ጸልዩ፤ በሙላትም እመኑ። በእራስ መታመናችንን በመተው በዋጀን ኃይል እንታመን። ይህን ስናደርግ በገጽታችን ላይ ጤነኛ ስሜት እንዲነበብ ላደረገ ለእርሱ ምስጋና እንሰዋለን።

ወደ ኢየሱስ የበለጠ በተጠጋችሁ ቁጥር እይታችሁ እየበራ ስለሚመጣ ራሳችሁን ከእርሱ ፍጹም ባሕርይ ጋር ስታነጻጽሩት የእናንተን ኃጢአተኝነት በሰፊውና በግልጽ ታያላችሁ። ይህ ሲሆን የበለጠ ኃጢአተኛ መሆናችሁን በራሳችሁ ዓይኖች ትመለከታላችሁ። ይህም የሰይጣን ማታለያዎች ኃይል የማጣታቸው ምስክር

ሲሆን በእናንተ ውስጥ ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ስራውን መጀመሩን ያሳያል።

የራሱን ኃጢአተኛነት በግልጽ ባልተገነዘበ ልብ ውስጥ ጥልቅ የሆነው የኢየሱስ ፍቅር ሊኖር አይችልም። በክርስቶስ ፀጋ የተለወጠ ነፍስ የክርስቶስን መለኮታዊ ባሕርይ ያደንቃል። የራሳችንን የባህሪ መበላሸት ማየት ከተሳነን የክርስቶስን ውበትና ልዕቀት በሚገባ አላስተዋልንም ማለት ነው።

በእራሳችን መመካታችንን ባሳነስን መጠን ወሰን በሌለው የአዳኛችን ንጽሕናና ውበት ላይ መመካታችን ይጨምራል። ኃጢአተኛነታችንን ማመናችን ይቅር ሊል ወደሚችለው ወደ እርሱ እንድናይ ይገፋፋናል።ረዳተ ቢስነታችንን አስተውለን ወደ ክርስቶስ ስንቀርብ፣ እርሱ ራሱን

ከነሙሉ ኃይሉ ይገልጥልናል። የጎዶሎነት ስሜታችን ወደ እግዚአብሔርና ወደ እግዚአብሔር ቃል አብዝቶ ባስጠጋን ቁጥር ስለ እርሱ ባሕርይ ላቅ ያለ አመለካከት ይኖረናል። የእርሱንም አምሳል በተሻለ ሙላት እናንጸባርቃለን።

## ምዕራፍ 8 - ወደክርስቶስ ሙላት ማደግ

በእግዚአብሔር ልጆች የምንሆንበትን የልብ ለውጥ መጽሐፍ ቅዱስ ከመወለድ ጋር ያመሳስለዋል። እንዲሁም በገበሬ ከተዘራና ከሚያቆጠቁጥ ጥሩ ዘር ጋር ያነጻጽረዋል። ከዚህ አኳያ፣ ወደ ክርስቶስ የተለወጡ ሁሉ «አዲስ እንደተወለዱ ህፃናት» በክርስቶስ ሙሉ ሰው ወደ መሆን «ማደግ» እንደሚያስፈልጋቸው ወይም በእርሻ እንደተዘራ መልካም ዘር፣ ማደግና ፍሬ ማፍራት እንደሚኖርባቸው ተጽፎአል (1ኛ ጴጥ. 2:2፣ ኤፌ. 4:15)። ኢሳይያስም «እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የፅድቅ ዛፎች ይባላሉ» ይለናል (ኢሳ. 61፡ 3)። የመንፈሳዊውን ሕይወት ምስጢራዊ እውነቶች በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እንችል

ዘንድ እነዚህ ምሳሌዎች ከተፈጥሮ ተወስደዋል::

የሰው ጥበብ እና ክህሎት ሁሉ ትንሿ የተባለችን ሕይወት ማፍራት አይችልም። እፅዋት ወይም እንስሳት በሕይወት የሚኖሩት እግዚአብሔር ራሱ በሚሰጣቸው ሕይወት ብቻ ነው። ስለዚህ በሰዎች ልብ ውስጥ መንፈሳዊ ሕይወት የሚወለደው ከእግዚአብሔር በሚገኝ ሕይወት ብቻ ነው:: መንፈሳዊ ሕይወትም እንደዚሁ በሰው ልጆች ልብ ውስጥ የሚወለደው ከእግዚአብሔር በተገኘ ሕይወት አማካይነት ብቻ ነው:: አንድ ሰው «ከላይ ካልተወለደ በስተቀር ክርስቶስ ሊሰጠን የመጣው ሕይወት ተካፋይ ሊሆን አይችልም ዮሐ. 3:3)። እድገትንም በተመለከተ እንደዚያው ነው። እንቡጥን ወደ ማበብ ፣ አበባንም ወደ

ፍሬነት የሚለውጠው እግዚአብሔር ነው፡፡ ዘር የሚያድገው በእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ «ምድሪቱ አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍፁም ሰብል ታፈራለች» (ማር. 4:28)። ነብዩ ሆሴዕ ስለ እስራኤል ሲናገር «እንደ አበባ ያብባል፤» «እንደ ወይንም አረግ ያብባሉ፤ መታሰቢያውም እንደ ሊባኖስ ወይን ጠጅ ይሆናል።» ይላል (ሆሴዕ 14፡5-7)። እንደዚሁም ኢየሱስ «አበቦችን እንዴት እንዲያድጉ ተመልከቱ፤» በማለት ይናገረናል (ሉቃ.12:27)። ዕፅዋትና አበቦች በራሳቸው ክብካቤ ወይም ጭንቀት ወይም ጥረት አያድጉም፡፡ እነርሱ የሚያድጉት ለሕይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን በሙሉ ከእግዚአብሔር በመቀበል ነው። አንድ ህፃን ልጅ የተቻለውን ያህል እንኳን ቢጥር በቁመቱ ላይ ምንም ሊጨምር እንደማይችል ሁሉ እኛም

በራሳችን ጥረት መንፈሳዊ ዕድገትን ልናመጣ ከቶ አንችልም። እፅዋት እና ህፃናት ለሕይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን አየር፣ የፀሐይ ብርሃንና ምግብ ስለሚያገኙ ነው ዕድገትን የሚያሳዩት:: ተፈጥሮ ለእንስሳት እና ለእፅዋት የምትለግሳቸውን እነዚህን ነገሮች ክርስቶስ ደግሞ በእርሱ ለሚታመኑት ይሰጣቸዋል። እርሱ ለእነርሱ «የዘለዓለም ብርሃን» «ፀሐይ እና ጋሻ» ነው (ኢሳ. 60፡19፤ መዝ. 84፡11)። እርሱ «የእስራኤል ጠል» ነው:: «በግጦሽ ሳር ላይ እንደዝናብ ይመጣል» (ሆሴ. 14፡5፤ መዝ. 72:6)። እርሱ የሕይወት ውሃ ነው:: «የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነው» ዮሐ. 6፡33)።

ተወዳዳሪ በሌለው በልጁ ስጦታ፣ እግዚአብሔር አለምን ልክ እንደተከበበችበት

አየር በጸጋው ከቧታል:: ይህንን ሕይወት ሰጪ አየር ለመተንፈስ ፈቃደኞች የሆኑ ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን ሕይወት ይኖራሉ፤ ወደ ሙሉ ሰውነት ደረጃም ያድጋሉ። ውበትና መልካም አቋም እንዲኖረው አበባ የብርሃን ጨረርን ለማግኘት ወደ ፀሐይ እንደሚያጋድል እኛም የሰማይ ብርሃን በእኛ ላይ እንዲያበራና ባሕርያችን ክርስቶስን ወደ መምሰል እንዲያድግ ወደ ጽድቅ ጸሐይ ፊታችንን ልናዞር ይገባል።

ኢየሱስ በዮሐንስ 15:4-5 ላይ ‹በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፣ እንዲሁም ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም:: እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለእኔ ምንም ልታደርጉ

አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፣እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።» በማለት ተመሳሳይ ነገርን አስተምሯል። ቅርንጫፍ ለማደግ እና ፍሬ ለማፍራት በግንዱ ላይ ጥገኛ እንደሚሆን ሁሉ እናንተ የቅድስና ሕይወት እንድትኖሩ በክርስቶስ ላይ ጥገኞች ናችሁ፡፡ከእርሱ ተለይታችሁ ሕይወት አይኖራችሁም። ያለ እርሱ ፈተናን ለመቋቋም ወይም በጸጋ እና በቅድስና ለማደግ ብቃት አይኖራችሁም። በእርሱ ከኖራችሁ ታብባላችሁ፡፡ ሕይወታችሁ ከእርሱ ጋር የተጣበቀ ከሆነ አትደርቁም፤ ፍሬ አልባም አትሆኑም። በወንዝ ዳር እንደተተከለ ዛፍ ሁልጊዜ ለምለም ትሆናላችሁ።

ብዙዎች በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ የሚያስፈልገውን ሥራ ቢያንስ የተወሰነውን ክፍል ብቻቸውን የመሥራት ሃሳብ አላቸው፡፡

በርግጥ ለኃጢአታቸው ይቅርታን ለማግኘት ክርስቶስን ታምነው የነበረ ቢሆንም፣ መንፈሳዊ ሕይወትን ለመኖር ግን በራሳቸው ጥረት ላይ ይደገፋሉ። ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ያለው ጥረት የማይሳካ ነው:: ኢየሱስ «ከእኔ በቀር ምንም ልታደርጉ አትችሉም» ብሎናል። የእኛ በፀጋ ማደግ፣ ደስታና ጠቃሚነታችን ሁሉ ከክርስቶስ ጋር በሚኖረን ሕብረት ላይ የተመሰረተ ነው:: በፀጋ የምናድገው ከእርሱ ጋር ዕለት ተዕለትና በየሰዓቱ ስንኖር እንዲሁም በእርሱ ውስጥ ስንሆን ነው:: እርሱ የእምነታችን ጀማሪ ብቻ ሳይሆን ፈጻሚም ነው። ክርስቶስ ፊተኛውና ኋለኛው እንዲሁም ሁሉ በሁሉ ነው:: እርሱ በጅማሬ እና በፍፃሜያችን ላይ ብቻ ሳይሆን በሕይወታችን በእያንዳንዱ ርምጃ ላይ አብሮን ሊሆን ይገባል። ዳዊት በመዝሙር 16፡8 ላይ «ሁል ጊዜ

እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ በቀኜ ነውና አልታወክም።» ብሏል።

«በክርስቶስ እንዴት እኖራለሁ?» ብላችሁ ጠይቃችኋል? በእርሱ የምትኖሩት ልክ መጀመሪያ እርሱን ስትቀበሉት በነበረበት ሁኔታ ነው። «እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ።» «ፃድቅ ግን በእምነት ይኖራል» (ቆላ. 2፥6፤ ዕብ 10:38)። ሙሉ በሙሉ የእርሱ ለመሆን፣ እርሱን ለማገልገልና ለመታዘዝ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ሰጥታችኋል፤ ክርስቶስንም እንደ ግል አዳኛችሁ ተቀብላችሁታል:: በራሳችሁ ኃጢያታችሁን ልታስተሰርዩና ልባችሁንም ልትለውጡ አትችሉም። በራሱ የሚታመን አዕምሮ የብርታትና የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከክርስቶስ የራቀ ነው። ነገር ግን

ራሳችሁን ለእግዚአብሔር በመስጠት
እነዚህን ሁሉ ነገሮች ስለ ክርስቶስ ሲል እርሱ
እንዳደረገላችሁ አምናችኋል። በእምነት
የክርስቶስ ሆናችኋል:: እንደዚሁም
በመስጠትና በመቀበል ላይ በተገነባ እምነት
በእርሱ ውስጥ ታድጋላችሁ:: እርሱን
በሁሉም መስፈርቱ ለመታዘዝ ልባችሁን ፣
በፊስ ፈቃዳችሁን፣
አገልግሎታችሁን፣እራሳችሁንም ባጠቃላይ
ሁለንተናችሁን ለእርሱ መስጠት አለባችሁ::
ከዚያም ክርስቶስ ጥንካሬያችሁ
እንዲሆን፣ጽድቃችሁና የዘላለም
ረድኤታችሁ እንዲሆንላችሁ፣ ለመታዘዝ
ኃይል እንዲሰጣችሁ እርሱን ከነሙሉ በረከቱ
በልባችሁ እንዲኖር መውሰድ አለባችሁ::

በማለዳ እራሳችሁን ለእግዚአብሔር ቀድሱ፤
ይህ የመጀመሪያ ሥራችሁ እንዲሆን

አድርጉ። ፀሎታችሁ «ኦ! ጌታ ሆይ ውሰደኝ፣
ሙሉ በሙሉ የራስህ አድርገኝ! እቅዶቼን
ሁሉ በእግርህ ስር አስቀምጣለሁ። ዛሬ
ለአገልግሎትህ ተጠቀምብኝ ። ከእኔ ጋር
ሁንና የማደርገውን ነገር ሁሉ በአንተ
እንዳደርገው እርዳኝ» የሚል ይሁን። ይህም
በየዕለቱ የምንለማመደው ፀሎት ይሁን።
በየማለዳው ለዚያን ቀን እራሳችሁን
ለእግዚአብሔር ቀድሳችሁ ስጡ፡፡ የእርሱ
ምሪት በሚያሳያችሁ መሰረት ወይ
እንዲከናወኑ አልያም እንዲከሽፉ
እቅዶቻችሁን ሁሉ ለእርሱ ስጡ። በዚህም
መሰረት ዕለት በዕለት ሕይወታችሁን
ለእግዚአብሔር እጆች
ትሰጣላችሁ፤ሕይወታችሁም ክርስቶስን ወደ
መምሰል እየተለወጠ ይሄዳል።

በክርስቶስ የሆነ ሕይወት የዕረፍት ሕይወት ነው። ምንም አይነት የፍንደቃ ስሜት ላይኖረን ይችላል፤ ነገር ግን በሰላም የተሞላ መታመን ይኖረናል። ተስፋችን በራሳችን ሳይሆን በክርስቶስ ነው:: የእኛ ድካም ከእርሱ ብርታት፣ አላዋቂነታችን ከእርሱ ጥበብ፣ ልፍስፍስነታችን ከእርሱ ዘለዓለማዊ ኃይል ጋር ተቆራኝቶአል። ስለዚህም መመልከትና አዕምሮአችን ማተኮር ያለበት በራሳችን ነገር ላይ ሳይሆን፣ ወደ ክርስቶስ ልንመለከት ይገባል። አዕምሮአችን የእርሱን ፍቅር፣ የባሕርይውን ውበትና ፍጽምና ያስብ። ነፍስ ልታሰላስለው የሚገባ ርእስ ቢኖር፣ የክርስቶስ ራሱን መካድ፣ትህትናው፣ ንጽሕናው፣ ቅድስናው እንደዚሁም ወደር የለሽ ፍቅሩ ሊሆኑ ይገባል። እርሱን በማፍቀር፣ የእርሱ ቅጂ በመሆን ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ በመደገፍ እርሱን ወደመምሰል ማደግ

አለባት። እርሱን ወደ መምሰል የምንለወጠው፣ እርሱን በመውደድ፣ ከእርሱ በመቅዳት፣ እንደዚሁም ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ በመደገፍ ነው::

ኢየሱስ «በእኔ ኑሩ» ብሏል፡እነዚህም ቃላት የያዙት የዕረፍት፣ የመረጋጋትና የመተማመን ሃሳብ ነው:: እንደገናም እርሱ «ወደ እኔ ኑ …እኔም አሳርፋችኋለሁ» (ማቴ. 11:28) ሲል ጋብዟል። የመዝሙረኛውም ቃል ይህንኑ ይገልፃል፡- «በእግዚአብሔር ፊት ፀጥ በል በትዕግስትም ተጠባበቀው» (መዝ. 37፡7)። ኢሳይያስም ይህን ሲያረጋግጥ፡- «በመመለስ እና በማረፍ ትድናላችሁ፤ በፀጥታ እና በመታመን ኃይል ይሆንላችኋል» (ኢሳ. 30፡15) አዳኛችን የሰጠን የዕረፍት ተስፋ ከአገልግሎት ጥሪ ጋር የተያያዘ ስለሆነ እጅና እግርን አጣጥፎ በመቀመጥ አይገኝም።

«ቀንበሬን ተሸከሙ ... ዕረፍት ታገኛላችሁ» (ማቴ 11:29)። በክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ያረፈ ልብ ክርስቶስን በሙሉ ልቡ እና በትጋት ያገለግለዋል።

በራሱ የሚተማመን አዕምሮ የብርታትና የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከክርስቶስ የራቀ ነው። በመሆኑም የሰይጣን የማያቋርጥ ጥረት፣ ትኩረታችንን ከአዳኛችን ላይ አንስቶ በሌላ ነገር ላይ በማድረግ፣ ነፍሳችን ከክርስቶስ ጋር ያላትን ግንኙነትና አንድነት ማደናቀፍ ነው:: ሰይጣን ወደ ዓለም ደስታ፣ የኑሮ ውጣ ውረድ፣ ጭንቀቱና ሃዘኑ እንዲሁም ወደ ሌሎች ሰዎች ስህተት ወይም ወደ እኛ ጥፋትና ፍጹም አለመሆን፣ እነዚህንና እነዚህን ወደ መሳሰሉት ነገሮች ትኩረታችንን ለመቀልበስ ይተጋል። በእርሱ ማታለያዎች መደናቀፍ የለብንም።

በእርምጃቸው ጥንቁቆች የሆኑና ለእግዚአብሔር ለመኖር ከልባቸው የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ። ይሁንና ሰይጣን ደግሞ በስህተቶቻቸውና በድክመታቸው ላይ ትኩረታቸውን ዘወትር እንዲያነጣጥሩና ከክርስቶስ እንዲለዩ በማድረግ ድል ሊነሳቸው ተስፋ ያደርጋል። ትኩረታችንን በእኛ በራሳችን ላይ ብቻ በማድረግ «እንድናለን ወይስ አንድንም?» በማለት በጭንቀትና በፍርሀት መዋጥ የለብንም። እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ነፍስን የብርታት ምንጭ ከሆነው ዘወር እንድትል ያደርጋል። ነፍሳችሁን የመጠበቅን አደራ ለእግዚአብሔር በመስጠት በእርሱ ታመኑ። ኢየሱስን አስቡ እርሱን ተጫወቱት፤ በራስ የመመካት ነገር እርሱን በመታመን ይተካ። ጥርጣሬን አስወግዱ፤ ፍርሀትን ሁሉ ደምስሱ፤ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር

«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆ ኘ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» (ገላ. 2:20) በሉ።በእግዚአብሔር እረፉ። እርሱ አደራ የሰጣችሁትን ነገር ሁሉ በብቃትመጠበቅ ይችላል። እራሳችሁን በእርሱ እጅ ላይ ብታኖሩት በእርሱብወደዳችሁ ከአሸናፊዎች በላይ አድርጎ ያቆማችኋል።

ክርስቶስ የሰውን ተፈጥሮ ለብሶ በመምጣቱ፤ በራሳችን ምርጫ ካልሆነ በስተቀር፤ የትኛውም ኃይል ሊበጥሰው በማይችል ጠንካራ የፍቅር ገመድ እራሱን ከእኛ ከሰብዓዊያን ጋር አጣምራል። ሰይጣን ደግሞ ያለማቋረጥ እኛን የሚማርክ ነገር በማቅረብ ይህንን ገመድ በራሳችን እንድንበጥስ፣ራሳችንንም ከክርስቶስ ለመለየት እንድመርጥ ለማድረግ

ይጥራል።ከክርስቶስ በስተቀር በላያችን ላይ ሌላ ገዢ እንዳንሸም ሁል ጊዜ ነቅተን መጠበቅ፣ መጋደል፣ እንዲሁም መጸለይ ይኖርብናል። ምክንያቱም የፈለግነውን የመምረጥ ነጻነቱ አለንና። ዓይናችንን በክርስቶስ ላይ ስንተክል፤እርሱም ከጥፋት ይጠብቀናል። ወደ ክርስቶስ እስከተመለከትን ድረስ ምንምአያሰጋንም:: ምንም ነገር ከእጁ ነጥቆ ሊወስደን አይችልም::

ያለማቋረጥእርሱን በመመልከት « መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ የእርሱን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን» (2ኛቆሮ. 3:18)።

የቀድሞዎቹ ደቀመዛሙርት ውዱን አዳኛቸውን የመሰሉበት መንገድ ይህ ነበር። እነዚያ ደቀመዛሙርት የኢየሱስን ቃል ሲሰሙ ጉድለታቸውን አስተዋሉ። ፈለጉት፤

አገኙት ከዚያም ተከተሉት:: እነዚያ ደቀመዛሙርት ከእርሱ ጋር አንድ ቤት ውስጥ ነበሩ፤ አንድ ላይ በልተዋል፤ በእልፍኝ ውስጥም በሜዳም ላይ አብረውት ነበሩ። እነርሱም እንደ ተማሪ ሆነው ከመምህራቸው ከኢየሱስ አንደበት በየዕለቱ የቅዱሱን እውነት ትምህርት ተማሩ። ደቀመዛሙርቱ «እንደ እኛ የሆነ ሰው» ነበሩ (ያዕ. 5:17)። እነርሱ ልክ እንደእኛ ከኃጢአት ጋር ትግል ውስጥ ነበሩ:: ቅዱስ ሕይወት ለመኖር ይችሉ ዘንድ የሚያስፈልጋቸውም ጸጋ ልክ ለእኛ እንደሚያስፈልገው አይነት ነበር።

የአዳኙን መልክ በተሻለ ሙላት ማንጸባረቅ ችሎ የነበረው ተወዳጁ ደቀመዝሙር ዮሐንስም እንኳን ቢሆን ያንን በፍቅር የተሞላ ባሕርይ በተፈጥሮ ያገኘው

አልነበረም። ዮሐንስ ግትር እና ለክብር የሚጓጓ ብቻ ሳይሆን በአደጋ ጊዜ ቁጡ እና ግልፍተኛም ነበር። የመለኮት ባህርይ በተገለጠለት ጊዜ ግን የእራሱን ጉድለት ተረዳ፤ ይህን ባስተዋለ ጊዜ ራሱን ዝቅ አደረገ።በእግዚአብሔር ልጅ የየዕለት ሕይወት ውስጥ ይገለፅ የነበረው ብርታት እና ትዕግስት፣ ኃይልና ርህራሄ፣ ግርማና ትህትና የዮሐንስን ነፍስ በአድናቆት እና በፍቅር ሞሉት። በራሱ ላይ የነበረው መመካት ለጌታው ባለው ፍፁም ፍቅር እስኪዋጥ ድረስ ልቡ ዕለት ዕለት ወደ ክርስቶስ ይጠጋ ነበር። የእርሱ በቁጣና በትምክህት የተሞላ ስሜት፣ መቅረፅ ለሚችለው ለክርስቶስ ኃይል ተሰጠ። ልቡ እንደገና መፍጠር በሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ታደሰ።የክርስቶስ የፍቅር ኃይል በውስጡ የባህሪ ለውጥን አመጣ። ይህ ከኢየሱስ ጋር

እውነተኛ ሕብረት የማድረግ ውጤት ነው። ክርስቶስ በልብ ውስጥ ሲኖር፣ መላ ተፈጥሮ ይቀየራል። የክርስቶስ መንፈስና ፍቅሩ ልብን አለስልሶ ነፍስን ይማርክና፣ አስተሳሰብንና ፍላጎትን ወደ እግዚአብሔር እና መንግስቱ ከፍ ከፍ ያደርጋል።

ክርስቶስ ወደ ላይ ሲያርግ የእርሱ የአብሮነት መንፈስ ግን ከተከታዮቹ ጋር ነበር። ከእነርሱ ጋር የተጓዘው እና የተነጋገረው፣አብሮአቸውየፀለየው፣ ለልባቸው ተስፋንና መጽናናትን የተናገረው አዳኙ ኢየሱስ የሰላም መልእክት በአንደበቱ ላይ እያለ ነበረ ወደ ላይ የተነጠቀው። ሊቀበሉት በመጡ የመላእክት ደመና ከመሸፈኑ በፊት እንዲህ የሚለው ድምጽ በጆሮአቸው አስተጋባ፡- «እነሆ እኔ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ

ጋር ነኝ» (ማቴ. 28:20)። ወደ ሰማይ ያረገው ሰብአዊውን ተፈጥሮ እንደለበሰ ነው:: በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የሚቀርበው እርሱ፣ አሁንም ወዳጃቸውና አዳኛቸው እንደሆነ፣ ርህራኄው እንደማይለወጥ፣ ኃጢአት ከሚሰቃየው ሰብአዊ ቤተሰብ ጋር ራሱን እንዳቆራኘ ያውቃሉ። የገዛ ራሱን ክቡር ደም ብቁነት፣ የቆሰሉ እጆችና እግሮቹን፣ ለተቤዣቸው የከፈለውን ዋጋ በማስታወስ በእግዚአብሔር ፊት ያሳያል። ደቀዛሙርቱ እርሱ ወደ ሰማይ ያረገው ቦታ ሊያዘጋጅላቸው እንደሆነና ዳግመኛም እርሱ ወዳለበት ሊወስዳቸው እንደሚመጣም ያውቁ ነበር።

ከእርገቱ በኋላ አንድ ላይ ሲሰበሰቡ፣ በኢየሱስ ስም ጥያቄያቸውን ለአብ ሊያቀርቡ ጓጉተው ነበር። አክብሮትን በተሞላ አግራሞት ውስጥ

ሆነው በጸሎት እንዲህ የሚሉትን የጌታን የተስፋ ቃላት ይደጋግሙ ነበር፡-«እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ

ክርስቶስ በልብ ውስጥ ሲኖር፣ መላ ተፈጥሮ ይቀየራል።

ይሰጣችኋል።እስከአሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበላላችሁ» (ዮሐ.16:23-24)። እንዲህም በማለት የእምነት እጃቸውን ከፍ ከፍ አደረጉ፡-«የሞተው፣ ይልቁንም ከሙታን

ይሰጣችኋል።እስከአሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበላላችሁ» (ዮሐ.16:23-24)። እንዲህም በማለት የእምነት እጃቸውን ከፍ ከፍ አደረጉ፡-«የሞተው፣ ይልቁንም ከሙታን

የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፣ደግሞ ስለእኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» (ሮሜ 8:34)።ጴንጤቆስጤም፣ ክርስቶስ እራሱ «በእናንተ ይኖራል» ያለው እና «እኔ ብሄድ ይሻላችኋል፣ እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ።» ያለውን አጽናኙን ይዞላቸው መጣ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ክርስቶስ ያለ ማቋረጥ በመንፈሱ አማካይነት በልጆቹ ውስጥ ይኖራል። ከእርሱም ጋር አሁን ያገኙት ሕብረት፣ እርሱ በአካል ከእነርሱ ጋር ይኖርበት ከነበረው ጊዜ ይልቅ የቀረበ ነበር። በውስጣቸው ያደረው የክርስቶስ ብርሃን፣ ፍቅርና ኃይል በእነርሱ ላይ ይንጸባረቅ ነበርና የተመለከቷቸው ሰዎች «መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደሆኑ አስተውለው አደነቁ» (የሐዋ. 4፡13)።

ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ሆኖላቸው የነበረውን ሁሉ፣ ዛሬም ላሉትልጆቹ እንደዚያው ሊሆንላቸው ይፈልጋል። በመጨረሻው ጸሎቱ ላይ፣ ከእርሱ ጋር ከተሰበሰቡት ጥቂት ደቀመዛሙርቱ ጋር ሆኖ እንዲህ አለ፦ «ከቃላቸው የተነሳ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለእነዚህ ብቻ አልለምንም» (ዮሐ. 17:20)።

ኢየሱስ እርሱ ከአብ ጋር አንድ እንደሆነ እኛም ከእርሱ ጋር አንድ እንድንሆን ፀልዮልናል። ይህ እንዴት ያለ አስደናቂ ሕብረት ነው! አዳኙ ስለ ራሱ ሲናገር እንኳን «ወልድ በራሱ ምንም ማድረግ አይችልም»፤ «በእኔ የሚኖረው አብ ግን ይህን አድርጓል» ዮሐ. 5:19 ና 14፡10) በማለት ተናግሯል። ክርስቶስ በእኛ ልብ የሚኖር ከሆነ «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም» በእኛ

ውስጥ ይሰራል ማለት ነው (ፊሊ. 2:13)። ያን ጊዜ እርሱ እንዳደረገ እንደዛው እናደርጋለን፤ ያንኑ መንፈስ እንገልጻለን። እናም እርሱን በማፍቀርና በእርሱ በመኖር «በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ» እናድጋለን (ኤፌ. 4፡15)።

# ምዕራፍ 9 - ሥራ አና ሕይወት

እኔ ግዚአብሔር ለዓለማት ሁሉ የሕይወት፣ የብርሃንና የደስታ ምንጭ ነው። የብርሃን ጨረር ከጸሐይ እንደሚፈነጥቅ፣ የወንዝ ውሃም ከምንጭ ፈልቆ እንደሚጐርፍ እግዚአብሔርም በረከቱን ለፍጥረቱ ሁሉ አብዝቶ ይሰጣል። መለኮታዊ ሕይወት በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ሲኖር ከዚያ ሰው ልብ ለሌሎች ሰዎች የሚሆን ፍቅርና በረከት ይፈልቃሉ።

የአዳኛችን ደስታ በኃጢአት የወደቀውን ሰው ማንሳትና ማዳን ነበር። ለዚህም ነው ለሕይወቱ ሳይሳሳ ነገር ግን መስቀሉን ታግሶ፣ ነውርንም ንቆ ያለፈው። መላእክትም እንዲሁ ሌሎች ፍጡራንን ደስ ለማሰኘት ሁልጊዜ ይሰራሉ:: ይህም ለእነርሱ

ደስታቸው ነው:: ራስ ወዳዶችና ትእቢተኞች የሚንቁት፣ ድሆችንና የተዋረዱትን፣ በማእረግም ዝቅ ያሉትን የማገልገል ሥራ በኃጢአት ያልወደቁት መላእክት በደስታ ይሰሩታል። የክርስቶስ እራሱን መስዋት አድርጎ የመስጠት የፍቅር መንፈስ የመንግስተ ሰማይ መመሪያ ነው። ይህም እውነተኛ ደስታን ለማግኘትም በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። የክርስቶስ ተከታዮችም ተመሳሳይ መንፈስን በመጋራት፣ ተመሳሳይ ሥራን ይሰራሉ።

የክርስቶስ ፍቅር በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ሲኖር ልክ ጣፋጭ ማዕዛ እንዳለው እጣን ሊሸሸግ አይችልም። የዚህን ፍቅር ቅዱስ ኃይል የምናገኛ ቸው ሰዎች ሁሉ ያዩታል:: በአንድ ሰው ልብ ውስጥ የሚኖረው የክርስቶስ መንፈስ የደረቀውን ሁሉ

እንደሚያረሰርስ፣ ሊሞቱ የቀረቡትንም በፍጥነት ወደ ሕይወት ውሀ እንዲመጡ እንደሚያደርግ በበረሀ ውስጥ እንዳለ የውሀ ምንጭ ነው:: ኢየሱስን መውደዳችን የሚገለጸው እርሱ ይሰራ እንደነበረው ሰዎችን የማበረታታትና ለሰዎች በረከት የሚጠቅም ስራ ስንሰራ ነው። የክርስቶስ ፍቅር የሰማዩ አባታችን የሚያስብላቸውን ፍጥረታት ሁሉ እንድንወድ፣ እንድንራራላቸው፣ ችግራቸውንም እንድንካፈልላቸው ወደ መልካም ሃሳብ ይመራናል።

የአዳኛችን የምድር ሕይወት የምቾትና ራስን የመውደድ ሕይወት አልነበረም። የጠፋውን የሰው ዘር ለማዳን ደከመኝ ሳይል በቅንነት ያለማቋረጥ ለፋ። ከበረት ጀምሮ እስከ ቀራንዮ ድረስ «ስራው ከበደኝ፣ ጉዞው

ሰለቸኝ፣አቅም አጣሁ» ሳይል ራስን የመካድን ጉዞ ተጓዘ። ስለራሱ ሲናገር እንዲህ አለ፥ «የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና» (ማቴ. 20:28)። በምድር ሳለ የነበረው ዋና ዓላማ ይህ ነበር። ሌላው ሁሉ ሁለተኛና ከዚህ በታች የሚመጣ ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግና ስራውን መፈጸም የእርሱ መብልና መጠጥ ነበር። ራስንና የራስን ጥቅም መውደድ በስራው ውስጥ ቦታ የላቸውም ነበር።

የክርስቶስ ጸጋ ተካፋዮች የሆኑ ሁሉ ይህንን የሰማይ ስጦታ ሌሎች ክርስቶስ የሞተላቸው ሰዎችም እንዲያገኙ ማንኛውንም አገልግሎትና መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጁ ይሆናሉ። በዓለማችን ላይ የተሻለ

ሕይወት እንዲኖር የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። እንደዚህ ያለ መንፈስ ከልብ ወደ ጌታዋ የተመለሰች ነፍስ ፍሬ ነው፡፡

የክርስቶስ ፍቅር በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ሲኖር፣ ልክ ጣፋጭ ማዕዛ እንዳለው እጣን ሲሸሸግ አይችልም።

አንድ ሰው በርግጥ ወደ ክርስቶስ ለመመለሱ ማረጋገጫው፤ እርሱ ስላገኘው የከበረ ወዳጅ ስለ ኢየሱስ ለሌሎች ለመመስከር ፍላጎት ሲያድርበት ነው፡፡ ይህንን የሚያድንና የሚቀድስ እውነት ለራሱ ብቻ ይዞ መቀመጥ አይችልም። የክርስቶስን ጽድቅ ከለበስንና በልባችን በሚኖረው የመንፈሱ ደስታ ከተሞላን ዝም ልንል አንችልም፡፡ ጌታ ቸር እንደሆነ ከቀመስንና ካየን የምንናገረው ነገር ይኖረናል። እንደ ፊሊጶስ እኛም መድኅንን

ካገኘን በኋላ ሌሎችን ወደ እርሱ እንጋብዛለን። ስለ ክርስቶስ የማዳን ኃይል እንዲሁም አሁን በዓይን ስለማይታየው ነገር ግን ስለሚመጣው የጌታ መንግስት እውነታ ለእነርሱ ለመንገር እንጓጓለን። ኢየሱስ የሄደበትን ፍለጋ ለመከተል ጥልቅ ፍላጎት ያድርብናል። በዙሪያችን ያሉት ሰዎችም «የዓለምን ኃጢአት ሁሉ የሚያስወግደውን የእግዚአብሔርን በግ» ዮሐ. 1፡ 29) እንዲመለከቱ የጋለ መሻት ይኖረናል።

ሌሎች ሰዎች እንዲባረኩ የሚጥር ሰው ራሱ በረከትን ይቀበላል። በድነት ስራ ላይ እንድንተባበር እግዚአብሔር ሲጋብዘን ዓላማው ይህ ነበር። በፀጋው የመለኮታዊው ኃይል ተካፋዮች እንድንሆን አድርጎናል፤ በምላሹም እኛ የተሰጠንን በረከት ለሌሎች ሰዎች እንድናካፍል ይፈልጋል። እግዚአብሔር

ይህንን በረከት ለሰዎች መስጠቱ ትልቅ ደስታና ክብር ነው፡፡ በፍቅር አገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉ ሁሉ ወደ ፈጣሪያቸው ይበልጥ እየተጠጉ ይመጣሉ፡፡

ወንጌልን የማሰራጨት ኃላፊነትንና የፍቅር አገልግሎት ማበርከትን እግዚአብሔር ለመላእክቱ መስጠት ይችል ነበር። ዓላማውን ለማከናወን ሌላ መንገድ መቀየስም ይችል ነበር። ቢሆንም ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ከእርሱ፣ከክርስቶስና ከመላእክቱ ጋር ተባብረን በመስራት በዚያ ውስጥ የሚገኘውን በረከት፣ ደስታ እና መንፈሳዊ እርካታ እንድንካፈል ፈለገ።

የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች ስንሆን የእርሱን ርህራኄ ጭምር እንጋራለን።ራስን መስዋዕት በማድረግ የሚከናወን በጎ አድራጎት፣

በድርጊት ፈጻሚው ልብ ውስጥ የለጋስነትን ስሜት የሚያጠናክር ሲሆን «በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ» (2 ቆሮ. 8፡ 9) ከሆነው የዓለም አዳኝ ጋር ይበልጥ ያቀራርበዋል:: አምላክ ለእኛ ያለውን ዓላማ በእርግጠኝነት ስንከተል ሕይወታችን ለሌሎች በረከት ይሆናል።

ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ በነደፈው እቅድ መሠረት ብትሰሩና ነፍሳትን ወደ እርሱ ብትማርኩ፣ መለኮታዊውን ነገር በጥልቀት ለመለማመድና ጠንቅቆ ለማወቅ የሚኖራችሁ ፍላጎት ይጨምራል፤ ጽድቅንም የምትራቡና የምትጠሙ ትሆናላችሁ:: እግዚአብሔርን የሙጥኝ ትላላችሁ፤እምነታችሁም ይጠነክራል፤ ነፍሳችሁም ከድነት የውሃ ጉድጓድ ጠለቅ አድርጋ መቅዳትና መጠጣት ትችላለች።

ራስን ብቻ የመውደድ መንፈስ የሌለበት አገልግሎት ከአስመሳይነት ይጠብቀናል፣ ጥንካሬንና ፍቅርን ያስገኝልናል፣ ሰላምንና ደስታም ይሰጠናል።መንፈሳዊነታችንም ከፍ እያለ ይሄዳል። በመሆኑም ስንፍናና እራስን ብቻ መውደድ በእኛ ዘንድ ስፍራ አይኖራቸውም:: በመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ ዎች የሚያገለግል ሰው በእግዚአብሔር እየበረታና እየጠነከረ ይሄዳል፣ ንጹህ መንፈሳዊ እውቀትን ያገኛል፣ በእምነትና በጸሎት ኃይልም ይጸናል (ይበረታል)። እግዚአብሔርን በመተዋወቁ ምክንያት መንፈስ ቅዱስ የአማኙን ልብ ከሰማይ አባት ጋር ቅዱስ ስምምነት እንዲኖረው ያደርገዋል። ለሌሎች መልካም እንዲሆንላቸው ራስን ብቻ መውደድ በሌለበት ጥረት እራሳቸውን ለሌሎች

ቀድሰው የሚሰጡ ሁሉ ለራሳቸው ደህንነት እጅግ ጠንክረው በመስራት ላይ ናቸው፡፡

በክርስቶስ ጸጋ የምናድገው የራሳችንን ጥቅም ብቻ ሳንፈልግ ክርስቶስ ለኛ የሰጠውን ስራ ስናደርግና በተቻለን ኃይል የእኛ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ስንደርስ ብቻ ነው፡፡ ኃይል በስራ ልምምድ ነው የሚገኘው። ስራ ደግሞ ለሕይወት ዋና ነገር ነው፡፡ ለክርስቶስ አንዳች ነገር ሳይሰሩ ከጸጋው የሚገኘውን በረከት በመቀበል ብቻ የክርስቶስን ሕይወት ለማግኘት የሚጥሩ ሁሉ ሳይደከሙና ሳይጥሩ መብላትን የሚፈልጉትን ይመስላሉ። እንደዚህ አይነት አስተሳሰብ በመንፈሳዊም ሆነ በስጋዊ ሕይወት ውርደትንና ጥፋትን ያመጣል። አካሉን ስራ ከማስለመድ እንቢ የሚል ሰው ሰውነቱን ማንቀሳቀስ እስኪሳነው ድረስ

በቶሎ ኃይል ያጣል። እግዚአብሔር በሰጠው ስጦታ የማያገለግል ክርስቲያንም እንዲሁ በክርስቶስ ማደግ ካለመቻሉ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም የሰበሰበውን ኃይል ሁሉ ያጣል።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የመረጣት ሰውን ለማዳን እንድትሰማራ በማሰብ ነው፡፡ የጥሪዋም ዋና ዓላማ ወንጌልን ለዓለም ማዳረስ ነው፡፡እያንዳንዱ ክርስቲያን በተሰጠው ስጦታ እና አጋጣሚ የአዳኙን ትእዛዝ እንዲፈጽም ታዟል። ለእኛ የተገለጸው የክርስቶስ ፍቅር ላልሰሙትና ለማያውቁት እንድንነግር ባለእዳ ያደርገናል፡፡ እግዚአብሔር ብርሃኑን የሰጠን ለኛ ብቻ እንዲሆን አይደለም ለሌሎችም እንዲበራላቸው ጭምር እንጂ።

የክርስቶስ ተከታዮች ይህንን ስራ ለመስራት ከልባቸው ቢፈልጉ ኖሮ ዛሬ አንድ ሰው ብቻ ባለበት ስፍራ አንድ ሺህ ወንጌልን የሚያሰራጩ ሰዎች በተገኙ ነበር፡፡ አንድ ሰው ወንጌልን እርሱ ራሱ ማሰራጨት ባይችልም እንኳን ቢያንስ በገንዘቡ፣ በበጎ ፈቃዱ እና በጸሎቱ ሊያግዝ ይገባዋል። እንዲህ ቢሆን ከአሁኑ አዳኞችን የበለጠ የነፍሳት ማዳን ስራ በክርስቲያን አገሮች ድጋፍ አማካኝነት በተካሄደ ነበር።

አብዛኛውን የሕይወት ዘመኑን ናዝሬት በሚገኘው አነስተኛ የአናጢ ቤት ነበር ሲሰራ የቆየው።

ክርስቶስን ለማገልገል ወደ ሩቅ አገሮች መሄድ ወይም ደግሞ አገራችንን ለቀን መሄድ እንኳን አያስፈልገን ይሆናል።

በቤታችን፣ቤተክርስቲያናችን፣ከወዳጆቻችን
ና በሥራ ቦታችን ከምናገኛቸው ሰዎች ጋር
መልካሙን የምስራች መካፈል እንችላለን።
አዳኛችን አብዛኛውን የሕይወት ዘመኑን
ናዝሬት በሚገኘው አነስተኛ የአናጢ ቤት
ነበር ሲሰራ የቆየው:: የሕይወት ታ
ከገበሬዎችና ከወዛደሮች ጋር ጐን ለጐን ሆኖ
ሲሰራ እነርሱ ባያስተውሉትም እንኳን
የሚያገለግሉት መላእክቱ ዙሪያውን ከበውት
ነበር።የእጅ ሙያ ስራ ይሁን፣ በሽተኞችን
መፈወስ፣ ወይም በገሊላ ባህር ላይ
መራመድ፣ ኢየሱስ የትኛውንም አገልግሎቱን
በታማኝነት ይፈጽም ነበር።እንዲሁም እኛም
የተሰጠንን ኃላፊነት ትንሽም ብትሆን
እንኳን ከኢየሱስ ጋር በመሆን ማከናወን
ይገባናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሲጽፍ እንዲህ አለ «ወንድሞች ሆይ እያንዳንዱ በተጠራበት እንደዚሁ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ይኑር» (1 ቆሮ. 7:24)። ነጋዴው በታማኝነት ሲነግድ ጌታውን በሚያስከብር መንገድ እየሰራ ነው ማለት ነው:: እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ ከሆነ በሚያደርገው ነገር ሁሉ ኃይማኖቱን ያሳያል ፣ የክርስቶስንም መንፈስ ለሰዎች ይገልጻል።

የእጅ ሙያ ያለው ደግሞ በታታሪነቱና በታማኝነቱ በገሊላ ተራ ስራ ሲሰራ የነበረውን የኢየሱስን ባህሪይ ያንጸባርቃል። እያንዳንዱ የክርስቶስን ስም የሚጠራ ሁሉ ሌሎች መልካም ስራውን በማየት የእርሱን ፈጣሪና አዳኝ ያከብሩ ዘንድ ስራውን በታማኝነት መስራት አለበት::

«ከእኔ ይልቅ ሌሎች የተሻለ ችሎታና የተመቻቸ ሁኔታ አላቸው» የሚል ምክንያት በመስጠት ብዙዎች ስጦታቸውን ለክርስቶስ አገልግሎት ለማዋል ፈቃደኞች አይደሉም:: «ልዩ ስጦታ ያላቸው ብቻ ናቸው የእግዚአብሔርን ስራ መስራት የሚችሉት» የሚለው አስተሳሰብም የመጣው ከእንደዚህ አይነቱ አቋም ነው። እንዲያውም «ለጥቂቶች ብቻ ነው ስጦታ የተሰጠው፤የቀሩቱ ግዴታ የለባቸውም፤ ሽልማትም አይሰጣቸውም» ብለው የሚያስተውሉ ብዙዎች አሉ። ኢየሱስ ግን ለአገልጋዮቹ ስራ ስላከፋፈላቸውአንድ ጌታ በተናገረው ምሳሌ ላይ ከቶ እንዲህ አላለም:: ምሳሌው «ጌታውአገልጋዮቹን ስበስቦ ለእያንዳንዱ ስራን ሰጥቷቸው ሄደ» ነው የሚለው::

በሰው አይነት አነስተኛ ግምት የሚሰጠው አገልግሎትም ቢሆን «ለጌታ እንደምናደርገው» (ቆላ. 3፥ 23) በማሰብ በደስታ መንፈስ እናገልግል። የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ውስጥ ካለ በሕይወታችን ይገለጣል። የክርስቶስ መልካም ማዕዛ ዙሪያችንን ይከበናል፤ በሌሎች ላይ የምናሳድ ረው ተጽእኖም ወደ ሰማይ ከፍ የሚያደርጋቸውና የሚባርካቸው ይሆናል።

ለእግዚአብሔር ለመስራት ትልቅ አጋጣሚ እስኪከሰት ድረስ ወይም ደግሞ ልዩ ችሎታ እስኪኖረን ድረስ አንጠብቅ፡፡ ሌሎች ስለእኛ ስለሚያስቡትም ሆነ ስለሚናገሩት ልባችን አይጨነቅ፤ በየዕለቱ ሕይወታችን የምናሳየው በንጽህናና በሀቀኝነት የተሞላው እምነታችን ምስክር ከሆነ እንዲሁ ሌሎች ሰዎች በሙሉ ልባችን ልንረዳቸው

እንደምንፈልግሲያስተውሉ ልፋታችን ከንቱ እንዳልሆነ እንወቅ።

ትሁትና ምስኪን የሆኑ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለሌሎች ሰዎች በረከት ይሆናሉ:: እነርሱ ምናልባት መልካም ነገር እያደረጉ መሆናቸው አይታወቃቸው ይሆናል:: ቢሆንም ከእነርሱ ውስጥ ኃይለኛ የበረከት ምንጭ ይፈልቃል። የአገልግሎታቸውም ፍሬ በመጨረሻው የፍርድ ቀን ለሁሉም ግልጽ ሆኖ ይታያል። ትልቅ ነገር ማድረጋቸው አይታወቃቸውም፣ስለጥረታቸውም ውጤታማነት አይጨነቁም። ስራቸውን ያለማወላወልይሰራሉ፣ እግዚአብሔር እንደባለጥበብነቱ የሰጣቸውን ኃላፊነት (ስራ)በታማኝነት ያከናውናሉ። በመሆኑም ሕይወታቸው እንዲሁ ከንቱ አይሆንም። እንዲያውም ክርስቶስን እየመሰሉ ይሄዳሉ።

በዚህ ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ተባብረው በመስራት ወደፊት ለሚጠብቃቸው ኃላፊነትእንዲሁም በዘላለም ሕይወት ለሚያገኙት ፍጹም ደስታ የተዘጋጁ ይሆናሉ።

# ምዕራፍ 10 - እግዚአብሔርን ማወምዕራፍቅ

እግዚአብሔር ለእኛ ራሱን ለማስተዋወቅና ከእርሱ ጋር ሕብረት እንዲኖረን የሚጠቀምባቸው መንገዶች ብዙ ናቸው። ተፈጥሮ ያለማቋረጥ ለሕሊናችን እግዚአብሔር መኖሩን ይነግረናል። ልቡን ከፍቶ ያስተዋለ ሰው ሁሉ በእጁ ስራ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፍቅርና ክብር በማየት ይደነቃል። ጆሮውን ከፍቶ ያዳመጠ ሰው ሁሉ ደግሞ እግዚአብሔር በተፈጥሮ አማካኝነት ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ለመስማትና ለማስተዋል ይችላል። የለመለሙት መስኮች፣ ረዣዥም ዛፎች፣ ቡቃያዎች፣ አበቦች፣ የሠማይ ደመናዎች፣ የሚዘንቡት ዝናቦች፣ ፈሳሽ ውሃዎች እና በሠማይ ያሉ ፍጥረቶች ሁሉ ለልቦቻችን

መልዕክትን ያስተላልፋሉ። እነዚህ ሁሉ እኛን ከፈጣሪ ጋር ለማስተዋወቅ ይጋብዙናል።

አዳኛችን ጠቃሚና ክቡር ትምህርቶቹን በፈጠረው ፍጥረት ውስጥ አስቀመጠ። በሥራ ብዛት የተወጠረውን ማንኛውም ሰው እንኳን ቢሆን የእግዚአብሔርን ትምህርት ሁልጊዜ ማስታወስ እንዲችል ብሎ ከዛፎች፣ ከወፎች፣ በሸለቆ ውስጥ ካሉት አበባዎች፣ ከኮረብታዎች፣ ከባሕሮች፣ ከኩሬዎች፣ ከሚያምሩት ሠማያት እንዲሁም በዙሪያችን ካሉት በእግዚአብሔር ቃል ከተፈጠሩት ፍጥረቶች ሁሉ ጋር የእውነትን ቃል አያይዞታል።

እግዚአብሔር ባማረ ውበት ያስጌጣትን ምድራዊ ቤታችንን በማየት ልጆቹ እንዲደሰቱና እንዲያደንቁ ይፈልጋል። እርሱ

ውበትን ይወዳል። በውጪ ከሚታዩት ነገሮች ሁሉ ይልቅ ግን ልጆቹ ያማረ ባሕርይ ፣ ንፅህና፣ ገርነት፣ እና በአበቦች ላይ የሚታየው አይነት ግርማ ሞገስ እንዲኖራቸው ይወዳል። በማስተዋል ካዳመጥን የእግዚአብሔር ፍጥረታት ስለመታዘዝና ስለመታመን ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን ይሰጡናል።

ኮቴ በሌለው መንገዳቸው በሕዋው ውስጥ ከዘመናት እስከ ዘመናት በተመደበላቸው መንገድ ከሚጓዙት የሠማይ ከዋክብት ጀምሮ በጣም ትንሽ እስከሆነችው ነገር (አተም) ድረስ ፍጥረት ለፈጣሪው ፈቃድ ይታዘዛል። እግዚአብሔር ለፈጠረው ሁሉ ያስባል፣ የሚያስፈልገውንም ሁሉ በሰዓቱ ይሰጠዋል። ከማስተዋል በላይ በሆነው ኃይሉ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ዓለማት የያዘው አምላክ ትሁት ዜማውን ለሚያዜመው ትንሹ ወፍ እንኳን

ይጠነቀቃል፤ የሚሻውንም ይሰጠዋል። ሰዎች የዕለት ስራቸውን ለመስራት ከቤታቸው ሲወጡ፣ ፀሎት ሲፀልዩ፣ በሌሊት ሲተኙም ሆነ በጠዋት ሲነሱ፣ ሃብታም ሰው በደስታ ሲበላና ሲጠጣ፣ ደሃውም ሰው በትንሹ ገበታው ዙሪያ ልጆቹን ሲሰበስብ እያንዳንዱ ነገር በሠማይ ባለው ሩህሩህ አባት ዓይን ታይቷል። እግዚአብሔር ያልተመለከተው የፈሰሰ እንባ የለም፣ የማያስተውለው ፈገግታም የለም።

በማስተዋል ካዳመጥን የእግዚአብሔር ፍጥረታት፣ ስለመታዘዝና ስለመታመን ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን ይሰጡናል።

ይህንን እውነት ሙሉ በሙሉ ብናምን ተገቢ ያልሆነው ስጋትና ሸብር ሁሉ ከኛ በራቀ ነበር። ሕይወታችንም እንደ አሁኑ ተስፋ

መቁረጥ አይታይበትም ነበር። በዛ ፊንታ ትንሽም ሆነ ትልቅ የችግራችን ብዛት በማያስጨንቀውና የክብደቱ መጠን በማያስቸግረው በእግዚአብሔር እጅ ላይ ሁሉን እንተወዋለን። ከዚያም ብዙ ሰዎች ለብዙ ዘመናት ያላገኙትን የነፍስ እረፍት በማግኘት እንደሰታለን።

የስሜት ህዋሳቶቻችን በምድር ውበት የሚደሰቱ ከሆነ እንግዲያውስ ኃጢአትና ሞት ያላቆሸሸውንና፣ የእርግማን ጥላ የማያጠላበትን ወደ ፊት የሚመጣውን ዓለም እናስብ። በምናባችሁ የጻድቃንን መኖሪያ ሳሉት። የፈለገ ብሩህ አእምሮ ቢኖረን እኛ ከምንገምተው በላይ እንደሆነ ግን እናስታውስ። እግዚአብሔር በተፈጥሮ ውስጥ በሰጠን የተለያዩ ስጦታዎች ማየት የምንችለው የእግዚአብሔርን የክብሩን

ብልጭታ ብቻ ነው። ‹‹ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንድተጻፈ÷ እንዲህ እንናገራለን።›› (1 ቆሮ. 2፡ 9)።

አዎ፣ ደራሲዎችና የተፈጥሮ ተመራማሪዎች ስለተፈጥሮ ውበት ብዙ የሚፅፉትና የሚናገሩት ይኖራል። በተፈጥሮ ውበት በእጅጉ የሚደሰተው ግን ክርስቲያን የሆነ ሰው ነው። ምክንያቱም ተፈጥሮ የአባቱ የእግዚአብሔር ድንቅ የእጅ ስራና በእያንዳንዱ አበባ፣ ቁጥቋጦና ዛፍ ላይ ደግሞ ፍቅሩ ሲንጸባረቅ ይመለከታልና። ተራራዎችና ሸለቆዎች ወንዞችና ባሕሮች የእግዚአብሔር ፍቅር መግለጫዎች እንደሆኑ የማያስተውል ሰው የተፈጥሮን ውበት ሙሉ በሙሉ ለማድነቅ አይችልም።

አዳኙን ለመተዋወቅ ከፈለጋችሁ መጽሐፍ ቅዱስን አጥኑ።

እግዚአብሔር አስደናቂ በሆነው እንክብካቤውና ጥበቃው እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ለልባችን ብዙ ይናገራል። ልባችንን ከፍተን ማስተዋል ከቻልን በሚያጋጥሙን የየዕለቱ ገጠመኞችና በአካባቢያችን በሚከሰቱት ክስተቶች ጠቃሚ ትምህርቶችን ማግኘት እንችላለን። ስለ እግዚአብሔር ዘወትር የሚያሰላስለው ዘማሪ እንዲህ በማለት ፅፏል፦ ‹‹የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች።›› ‹‹ጥበበኛ የሆነና ይህን የሚጠብቅ ማን ነው? እርሱ የእግዚአብሔርን ምሕረት ያስተውላል።›› (መዝ. 33፡ 5፤ 107፡ 43)።

እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነትም ይናገረናል። ስለ ባሕርይውም፣ ለእኛ ስላለው ዓላማ እና የጠፋውን ሰው ለማዳን ስላላው እቅድ ቃሉ የበለጠ ግልፅ በሆነ መንገድ ይነግረናል። በቃሉ ውስጥ የአበው፣ የነብያት እንዲሁም የሌሎች ቀደምት ቅዱሳን ታሪክ ተፅፎ እናነባለን። እነርሱም ‹‹እንደኛ ሰው ነበሩ›› ያዕ. 5.17። እንደኛ ከተስፋ መቁረጥ ጋር የታገሉ በፈተናም ውስጥ የወደቁ ነበሩ፤ ቢሆንም እንደገና ድፍረትን በማግኘት በእግዚአብሔር ፀጋ አማካኝነት አሸናፊዎች ሆኑ። በእነርሱ ምሳሌነት እኛም በጽድቅ ጎዳና በምንሮጠው ሩጫ መበረታትን እናገኛለን። እነዚያ የእግዚአብሔር ልጆች ስላሳለፏቸው ድንቅ ልምምዶች ስናነብ፣ በተገለጠላቸው ብርሃን፣ ፍቅርና በረከት አማካኝነት ያገኙ ስለነበረውም ደስታ ስናነብ፣ በተሰጣቸው ፀጋ አማካኝነት ያደርጉ

ስለነበረው ስራ ደግሞ ስንሰማ፤ ያ በእነርሱ ውስጥ ይሰራ የነበረው መንፈስ ቅዱስ እኛም እንደነርሱ አይነት ባሕርይን እንድንላበስ በልባችን ውስጥ የተቀደሰ ፍላጎት እሳትን ያቀጣጥላል።

ኢየሱስ ስለ ብሉይ ኪዳን እንዲህ በማለት የተናገረው መግለጫ ለአዲስ ኪዳንም ገጣሚ ነው፦ ‹‹እነርሱ ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው›› (ዮሐ. 5፡39) ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ አዳኙ፣ የዘላለም ሕይወት ተስፋችን መሠረት ስለሆነው ይመሰክራሉ። አዎ መላው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ይናገራል ‹‹ያለእርሱ ምንም ነገር አልተፈጠረም›› (ዮሐ. 1፡3) ከሚለው ከፍጥረት ታሪክ ጀምሮ ‹‹እነሆ በቶሎ እመጣለሁ›› (ራዕይ 22፡12) እስከሚለው የመጨረሻ ተስፋ ቃል ድረስ በቃሉ ውስጥ ስለ እጁ ስራ እናነባለን፣

ድምፁንም እንሰማለን። አዳኙን ለመተዋወቅ ከፈለጋችሁ መጽሐፍ ቅዱስን አጥኑ። ልባችሁን በእግዚአብሔር ቃል ሙሉት። ጥማታችሁን ሊያረካ የሚችል ሕያው ውሃ ነውና። ከሠማይ የወረደ ሕያው እንጀራ ነውና። ኢየሱስ ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።›› (ዮሐንስ 6፡53) አለ። ምን ለማለት እንደፈለገ ሲያብራራም፡- ‹‹እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው።›› (ዮሐ. 6፡63) ብሎ ተናገረ። ሰውነታችን ጥንካሬን የሚያገኘው ዕለት ዕለት በሚመገበው ምግብና በሚጠጣው ውሃ ነው። ለተፈጥሮአዊ ሰውነታችን ምግብና ውሃ እንዲህ ወሳኝ ከሆነ ለመንፈሳዊውም ህይወታችን እንደዚያው ነው። ለመንፈሳዊ

ተፈጥሮአችን ጥንካሬንና መልክን የሚሰጠው የምናሰላስለው ነገር ነው።

ኃጢአተኛውን ሰው በመቤዠት እግዚአብሔር የሰራው ሥራ መላእክት በጥልቅ ሊመረምሩት የሚመኙት ርዕስ ነው። ይህ የድነት ሚስጢር የዳኑት ፃድቃን ለዘለዓለም የሚመረምሩት ሳይንስ እንዲሁም የውዳሴ መዝሙራቸው ዋና ርዕስ ይሆናል። ታዲያ ይህንን ጠቃሚ ርዕስ ዛሬውኑ በሰፊው ልናጠናው አይገባምን ወሰን የለሹ የኢየሱስ ምህረትና ፍቅሩ በእኛ ፈንታ የከፈለው መስዋትነት፣ ስለዚህ አስፈላጊ ጉዳይ በደንብ እንድናስብበት ጥሪ ያቀርቡልናል። አዕምሮአችንና ሃሳባችን ሁሉ ስለአዳኛችን እና ስለአማላጃችን ባሕርይ እንዲሁም ሕዝቡን ከኃጢአት ለማዳን ስለመምጣቱ ዓላማ ማሰብና ማሰላሰል

አለበት። ስለ እነዚህ ሰማያዊ ነገሮች በበለጠ በምናሰላስልበት ጊዜ እምነታችንና ፍቅራችን የበለጠ እየጠነከረ ይሄዳል፣ ፀሎታችንም በእምነትና በፍቅር የተሞላ ስለሚሆን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ያገኛል። በመሆኑም በኢየሱስ ላይ ያለን እምነት የበለጠ ይጠነክራል፣ ዕለት በዕለትም የኢየሱስን የማዳን ኃይል በሕይወታችን እንለማመዳለን።

የጥሞና ጊዜ ወስደን ስለአዳኛችን ፍፅምና በምናሰላስልበት ጊዜ አዲስ ፍጡር ለመሆንና እርሱን ለመምሰል በልባችን ምኞት ይቀሰቀሳል። የምታመልከውን አምላክ ለመምሰል ነፍሳችን ትራባለች፤ ትጠማለች። ልባችን የበለጠ በክርስቶስ እየሞላ በሄደ ቁጥር ስለእርሱ ማንነት የበለጠ ለሌሎች

እንናገራለን፣ በዓለምም ላሉት እንመሰክራለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ለተማሩ ሰዎች ብቻ አይደለም፤ እንዲያውም ተራ ለሚባሉት ሰዎች ታስቦ ነው የተጻፈው። ለድነታችን አስፈላጊ የሆኑት እውነቶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ቀትር ፀሐይ ግልፅ ሆነው እናገኛቸዋለን። ግልፅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፍቃድ ትቶ በራሱ አስተሳሰብ ለመሄድ የሚፈልግ ሰው ካልሆነ በስተቀር ማንም ሊሳሳትና ትክክለኛውን መንገድ ሊስት አይችልም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን በተመለከተ ማንም ሰው የሚለንን ተከትለን መሄድ የለብንም። የእግዚአብሔርን ቃል በግላችን ልናጠናው ይገባል። ራሳችን በመመርመር

ፈንታ ሌሎች ስለእኛ እንዲመረምሩልን በምንፈቅድበት ጊዜ አዕምሮአችንን እያዳከምን መሄድ ብቻ ሳይሆን የማገናዘብ ችሎታችንም እየመነመነ ይሄዳል። የእግዚአብሔርን ቃል የጠለቀ ትርጉም የማይመረምር አዕምሮ አያድግም። አዕምሮአችን እየበሰለ የሚሄደው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በተመለከተ አንድን ጥቅስ ከሌላው ጥቅስ ጋር እያጣቀስን ፣ መንፈሳዊ ነገርን ከመንፈሳዊ ነገር ጋር እያነፃፀርን በምናጠናበት ጊዜ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን እንደማጥናት የአእምሮእንን የማገናዘብ ችሎታ የሚያጠነክር ሌላ ነገር የለም። አሳባችንን ከፍ የሚያደርግ እንደ እግዚአብሔር ቃል ያለ ሰፊና የከበሩ እውነቶችን የያዘ ሌላ መጽሐፍ የለም። መጽሐፍ ቅዱ እንደሚገባ ተጠንቶ

ቢሆን ኖሮ በዚህ ዘመን ብርቅ የሆኑትን የአእምሮ መስፋት፣ የባሕርይ ክቡርነትንና የዓላማ ጽናትን ሰዎች መቀዳጀት በቻሉ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስን በጥድፊያ በማንበብ ምንም ጥቅም አይገኝም። አንድ ሰው በውስጥ ውበቱን ሳያይ ወይም ጥልቅና የተሰወረውን ትርጉሙን ሳያስተውል መፅሀፍ ቅዱስን ከመጀመሪያው ገፅ እስከ መጨረሻው ገፅ ሊያነብ ይችላል። ትርጉሙ ምን እንደሆነ እስኪገባንና ከድነት እቅድ ጋር ጥቅሱ ያለውን ግንኙነት እስክናስተውል ድረስ የምናጠናው አንድ ጥቅስ፣ ያለ ዓላማና ከውስጡም ለእኛ የሚሆን ምንም መመሪያ ሳናገኝበት ከምናነበው የብዙ ምዕራፎች ንባብ ይሻላል። መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ሁልጊዜ ከእናንተ አይለይ። በአገኛችሁት አጋጣሚ ሁሉ

አንብቡት፤ ጥቅሶቹንም በቃላችሁ ያዙ። እንዲያውም በመንገድ ስትጓዙ አንድ ክፍልን አንብቡና በዚያ ክፍል ላያ አሰላስሉ። በዚህ መልኩ ቃሉ በአዕምሮዎ ውስጥ ይቀመጣል።

መጽሐፍ ቅዱስ ለተማሩ ሰዎች ብቻ አይደለም፤ እንዲያውም ‹‹ተራ›› ለሚባሉት ሰዎች ታስቦ ነው የተጻፈው።

በማስተዋልና በፀሎት ካላጠናነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚ እውቀትን ማግኘት አንችልም። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ግልፅ በመሆናቸው ምንም አያሳስቱም ቢሆንም ትርጉማቸው ሙሉ በሙሉ ግልፅ ያልሆኑ በጥንቃቄ ሊጠኑ የሚገባቸው አንዳንድ ጥቅሶች አሉ። እነዚህን ጥቅሶች ከሌሎች ጥቅሶች ጋር ማነፃፀር ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ መፀለይና

በጥንቃቄ መመርመር ግድ ነው። በዚህ መልኩ ከመረመርን ትልቅ ሽልማት እናገኝበታለን። ልክ አንድ ማዕድን ቆፋሪ በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኘውን የከበረ ድንጋይ በጥልቀት ቆፍሮ እንደሚያወጣ፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተደበቁትን እንቁዎች ለማግኘት ተግቶ የሚፈልግ ማንም ሰው ለሕይወቱ እጅግ ጠቃሚ እውነቶችን ያገኛል። ላይ ላዩን ለሚያነብ ሰው ግን እነዚህ እውነቶች አይታዩትም። ወደ ልባችን የምናስገባቸውና የምናስቀምጣቸው የእግዚአብሔር ቃሎች ከሕይወት ፏፏቴ እንደሚፈስ ምንጭ ይሆኑልናል።

መጽሐፍ ቅዱስን በምንም ዓይነት ያለፀሎት ማጥናት የለብንም። ገፆቹን ከመግለጣችንና ከማንበባችን በፊት መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንዲገልጥልንና እንድናስተውል እንዲረዳን

ልንጠይቀው ይገባል። እግዚአብሔርም ይገልጥልናል። አንድ ጊዜ ናትናኤል ወደ ኢየሱስ ሲመጣ አዳኛችን ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ «ተንኮል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ» ናትናኤልም ሲመልስ «ከወዴት ታውቀኛለህ;» አለው። ኢየሱስ ሲመልስ «ፊሊጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ» አለው። (ዮሐ. 1፡ 47-48)። ዛሬም ኢየሱስ የእውነትን ብርሃን ለማግኘት በስውር ሆነን ወደእርሱ ስንፀልይ እያንዳንዳችንን ያየናል። ቅዱሳን መላዕክት እራሳቸውን ዝቅ አድርገው በትህትና የእግዚአብሔርን አመራር ከሚሹ ሁሉ ጋር ይሆናሉ።

መንፈስ ቅዱስ አዳኛችንን ያከብረዋል ከፍ ከፍም ያደርገዋል። በክርስቶስ በኩል

ያገኘነውን አስደናቂ ድነት፣ የጌታን ፍፁምነትና ፅድቁን የሚገልፅልን ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢየሱስ ሲናገር «ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል» አለ (ዮሐ. 16፡14)። መለኮታዊ እውነትን ሊገልፅልን የሚችል ብቸኛ እና ብቁ አስተማሪ የእውነት መንፈስ ነው። ኦ እግዚአብሔር ለኛ ለሰዎች የሰጠው ዋጋ ምን ያህል ትልቅ ነው! አንድያ ልጁን ለኛ ሲል እንዲሞት አድርጎ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የእኛ አስተማሪ እና የማያቋርጥ መሪ እንዲሆን ያደረገልን!

# ምዕራፍ 11 - የጸሎት በረከት

እግዚአብሔር በፈጠረው ተፈጥሮ፣ በቃሉ፣ እንዲሁም በፍቅር እንክብካቤውና በመንፈሱ አማካይነት በሚያሳድረው ተጽእኖ ይናገረናል። እነዚህ ግን በቂ አይደሉም። እኛ ደግሞ ልባችንን በፊቱ ማፍሰስ ያስፈልገናል። መንፈሳዊ ህይወትና ብርታት እንዲኖረን ከፈለግን፣ ከሰማያዊ አባታችን ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። አሳባችን ወደ እርሱ ሊሳብ ይችል ይሆናል፤ ስለ እጁ ስራዎች፣ ስለ ምህረቱ፣ ስለባርኮቱ እናሰላስል ይሆናል፤ በዚህ ብቻ ግን ከእግዚአብሔር ጋር በሙላት ተገናኝተናል ለማለት አይቻልም። ከዚህ በተጨማሪ፣ ስለ አለንበት ትክክለኛ ሁኔታ ለእርሱ የምንናገረው ነገር ሊኖረን ይገባል።

ለወዳጅ የልብን እንደሚያጫውቱ ጸሎትም ለእግዚአብሔር የልብን ማጫወት ነው። የምንጸልየው ስለ እኛ ሁኔታ ለእግዚአብሔር የሚያውቀውን መረጃ ለመስጠት ሳይሆን፣ እርሱን በልባችን ለመቀበል እንዲያግዘን ነው። ጸሎት እግዚአብሔርን ወደ እኛ አያወርደውም፤ ነገር ግን እኛን ወደ እርሱ ከፍ ያደርገናል።

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው አስተማራቸው። እለታዊ ፍላጎታቸውን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዲያቀርቡና የሚያስጨንቃቸውን ሁሉ በእርሱ ላይ እንዲጥሉት መራቸው። ልመናቸው እንደሚሰማ የሰጣቸው ዋስትና ለእኛም ጭምር ነው።

ኢየሱስ ራሱ በሰዎች መካከል በኖረ ጊዜ ጸሎትን አዘውትሮ ተለማምዶአል። አዳኛችን ፍላጎቶቻችንንና ድካማችንን ተጋርቶ ስለነበር፣ ስራውን ለመስራትና ፈተናን ለመጋፈጥ እንዲችል አባቱ ጥንካሬ እንዲሰጠው ይለምን ነበር። እርሱ በሁሉ ነገር ምሳሌያችን ነው። «በሁሉ እንደእኛ የተፈተነ» ወንድማችን ሲሆን ምንም ኃጢአት የሌለበትና ስብዕናውም ለኃጢአት ጀርባውን የሰጠ ነበር። በኀጢአት በተሞላች ዓለም ውስጥ ያለውን ትግልና የነፍስ ስቃይ በትእግስት አልፎታል። ከለበሰው ሰብአዊ ተፈጥሮ የተነሳ ጸሎት ለእርሱ አስፈላጊና ደግሞም የበረከት ምንጭ ነበር። ከአባቱ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ደስታና መጽናናትን ያገኝ ነበር። ታዲያ የሰው ልጆች አዳኝ ለሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ጸሎት እንዲህ ካስፈለገው፣ ደካማና ሟች ለሆኑት

ኀጢአተኛ ፍጡራን ምን ያህል በበለጠ ብርቱና ፕሚ ጸሎት ያስፈልጋቸው ይሆን!

ለወዳጅ የልብን እንደሚያጫውቱ፣ ጸሎትም ለእግዚአብሔር የልብን ማጫወት ነው።

በሰማይ ያለው አባታችን የበረከቱን ሙላት በእኛ ላይ ሊያወርድ እየተጠባበቀ ይገኛል። ወሰን ከሌለው የፍቅር ምንጭ የፈለግነውን ያህል የመጠጣት መብት ተሰጥቶናል። ታዲያ ከዚህ የከበረ ዕድል አንጻር ሲታይ፣ በትንሹ መጸለያችን እንዴት የሚገርም ነው! እግዚአብሔር ከልጆቹ መካከል በጣም የደካማውን ሰው ልባዊ ጸሎት እንካDን ለመስማት ፈቃደኛና ዝግጁ ነው። ይህም ሆኖ ግን ፍላጎቶቻችንን በእግዚአብሔር ዘንድ ለማቅረብ ብዙ ስንፍና ተጠናውቶናል። ወሰን በሌለው ፍቅር የተሞላው

የእግዚአብሔር ልብ ከጠየቁት ወይም ከሚያስቡት ሁሉ በላይ ሊባርካቸው እጅግ Õጉቶ ሳለ፣ በትንሹ ብቻ ስለሚጸልዩትና እምነታቸውም ደካማ ስለሆነው ለፈተና ስለተጋለጡት፣ ምስኪንና ረዳተቢስ የሰው ልጆች መላእክት ምን ያስቡ ይሆን;
መላእክት በእግዚአብሔር ፊት መስገድ ይወዳሉ፤ ወደ እርሱም መጠጋት ደስታቸው ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግን እንደ ትልቅ ባርኮት ነው የሚቆጥሩት፤ እግዚአብሔር ብቻ የሚሰጠው እርዳታ በጣም የሚያስፈልጋቸው ምድራዊ ልጆች ግን ያለ የእግዚአብሔር መንፈስ ብርሃንና፣ ያለ ጌታ አጀብ መንገዳቸውን በማድረግ የረኩ ይመስላሉ።

መጸለይን ቸል የሚሉ ሁሉ የክፉው ጨለማ ይከብባቸዋል። የጠላት የፈተና ሹክሹክታ

ወደ ኃጢአት ይመራቸዋል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ታዲያ እግዚአብሔር በጸሎት ውስጥ ያስቀመጠውን በረከት ስላልተጠቀሙበት ነው። ጸሎት የሁሉን ቻይ አምላክ ወሰን የለሽ ሀብት የተከማቸበትን የሰማይ ግምጃ ቤት ለመክፈት የሚያስችል በእምነት እጅ ውስጥ የሚገኝ ቁልፍ ሆኖ ሳለ፣ ለምድን ነው የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ለመጸለይ የሚሰንፉት; ያለ ጽኑ ጸሎትና በትጋት የተሞላ ንቃት በይበልጥ ግዴለሽ እየሆንንና ከትክክለኛው መስመር እየወጣን ለመሄድ እንዳረጋለን። ከሳሻችን ወደ ጸጋው ዙፋን ቀርበን ፈተናውን ለመSSም የሚያስችለንን ጸጋና ኃይል እንዳናገኝ መንገዳችንን ሁልጊዜ ሊያጥርብን ይፈልጋል።

እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዲሰማና እንዲመልስ ስንጠባበቅ በቅድሚያ ልናሟላቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ። ከእነዚህ መካከል አንደኛው ከእርሱ ዘንድ እርዳታ እንደሚያስፈልገን መረዳት ነው። #በተጠማ ላይ ውኃን በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈስሳለሁና$ (ኢሳ. 44፡3) በማለት አምላካችን ተስፋ ሰጥቶናል። ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ እንዲሁም እግዚአብሔርን የሚናፍቁ ሁሉ እንደሚረኩ እርግጠኛ መሆን ይችላሉ። ለመንፈስ ቅዱስ አሰራር ልብ ክፍት ሊሆን ይገባል፤ አልያ የእግዚአብሔርን ባርኮት መለማመድ አይቻልም።

በውስጣችን ያለው የጎዶሎነት ስሜት ራሱ እኛን በመወከል ከአምላክ እርዳታ እንደሚያስፈልገን ጥሪውን በግልጽ መንገድ

ያስተጋባል። እንደዚያም ቢሆን፤ እነዚህን የጎደሉንን ነገሮች ያሟላልን ዘንድ እግዚአብሔርን ልንፈልገው ይገባል። #ለምኑ ይሰጣችኋል$ #ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም;$ ማቴ. 7፡7፤ ሮሜ. 8፡32።

ከፋትን በልባችን ከሰወርን፣ የሙጢኝ ያልነው የታወቀ ኀጢአት ካለ፣ እግዚአብሔር አይሰማንም። ስለ ኃጢአቱ የሚናዘዘውንና ራሱን የሚያዋርደውን ነፍስ ጸሎት ግን ጌታ ሁልጊዜ ይቀበላል። የምናውቃቸውን የተበላሹ ነገሮቻችንን ስናስተካክል፣ እግዚአብሔር ደግሞ ልመናችንን እንደሚሰማ ልናምን እንችላለን። የእኛ መልካም ሥራ መቼም ቢሆን በእግዚአብሔር

ፊት ሞገስ እንድናገኝ አያደርገንም። የሚያድነን የክርስቶስ ብቃት ነው፤ የሚያነጻንም ደሙ ነው። ነገር ግን እነዚህን ነገሮች የራሳችን አድርገን በመቀበል ረገድ ልንሰራው የሚገባን ስራ አለ።

የብርቱ ጸሎት ሌላው ባሕርይ ደግሞ በእምነት የሚጸለይ መሆኑ ነው። #ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።$ (ዕብ. 11፡6)። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፡- #የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል።$ (ማር. 11፡24)። እኛስ ጌታን እንደቃሉ እንቀበለዋለን;

ቃል ኪዳኑ ሰፊና ወሰን የለሽ ነው፤ ቃል የገባውም የታመነ ነው። የጠየቅነውን ነገር፣ በጠየቅነው ጊዜ ማግኘት ሳንችል ብንቀር እንካD፣ ጌታ ጸሎታችንን እንደሰማና ደግሞም እንደሚመልሰው ማመናችንን መቀጠል አለብን። አርቀን የማናይና በቀላሉም የምንስት ከመሆናችን የተነሳ፣ አንዳንዴ ሊባርኩን የማይችሉ ነገሮችን እንጠይቃለን። ይሁን እንጂ የሰማዩ አባታችን ለጸሎታችን መልስ አድርጎ በፍቅሩ የሚሰጠን፣ የነገሮችን ትክክለኛ ምንነት ማየት የምንችልበትን መለኮታዊ ማስተዋል ቢሰጠን ኖሮ የምንመርጠውን፣ እጅግ የሚጠቅመንን ነገር ብቻ ነው። ጸሎታችን ያልተመለሰ ሲመስለን፣ የሚመለስበት ጊዜ በእርግጥ ይመጣልና፣ የተስፋውን ቃል ልንጠማጠም ይገባል። በጣም የሚያስፈልገንን ባርኮትም እንቀበላለን።

በጸሎት እኛ የምንፈልገው ነገር ሁሉ በምንፈልገው መንገድ መልስ ያገኛል ብሎ ማሰብ አጉል ምኞት ነው። እግዚአብሔር ጥበቡ ጥልቅ ነውና አይሳሳትም፤ መልካምነቱም ታላቅ ነውና በቅንነት ለሚመላለሱት ምንም መልካም ነገር አያጎልባቸውም። እንግዲያውስ ለጸሎታችሁ አፋጣኝ ምላሽ ባታዩም እንካDን በእርሱ ለመታመን አትፍሩ። «ጠይቁ ይሰጣችኋDል» በሚለው የታመነው የተስፋ ቃሉ ተደገፉ። ከጥርጣሬያችንና ከፍርሃታችን ጋር ብንማከር፣ ወይም ያለእምነት በትክክል ልናያቸው የማንችላቸውን ነገሮች ሁሉ ለመፍታት ብንታገል፣ ጭንቀታችን እየጨመረና እየጠነከረ ከመሄድ ውጪ ሌላ የሚሆን ነገር አይኖርም። ነገር ግን ረዳተቢስ እንደሆንንና ድጋፍ እንደሚያስፈልገን በመረዳት ራሳችንን በማዋረድ፣ እውቀቱ

ወሰን ለሌለው፣ በፍጥረተ ዓለም ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ ለሚያየው፣ በፈቃዱና በቃሉ ሁሉን ለሚያስተዳድረው ለእግዚአብሔር በእምነት የሚያስፈልገንን ነገር ብናቀርበው ጩኸታችንን ሊሰማ ይችላል፤ ደግሞም ይሰማል፤ በልባችንም ላይ ብርሃን ያበራል። ልባዊ በሆነ ጸሎት ወሰን የለሽ ከሆነው መለኮታዊ አእምሮ ጋር እንገናኛለን። የአዳኛችን ፊት በርህራሄና በፍቅር ወደ እኛ የዞረ ላይመስለን ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን ፊቱ ወደ እኛ ዞሮአል። የእጆቹ መዳሰስ ላይሰማን ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን በሃዘኔታና በፍቅር እጆቹን በእኛ ላይ ጣል አድርጎአል።

ጸሎታችን ያልተመለሰ ሲመስለን፣ የሚመለስበት ጊዜ በእርግጥ ይመጣልና፣ የተስፋውን ቃል ልንጠማጠም ይገባል።

ከእግዚአብሔር ምህረትንና ባርኮትን ለመጠየቅ ስንቀርብ፣ በልባችን የፍቅርና የይቅርባይነት መንፈስ ሊኖረን ይገባል። «እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን» በማለት እየጸለይን፣ ይቅር የማይል መንፈስ እንዴት ሊኖረን ይችላል; የእኛ ጸሎት እንዲሰማ የምንፈልግ ከሆነ እኛ ይቅር ለመባል በምንፈልገው መንገድና በዚያው መጠን ይቅር ልንል ይገባል።

በትእግስት መጽናት በጸሎት ጠይቆ ለመቀበል ሌላው በቅድሚያ ልናሟላው የሚገባ ነገር ነው። በእምነትና በተሞክሮ ለማደግ ሁልጊዜ መጸለይ ያስፈልገናል። «በጸሎት ጽኑ» (ሮሜ. 12፡ 12)፤ «በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ።» (ቆላ. 4፡2) ጴጥሮስ ደግሞ አማኞችን «በጸሎት ንቁ…»

ይላል። (1ጴጥ. 4፡7) «በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።» (ፊል. 4፡6) በማለት ጳውሎስ ያዛል። ይሁዳ ደግሞ እንዲህ ይላል፦ «እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፥ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ።» ይሁዳ 20፣21። ሳያSCርጡ መጸለይ ማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ ህይወት ወደ ህይወታችን እንዲፈስና ከእኛም ህይወት ደግሞ ንጽሕናና ቅድስና ወደ እርሱ መልሶ እንዲፈስ ከአምላክ ጋር ነፍስን ማቆራኘት ማለት ነው።

በጸሎት መትጋት በእጅጉ ያስፈልገናል። ይህንንም ከማድረግ ምንም ነገር አያደናቅፋችሁ። በነፍሳችሁና በኢየሱስ መካከል ክፍት የሆነ የግንኙነት መስመር ዘወትር እንዲኖር በማድረግ የሚገባችሁን ሁሉ አድርጉ። ጸሎት ወደ ሚደረግበት ስፍራ ለመሄድ እያንዳንዱን ዕድል ተጠቀሙበት። ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት ማድረግ የሚፈልጉ ሁሉ ተግባራቸውን በታማኝነት ለመፈጸምና ሊያገኙ የሚችሉትን ባርኮቶች በትጋትና በጉጉት ለመሰብሰብ ዝግጁዎች ሆነው በጸሎት ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋሉ። የሰማይ ብርሃን ጨረር ሊያገኙ ወደሚችሉበት ስፍራ ራሳቸውን ለማስቀመጥ የሚረዳቸውን ዕድል ይጠቀሙበታል።

በነፍሳችሁና በኢየሱስ መካከል የማያቋርጥ የግንኙነት መስመር እንዲኖር በማድረግ የሚገባችሁን ሁሉ አድርጉ።

በቤተሰብ የጸሎት ጊዜ ሊኖረን ይገባል፤ ከሁሉም በላይ ግን በግል በስውር የምንጸልየውን ጸሎት ቸል ልንለው አይገባም፤ የነፍስ ህይወት ያለው በዚያ ነውና። ጸሎት ቸል ተብሎ ነፍሳችን ፈጽሞ ሊያብብ አይችልም። የቤተሰብ ወይም የጉባዔ ጸሎት ብቻውን በቂ አይደለም። ለብቻችን በመሆን ሁሉን ለሚመረምሩት የእግዚአብሔር ዓይኖች ህይወታችንን መገላለጥ ያስፈልጋል። የምስጢር ጸሎታችን የሚሰማው ጸሎት ሰሚ በሆነው አምላክ ብቻ ነው። እንደዚያ ያለውን የልብ ሸክም የትኛውም ለማወቅ የሚÕÕ ጆሮ ሊሰማው አይችልም። በስውር ጸሎት ነፍስ በዙሪያዋ

ከከበባት ተጽእኖና ከስሜታዊነት ነጻ ትወጣለች። በእርጋታ፣ ግን በግለት እግዚአብሔርን መቅረብ ይቻላል። በስውር ያለውን ከሚያየውና ጆሮውም ከልብ የሚጸለየውን ጸሎት ለመስማት ልቡ ከተከፈተው አምላክ ጣፋጭና ለዘለቄታው ከእኛ ጋር የሚቆይ እርዳታ እናገኛለን። በዚህም ነፍስ ከሰይጣን ጋር ለምታደርገው ተጋድሎ የሚያጠነክራትና የሚያዘልቃትን ሰማያዊ የብርሃን ጨረር በእምነት ትሰበስባለች። እግዚአብሔር የጥንካሬያችን ምንጭ ነው።

በÕዳችሁ ጸልዩ፤ ወደ ዕለት ተግባራችሁ ስትሰማሩም ልባችሁ ወደ እግዚአብሔር ያለማˢረጥ የሚያቀና ይሁን። ሔኖክ ከእግዚአብሔር ጋር የተራመደው በዚህ ሁኔታ ነበር። በስውር የምንጸልያቸው

ጸሎቶች በእግዚአብሔር የጸጋ ዙፋን ፊት እንዳለው የከበረ እጣን ናቸው። ልቡ ከእግዚአብሔር ጋር የተቆራኘን ሰው ሰይጣን ሊያሸንፈው አይችልም።

ለእግዚአብሔር ልመናችንን ለማቅረብ የማንችልበት ጊዜ ወይም ቦታ የለም። በእውነተኛ ጸሎት ልባችንን እንዳናፈስ የሚከለክለን ምንም ነገር የለም። በመንገድ ላይ ከተሰበሰበ ህዝብ መሃል ሆነን፣ ወይም በስራ ተጠምደን ባለንበት ሁኔታም ቢሆን ነህምያ በንጉስ አርጤክሰስ ፊት መጠይቁን ሲያቀርብ እንዳደረገው፣ እኛም እግዚአብሔር መለኮታዊ ምሪት እንዲሰጠን ልንጠይቀው እንችላለን። በየትኛውም ቦታ ብንሆን በስውር የምንጸልይበትን ዕድል ልናገኝ እንችላለን። የልባችን በር ዘወትር የተከፈተና ኢየሱስም እንደ ሰማያዊ እንግዳ

ሆኖ በነፍሳችን እንዲኖር ያለማsረጥ ልናድመው ይገባል።

ምንም እንካDን ኃጢአት በበከለው ከባቢ አየር ውስጥ የምንኖር ብንሆንም ቆሻሻውን መተንፈስ ግን አያስፈልገንም። በሰማያዊው ከባቢ አየር ውስጥ መኖር እንችላለን። ልባዊ በሆነ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ህልዎት (መገኘት) ራሳችንን ከፍ በማድረግ ወደ ምናባችን የሚመጡትን ርኩስ ነገሮችና በኃጢአት የተበከሉ አስተሳሰቦችን እንዳይገቡ በር መዝጋት እንችላለን። የእግዚአብሔርን እገዛና በረከት ለመቀበል የሚፈቅዱ ሁሉ፣ በቅድስና ከባቢ አየር ውስጥ ይመላለሳሉ፤ ከሰማይም ጋር sሚ ግንኙነት ይኖራቸዋል።

ስለ ኢየሱስ ልዩ የሆነ መረዳትና ስለ ዘላለማዊ እውነታዎች ዋጋ ሙሉ መረዳት

ያስፈልገናል። የቅድስና ውበት የእግዚአብሔር ልጅን ልብ ሊሞላው ይገባል። ይህም ተግባራዊ እንዲሆን የሰማያዊ ነገሮች መለኮታዊ መገለጥ እንዲኖረን መጸለይ አለብን።

ሰማያዊውን ከባቢ አየር መተንፈስ የሚያስችለውን መለኮታዊ ኃይል ከጌታ ለመቀበል እያንዳንዱ ነፍስ ወደ እርሱ መጠጋት አለበት። ወደ እግዚአብሔር በጣም ተጠግተን ስንኖርና ያልጠበቅነው መከራና አሳብ ሁሉ ሲመጣ፣ ልክ የሱፍ አበባ ወደ ጸሐይ ፊቱን እንደሚያዞር እኛም ወደ ሚረዳን ጌታ እንሮጣለን።

ፍላጎታችሁን፣ ደስታችሁን፣ ሃዘናችሁን፣ ጭንቀታችሁን ወይም ፍርሃታችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡት።

የማይችለውን ሸክም በእርሱ ላይ ልትጭኑበት አትችሉም፤ ልታደክሙትም አትችሉም። የራስ ጠጉራችሁን የቆጠረው እርሱ ስለ ልጆቹ ጉዳይ ፈጽሞ ግዴለሽ አይሆንም። «ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና።» ያዕ. 5፡11። የፍቅር ልቡ በሰቆቃችንና ስለ ኀዘናችን በምንናገረው ነገር ይነካል። አእምሮአችሁን የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ፊት አቅርቡት። ለእርሱ ለመሸከም የሚከብደው ምንም ነገር የለም፤ ምክንያቱም ዓለማትን ሁሉ በእጁ ይዞአልና፤ በዩንቨርስ ውስጥ ያለውንም ሁሉ የሚያስተዳድረው እርሱ ነው። ለእኛ ሰላም የሚጠቅመውን ማንኛውንም ነገር ቸል ብሎ አያልፍም። ለእርሱ ለማንበብ የሚያስቸግረው የጨለመ የህይወት ምዕራፍ የለንም፤ እርሱ ሊያስወግደው የሚከብደው ጭንቀትም

የለንም። የሰማይ አባታችን የማያየው ወይም የእርሱን ትኩረት የማይስብ ምንም አይነት መከራ ከልጆች መካከል ታናሽ በሆነው ላይ እንካD አይመጣም፤ ምንም አይነት ጭንቀት ነፍስን አያሰቃይም፤ እንዲሁም እርሱ የማያዳምጠውና ትኩረት የማይሰጠው አንድም እውነተኛ ጸሎት ከከንፈር አይወጣም። «ልባቸውን የቈሰሉትን ይፈውሳል፥ ሕማማቸውንም ይጠግናል።» መዝ. 147፡3። በእግዚአብሔርና በእያንዳንዳD ነፍስ መካከል ያለው ግንኙነት በጣም የግል እና የጠበቀ ከመሆኑም ባሻገር ይህ ግንኙነት በምድር ላይ የእርሱ ጥበቃ የሚያስፈልጋት ነፍስ አንድ ብቻ እንኳን ብትሆን ጥበቃውን ለእርሷ ለመለገስና የሚወደውን አንድያ ልጁን ለእርሷ ደህንነት ሲል ለመስጠት የሚያስችል አይነት ነው።

ኢየሱስ እንዲህ ብሎአል፡- #በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤ እናንተ ስለ ወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እኔ እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና።$ ፤ #እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፥ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ።$ ዮሐ. 16፡26-27፤ 15፡16። በኢየሱስ ስም መጸለይ ማለት ግን በጸሎታችን መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ስሙን እየጠሩ ከመጸለይ ያለፈ ትርጉም አለው። የተስፋውን ቃል በማመን፣ በጸጋው ላይ በመደገፍና ስራውን በመስራት በኢየሱስ አእምሮና መንፈስ መጸለይ ማለት ነው።

እግዚአብሔር እርሱን እናመልከው ዘንድ ከዓለም ውስጥ ወጥተን እንድንመነኩስ አሳቡ አይደለም። ሕይወታችን ልክ እንደ ኢየሱስ ሊሆንልን ይገባል፤ እርሱ ለጸሎት ወደ ተራራ ይወጣ ነበር፤ ለማገልገል ደግሞ ከህዝቡ ጋር ይቀላቀል ነበር። ከመጸለይ ውጪ ሌላ ምንም የማያደርግ ሰው ፈጥኖ መጸለዩን ይተዋል፤ ወይም ጸሎቱ ዘልማዳዊ ብቻ ይሆናል። ሰዎች ከማህበራዊ ህይወት ሲገለሉ፣ ከክርስትና ተግባርና መስቀልን ከመሸከም ሲሸሹ እንዲሁም ስለ እነርሱ ለተጋው ጌታ መትጋት ሲያቆሙ የጸሎትን ፍሬ ነገርና ለመጸለይ የሚያነቃቃቸውን ነገር ያጣሉ። ጸሎታቸው በራስወዳድነት የተሞላ ይሆናል። ስለ ሰብአዊ ፍጥረት ፍላጎት ወይም ስለ ክርስቶስ መንግስት መSSም፣ ለመንግስቱም መስራት እንዲችሉ ኃይል ለመቀበል መጸለይ አይችሉም።

በእግዚአብሔር አገልግሎት ውስጥ በመሳተፍ እርስ በርስ የመደፋፈርንና የመበረታታትን በረከት ቸል ስንል ለውድቀት እንዳረጋለን። የቃሉ እውነት በአእምሮአችን ውስጥ ግልጽነቱንና አስፈላጊነቱን ያጣል። ልባችን ቀዳሽ በሆነው ኃይል መነቃቃቱ ያቆማል፤ በመንፈሳዊ ህይወታችን ውድቀት ይገጥመናል። ከሌሎች ክርስትያኖች ጋር ባለን ግንኙነት ለሌሎች መራራት ባለመቻል ኪሳራ ያጋጥመናል። ራሱን ከሌሎች የሚያገል ሁሉ፣ እግዚአብሔር ለእርሱ ባቀደው ዓላማ እየኖረ አይደለም። ማህበራዊ ተፈጥሮአችንን በምናጎለብትበት ጊዜ ለሌሎች ሰዎች በመራራት እግዚአብሔርን ስናገለግል ጥንካሬ እንዲኖረን ያደርገናል።

ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ጥሩ ግንኙነት ቢኖራቸውና የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲሁም የመዳንን የከበሩ እውነቶች ቢነጋገሩ፣ የራሳቸው ልብ ይታደሳል፤ እርስ በርስም መተናነጽ ይችላሉ። በየዕለቱም ስለ ሰማያዊ አባታችን አዳዲስ መረዳቶችን እያገኘን እንሄዳለን። ስለ ፍቅሩም የመናገር ዝንባሌያችን ይጨምራል። ይህንንም ስናደርግ የራሳችን ልብ ይሞቃል፤ ደግሞም እንበረታታለን። ስለ ራሳችን ቀንሰን ስለ ኢየሱስ ብዙ ብናስብና ብናወራ የእርሱን ህልዎት (መገኘት) አብዝተን እንለማመድ ነበር።

እርሱ ለእኛ እንደሚጠነቀቀው ያህል እኛ እርሱን ብናስበው፣ ሁል ጊዜ እርሱን ባሰብነውና ከእርሱም ጋር ማውራትና እርሱን ማመስገን ደስታችን በሆነ ነበር። ነገር

ግን ትኩረታችንን በእነርሱ ላይ አሳርፈናልና ጊዜያዊ ስለሆኑ ነገሮች ስናወራ እንደመጣለን። ወዳጆቻችንን ስለምንወዳቸው ስለ እነርሱ መናገር ደስ ይለናል። ደስታችንንም ሆነ ሀዘናችንን ከእነርሱ ጋር እንካፈላለን። ነገር ግን ከምድራዊ ወዳጆቻችን አስበልጠን እግዚአብሔርን የምንወድበት ብዙ ምክንያት አለን። ከዚህም የተነሳ እርሱን ከሌሎች ነገሮች ሁሉ በላይ መጀመሪያ ማድረግ፣ ስለ እርሱ መልካምነትና ኃይል ማውራት ተፈጥሮአችን ሊሆን ይገባ ነበር። እግዚአብሔር የሰጠን ብዙ ባርኮቶች አሳባችንንና ፍቅራችንን ሙጥጥ አድርገው በመውሰድ፣ ሰጪውን እንድንረሳ ሊያደርጉን አይገባም። ይልቁንም ከሰማያዊ ረድኤታችን ጋር በፍቅርና በአመስጋኝ መንፈስ ሊያስተሳስሩን ስለ እርሱም ያለማቋረጥ

ሊያስታውሱን የተሰጡን ናቸው። እየኖርን ያለነው በምድር አዘቅት ውስጥ ነው። ዓይናችንን አንስተን ወደ ተከፈተው ሰማያዊ መቅደስ ደጅ እንመልከት። በዚያም «በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊድናቸው በሚችለው» ዕብ. 7፥ 25 በኢየሱስ ላይ የእግዚአብሔር ክብር ሲያጸባርቅበት እናያለን።

እግዚአብሔርን ማምለክና በእርሱም ሥራ ውስጥ ድርሻ ማግኘት እንደ ትልቅ ደስታ ልንቆጥረው የሚገባ ነገር ነው።

እግዚአብሔርን «ለሰው ልጆች ስላደረገው ተኣምራት ስለ ምሕረቱም» (መዝ. 107፥8) ልናመሰግነው ይገባል። የአምልኮ ህይወታችን በመጠየቅና በመቀበል ላይ ሊወሰን አይገባም። ሁልጊዜ ስለ ጎደሉን ነገሮች ብቻ በማሰብ

የተቀበልናቸውን ባርኮቶች አንርሳ። በምስጋና አፋችንን ሳንከፍት ብዙ ልንጸይ አንችልም። የእግዚአብሔርን ምህረት ያለማቋረጥ እየተቀበልን በምላሹ የምንሰጠው ምስጋና ግን ምን ያህል በጣም ትንሽ ነው!

ጥንት እስራኤላዊያንን ጌታ ለአምልኮ ሲሰበሰቡ እንዲህ ያደርጉ ዘንድ አዘዛቸው፡- «እጃችሁንም በምትዘረጉበት፥ አምላክህ እግዚአብሔር በባረከህ ነገር ሁሉ፥ እናንተና ቤተሰባችሁ ደስ ይበላችሁ።» ዘዳ. 12፡7። ለእግዚአብሔር ክብር የምናደርገው ነገር ሁሉ በደስተኛ ስሜት፣ በውዳሴ ዝማሬና በምስጋና እንጂ በኀዘንና በጠቆረ ፊት መሆን የለበትም።

አምላካችን ሩህሩህና መሐሪ አምላክ ነው። ለእርሱ የሚደረግ አገልግሎት ልብን በሐዘን

የሚሞላ፣ አስጨናቂ ልምምድ ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም። እግዚአብሔርን ማምለክንና በእርሱም ስራ ውስጥ ድርሻ ማግኘትን እንደ ትልቅ ደስታ ልንቆጥረው የሚገባ ነገር ነው። እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ መዳን ያዘጋጀላቸው ልጆቹ እርሱን እንደ ጨካኝና አምባገነን ጌታ አድርገው እንዲቆጥሩት አይፈልግም። እርሱ የቅርብ ወዳጃቸው ነው። በሚያመልኩትም ጊዜ ከእነርሱ መካከል በመገኘት ሊባርካቸውና ሊያጽናናቸው እንዲሁም ልባቸውን በደስታና በፍቅር ሊሞላ ይፈልጋል። ጌታ ልጆቹ እርሱን በማገልገላቸው ብዙ መጽናናት እንዲያገኙና ከችግር ይልቅ ደስታን እንዲለማመዱ ይፈልጋል። እርሱን ለማምለክ የሚመጡ ሰዎች ሁሉ፣ ስለ እርሱ ጥንቃቄና ፍቅር የከበሩ አሳቦችን ይዘው እንዲመለሱ በየዕለት ተግባራቸውም

ደስተኞች እንዲሆኑ፣ በነገር ሁሉ በእውነተኝነትና በታማኝነት መጋፈጥ የሚችሉበትን ጸጋ እንዲያገኙ ይፈልጋል። በመስቀሉ ዙሪያ ልንሰበሰብ ይገባናል። ክርስቶስና ስቅላቱ በአእምሮአችን የምናስበው ነገር፣ የንግግራችን፣ እንዲሁም የደስታችን ሁሉ ማእከል ሊሆኑ ይገባል። ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸውን መልካም ስጦታዎች ሁልጊዜ ማስታወስ ያስፈልገናል። ፍቅሩንም ስናስተውል በመስቀል ላይ ስለ እኛ በተቸነከሩት የጌታ እጆች ላይ ሁሉንም ነገራችንን ለማስረከብ ፈቃደኞች እንሆናለን። ነፍስ በምስጋና ክንፍ ወደ ሰማይ ትበራለች። በላይ በሰማይ አደባባዮች እግዚአብሔር በመዝሙርና በሙዚቃ ይመለካል። እኛ ደግሞ በዚህ ምድር ላይ ምስጋናችንን በመግለጥ ስናመልክ የሰማይ ሠራዊትን አምልኮ እየተጠጋን እንሄዳን።

«ምስጋናን የሚሰዋ ሁሉ» እግዚአብሔርን ያከብራል። መዝ. 50፡ 23። «በምስጋናና በዜማ ድምጽ» በአክብሮት በተሞላ ደስታ ወደ ፈጣሪያችን እንቅረብ። ኢሳ. 51፡3።

# ምዕራፍ 12 - ጥርጣሬን ማሸነፍ

ብዙዎች በተለይም በክርስትናቸው ገና ለጋ የሆኑ ሰዎች ከተጠራጣሪዎች በሚሰነዘሩ አስተያየቶች ይደነግጣሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊያብራሩዋቸው ይቅርና ሊያስተውሉዋቸው የማይችሉ ብዙ ነገሮች ያሉ ሲሆን ሰይጣን ደግሞ እነዚህን በመጠቀም ቅዱሳት መጻሕፍት ከእግዚአብሔር የተሰጡ መገለጦች እንደሆኑ ያላቸውን እምነት ሊናውጠው ይፈልጋል። እንዲህም በማለት ይጠይቃሉ፡- «ትክክለኛውን መንገድ የማውቀው እንዴት ነው; መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥ የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ ከእነዚህ ጥርጣሬዎች መላቀቅ የምችለው እንዴት ነው;»

እግዚአብሔር እምነታችንን ለመመስረት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ሳይሰጠን እንድናምን ፈጽሞ አይጠይቀንም። ህልውናው፣ ባህሪይው፣ የቃሉ እውነተኛነት ለአእምሮአችን አጥጋቢ በሆኑ ምስክሮች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ሆኖም ግን የጥርጣሬ በሮችን ሁሉ አልዘጋም። እምነታችን በማስረጃዎች ላይ እንጂ በተገለጡ ነገሮች ላይ መመስረት የለበትም። መጠራጠር የሚፈልጉ ሰዎች አጋጣሚውን ያገኛሉ። በአንጻሩ ደግሞ እውነትን ለማወቅ ከልባቸው የሚመኙ ሰዎችም እምነታቸውን ለመመስረት በቂ ማስረጃ ያገኛሉ።

ወሰን የለሽ የሆነውን ጌታ ባህሪይና ስራ ውስን በሆነው አእምሮአችን በሙላት ለማስተዋል መሞከር ፈጽሞ የማይታሰብ ነው። እጅግ በከፍተኛ ደረጃ የተማረና የረቀቀ

እውቀት ካለው ሰብአዊ ፍጥረት እንኳን ሳይቀር እግዚአብሔር በምስጢር ካባ ተሸፍኖአል። «የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክን ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን? ከሰማይ ይልቅ ከፍ ይላል፤ ምን ልታደርግ ትችላለህ? ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ ትችላለህ?» ኢዮብ 11፡7-8።

ጳውሎስ ደግሞ እንዲህ ይላል፡- «የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም።» ሮሜ 11፡33። «ደመና ጭጋግም በዙሪያው ናቸው፤ ጽድቅና ፍርድ የዙፋኑ መሠረት ናቸው።» መዝ. 97፡2። ከእኛ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት፣

እንዲሁም ከድርጊቶቹ በስተጀርባ በሚገኘው መነሻ ምክንያት ውስጥ ፍቅርና ምህረት ወሰን ከሌለው ኃይል ጋር ተቆራኝተው እናያለን። ለእኛ ለማወቅ የሚጠቅመንን ያህል የእርሱን ዓላማዎች ለማስተዋል እንችላለን። ነገር ግን ከዚያ ውጪ ስለሆነው ነገር ሁሉን ቻይ በሆኑት በጌታ ክንዶችና በፍቅር በተሞላው ልቡ ላይ ልንደገፍ ይገባናል።

የእግዚአብሔር ቃል ልክ እንደ መለኮታዊ ደራሲው ውስን በሆኑት ፍጥረታት በሙላት ሊስተዋሉ የማይችሉ ሚስጢሮችን ይዞአል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት የኃጢአት ወደ ዓለም መግባት፣ የክርስቶስ ስጋ መልበስ፣ ዳግም መወለድ፣ ትንሳኤ፣ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ርእሶች ለሰብአዊ

ፍጡር አእምሮ ለማስረዳትም ሆነ በሙላት ለመረዳት የሚያዳግቱ ምስጢራት ናቸው። ሆኖም ግን የአሰራሩን ምስጢር ማስተዋል ስላልቻልን፣ የእግዚአብሔርን ቃል የምንጠራጠርበት ምክንያት ሊሆነን አይችልም። በምድራዊው ህይወታችን በብዙ ምስጢራዊ ነገሮች ተከበናል። በጣም ትንሽ የምትመስለዋን ሕይወት፣ እጅግ ጠቢብ የተባለው ፈላስፋ እንኳን በሙላት ሊያብራራት አይችልም። በየቦታው ከማስተዋላችን በላይ የሆኑ አስደናቂ ነገሮች አሉ። ታዲያ በመንፈሳዊውስ ዓለም ከማስተዋላችን በላይ የሆኑ ነገሮችን በማግኘታችን ልንደነቅ ይገባልን; ችግሩ ያለው ደካማና ጠባብ ከሆነው ከሰው አእምሮ ነው። እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት ስለ መለኮታዊ ባሕርይው በቂ ማስረጃ ሰጥቶናል። በመሆኑም የአሰራሩን

ምስጢር በሙላት ስላልተረዳን ቃሉን ልንጠራጠር አይገባም።

ሐዋሪያው ጴጥሮስ ሲጽፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡- «ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፥ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ።» በማለት ይናገራል። 2 ጴጥ. 3፡16። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ለማስተዋል የሚቸግሩ ጥቅሶች ቃሉን የማያምኑት መጽሐፍ ቅዱስን ለማጣጣል የሚጠቀሙባቸው ቢሆንም ነገር ግን የበለጠ በቃሉ ላይ መታመንን የሚጨምሩ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር በቀላሉ የሚስተዋሉ ነገሮችን ብቻ ይዞ ቢሆን ኖሮ፣ የእግዚአብሔር ታላቅነት ግርማ ውስን በሆነው አእምሮአችን በቀላሉ ቢስተዋል ኖሮ፣ መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ምንጭ

ባልኖረው ነበር። የምስጢራት መኖር በራሱ በእግዚአብሔር ቃል ላይ እምነትን ሊጭርልን ይገባል። ቀለል ባለና ለሰብአዊ ፍጡር ፍላጎት ፍጹም ገጣሚ በሆነ መልኩ እውነትን የሚገልጠው መጽሐፍ ቅዱስ፣ የጠቢባንን አእምሮ ሲያስደንቅ፣ በምድራዊ እውቀት ብዙ ያልገፉትን ደግሞ የድነትን መንገድ ማስተዋል እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ሆኖም እነዚህ ቀለል ተደርገው የተገለጹት እውነታዎች ከፍ ያሉና በሰው አእምሮ ሊስተዋሉ ከማይችሉ ርእሶች ጋር የተያያዙ ስለሆኑ የምንቀበላቸው እግዚአብሔር ራሱ ስለተናገራቸው ብቻ ነው። በንስሓ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስና በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ማመን እንዲደርስ በዚህም በእግዚአብሔር መንገድ ይድን ዘንድ ለእያንዳንዱ ነፍስ የድነት እቅድ በግልጽ ተቀምጦአል። ነገር ግን ከእነዚህ በቀላሉ

ሊስተዋሉ ከሚችሉ እውነቶች ባሻገር የእግዚአብሔርን ክብር መሰወሪያ የሆኑና ለሰው አእምሮ ለማስተዋል የሚከብዱ ምስጢራት አሉ። እውነትን ፈላጊ ሰው ጠለቅ አድርጎ ቃሉን ሲያጠና እነዚህ ምስጢራት በህያው አምላክ ቃል ላይ ያለውን መታመን ይጨምሩለታል። እንደዚሁም ሰብአዊ አስተሳሰብ ሁሉ ለመለኮታዊው መረዳት እንዲንበረከክ ያደርጋሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስን ታላላቅ እውነቶች በሙላት ማስተዋል እንደማንችል መቀበል ማለት ውስን የሆነው አእምሮአችን ወሰን የለሹን በሙላት ሊይዘው እንዳልቻለ፣ ሰው ውስን በሆነው እውቀቱ ሁሉን አዋቂ የሆነውን ጌታ ዓላማ በሙላት መረዳት አለመቻሉን መቀበል ማለት ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስን ምስጢራት ሁሉ ማስተዋል ስላልቻሉ፣ ኃይማኖትን የሚክዱ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስንም አይቀበሉትም። መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን የሚሉ ሰዎች ሁሉም ከዚህ ችግር አያመልጡም። ሐዋርያው እንዲህ ይላል፦ «ወንድሞች ሆይ፥ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ፤» ዕብ. 3፡ 12። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እስተከተገለጡ ድረስ የቅዱሳት መጻሕፍትን አስተምህሮ መመርመርና «ወደ ጠለቀው የእግዚአብሔር ነገር» መግባት መልካም ነው። 1 ቆሮ. 2፡ 10። «ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም

ለልጆቻችን ነው።» ዘዳ. 29፡29።
የመመርመርን ኃይል ማዳከም የሰይጣን ስራ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ሲያጠኑ በሰዎች ልብ ውስጥ ትእቢትን በመዝራት እያንዳንዱን ጥቅስ እነርሱን በሚያረካቸው ደረጃ ማብራራት ካልቻሉ ሽንፈት እንዲሰማቸው ያደርጋል። በመንፈስ መሪነት የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል እንደማያስተውሉት አምኖ መቀበል ያሳፍራቸዋል። ያን እውነት እግዚአብሔር ለእነርሱ የሚገልጽበትን ጊዜ ለመጠበቅ ትእግስት የላቸውም። ቅዱሳት መጽሐፍትን ለማስተዋል ሰብአዊ ጥበባቸው ብቻውን በቂ ይመስላቸዋል። ይህንንም ማድረግ ሲያቅታቸው የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን ይክዳሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኙ የሚመስሉ ብዙ አስተምህሮዎችና መላምቶች ምንም አይነት መጽሐፍ

ቅዱሳዊ መሰረት የላቸውም፤ እንዲያውም የቃሉን ጭብጥ የሚቃወሙ ናቸው። እነዚህም ነገሮች ለብዙ አእምሮዎች የጥርጣሬ ምንጭ ሆነው ቆይተዋል። ነገር ግን ምንጫቸው እግዚአብሔር ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር የተነገረውን ነገር ያጣመሙ ሰዎች ናቸው። ስለ እግዚአብሔርና ስለ ስራዎቹ ሙሉ ማስተዋል በፍጡራን ዘንድ ማግኘት የሚቻል ቢሆን ኖሮ፣ ሌላ ተጨማሪ እውነት መረዳት፣ በእውቀት ማደግ እንዲሁም የአእምሮ መዳበር ባልኖሩ ነበር። እግዚአብሔርም ከሁሉ በላይ ባልሆነ ነበር። ሰውም የእውቀት ጣሪያ ላይ ደርሶ ከዚያ በላይ ማደግ ባልቻለ ነበር። ይህ ባለመሆኑ ግን እግዚአብሔርን እናመስግነው! እግዚአብሔር ወሰን የሌለው አምላክ ነው፤ «የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና።» ቆላ. 2፡3። እናም ሰዎች ስለ እርሱ

ጥበብ፣ መልካምነትና ኃይል ለዘላለም ይመረምራሉ፤ ይማራሉ፤ ነገር ግን አውቀው ሊጨርሱት አይችሉም።

የመጽሐፍ ቅዱስን ምስጢራት ሁሉ ማስተዋል ስላልቻሉ ተጠራጣሪዎችና ኃይማኖትን የሚክዱ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስንም አይቀበሉትም።

በዚህ ምድር ህይወታችንም ጭምር እግዚአብሔር የእውነቱን ብርሃን እየገለጠልን እንድንÕዝ ይፈልጋል። ይህ አይነቱ እውቀት የሚገኝበት መንገድ ደግሞ አንድ ብቻ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ማስተዋል የምንችለው ቃሉ በመጀመሪያ በተሰጠበት በመንፈስ ቅዱስ እገዛ ነው። «በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም

ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።» «መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።» 1 ቆሮ. 2፡11፣10። አዳኙ ለተከታዮቹ የሰጠው ተስፋ ደግሞ እንዲህ የሚል ነበር፡- «ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል ... ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና።» ዮሐ. 16፡ 13-14

የእግዚአብሔርን ቃል ማስተዋል የምንችለው ቃሉ በመጀመሪያ በተሰጠበት በመንፈስ ቅዱስ እገዛ ነው።

እግዚአብሔር ሰው የማገናዘብ ችሎታውን እንዲለማመድ ይፈልጋል፤ መጽሐፍ ቅዱስ

ማጥናት ደግሞ ከሌላ የትኛውም ጥናት በላይ የአዕምሮን ችሎታ ያጠነክራል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማስተዋል ከፈለግን ለመማር በተዘጋጀ መንፈስ፣ ሕፃናት በወላጆቻቸው ላይ ባላቸው አይነት እምነት፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እየጠየቅን መቅረብ ያስፈልገናል። የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል እንዲሁም ከእኛ ማስተዋል በላይ የሆነው ታላቅነቱ ራሳችንን እንድናዋርድና ቃሉንም በምንከፍትበት ጊዜ ልክ ወደ እርሱ መገኘት ውስጥ እንደምንገባ በመቁጠር በታላቅ አክብሮት እንድናጠናው ያነሳሳናል። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስንቀርብ አእምሮአችን ከእርሱ በላይ ስልጣን ላለው አምላክ እውቅና መስጠት እንዲሁም ልባችን ለታላቁ አምላክ መስገድ አለበት።

በአርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማስተዋል የሚቸግሩ ብዙ የተሰወሩ ነገሮች ቢኖሩም ማስተዋልን ለማግኘት ከእግዚአብሔር ጥበብን ለሚጠይቁ ሁሉ እርሱ የሰጣቸው ዝግጁ ነው። ነገር ግን ያለ መንፈስ ቅዱስ ምሪት ቅዱሳት መጻሕፍትን በስህተት ለማስተዋል ወይም ደግሞ ለማጣመም ሁልጊዜ የተጋለጥን እንሆናለን። ምንም ትርፍ የሌላው እንዲያውም ጉዳት የሚያመጣ የመጽሐፍ ቅዱስ አነባብ አይነት አለ። የእግዚአብሔር ቃል ያለ አክብሮትና ያለ ጸሎት ሲከፈት፣ አስተሳሰባችን በእግዚአብሔር ላይ ሳያነጣጥር ሲቀርና ከፈቃዱም ጋር ያልተስማማ ከሆነ፣ አእምሮአችን በጥርጣሬ ደመና ይከሰባል። በመሆኑም የዚህ አይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በውስጣችን ያለውን ጥርጣሬ የሰለጠ ያጠናክራል። ጠላት አስተሳሰባችንን

ሰመቆጣጠር የተሳሳቱ ትርጉሞችን (መረዳትን) . ያቀርብልናል። ሰዎች ሰቃልና በተግባር ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ለመፍጠር በማይፈልጉበት ጊዜ ሁሉ፤ ምንም ያህል አንኳን ጥሩ የትምህርት ደረጃ ቢኖራቸውም ስላ ቃሉ ባላቸው ግንዛቤ የሳቱ ይሆናሉ። በእንደዚህ አይነት ሰዎች አስተምሮ ላይ መደገፍ አስተማማኝ አይሆንም። ስህተትን ፍለጋ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነሱ ሰዎች ምንም አይነት መንፈሳዊ መረዳት አያገኙም። በተዛባ አይታቸውም ብዙ የጥርጣሬ እና የአላማመን ምክንያቶችን ይደረድራሉ። ቀላልና ግልጽ የሆኑትን እውነቶች አንኳን ሳይቀር ማመን ይሳናቸዋል።

ምንም እንካ ብንተሰውረውም ሆነ በአብዛኛው ያለማመንና የጥርጣሬ እውነተኛ

ምንጭ የኃጢአት ፍቅር ነው። የእግዚአብሔር ቃል አስተምህሮዎችና መመሪያዎች በትእቢት በተወጠረውና በኃጢአት ፍቅር በተነደፈው ልብ ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም። ትእዛዛቱንም ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ስልጣን ለመጠራጠር ዝግጁዎች ናቸው። ወደ እውነት ለመድረስ፣ እውነትን ለማወቅ እውነተኛ መሻትና ለመታዘዝም ፈቃደኛ የሆነ ልብ ያስፈልገናል። በዚህ መንፈስ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የሚቀርቡ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ በቂ መረጃ ያገኛሉ። ለመዳን የሚያበቃቸውንም የቃሉን እውነት መረዳት ይችላሉ።

ክርስቶስ እንዲህ በማለት ተናግሮአል፡- «በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት

ነው። ዮሐ. 17፡17። ስለማታስተውሉት ነገር ጥያቄ ከማብዛት ይልቅ፣ የበራላችሁን እውነት በደንብ አጢኑት፤ ያን ጊዜ የበለጠ ብርሃን ትቀበላላችሁ። በክርስቶስ ጸጋ በግልጽ ለተረዳችሁት እውነት ታዘዙ፤ ይህንን ስታደርጉ አሁን የምትጠራጠሩባቸውን ነገሮች የበለጠ ለማስተዋልና ለመታዘዝ ኃይል ታገኛላችሁ።

በጣም ለተማረውም ሆነ ምንም ላልተማረው በእኩል የተሰጠ ማስረጃ አለ። ይሄውም የግል ተሞክሮ መረጃ ነው። እግዚአብሔር የቃሉን እውነታነት የተስፋውንም እርግጠኝነት ለራሳችን ሞክረን እንድናየው ያድመናል። እንዲህ ይለናል፦ «እግዚአብሔር ቸር እንደ ሆነ ቅመሱ እዩም፤» መዝ. 34፡8። በሌላ ሰው ቃል ላይ ከምንደገፍ ለራሳችን ቀምሰን

ማየት አለብን። «ጠይቁ ይሰጣችኋል» ዮሐ. 16፡24 በማለት ያውጃል። የተስፋው ቃሎች ይፈጸማሉ። ሳይፈጸሙ የቀሩበት ጊዜ የለም፤ ለወደፊትም አይኖርም። ወደ ኢየሱስ ስንቀርብና በፍቅሩ ሙላት ስንደሰት ጥርጣሬያችንና ጨለማችን ሁሉ በመገኘቱ ብርሃን ይገፈፋሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- «እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ … ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን። …» ቆላ. 1፡ 13። ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገረ ሁሉ ደግሞ «እግዚአብሔር እውነተኛ እንደ ሆነ አተመ…» ዮሐ. 3፡33። እንዲህም ብሎ መመስከር ይችላል፡- «እርዳታ ፈልጌ ሳለ ኢየሱስን አገኘሁት። ፍላጎቶቼን ሁሉ አማDላልኝ። የነፍሴ ረሐብ በጥጋብ ተተካ።

አሁን ለእኔ መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ መገለጥ ነው። ለምን በክርስቶስ ታምናለህ; ብትሉኝ እርሱ ለእኔ መለኮታዊ አዳኜ ስለሆነ ነው። ለምን በመጽሐፍ ቅዱስን ታምናለህ; ብትሉኝ ለነፍሴ የእግዚአብሔር ድምጽ ሆኖ ስላገኘሁበት ነው።» መጽሐፍ ቅዱስ እውነት እንደሆነና ክርስቶስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለራሳችን ምስክርነቱን ልናገኝ እንችላለን። በጥበብ የተቀነባበረ ውሸት እንደማናምን እናውቃለን። ጴጥሮስ ወንድሞቹን እንዲህ ይላቸዋል፦ «ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ።» 2 ጴጥ. 3፡ 18። የእግዚአብሔር ህዝቦች በጸጋ እያደጉ ሲሄዱ ስለ ቃሉ ተጨማሪ መረዳቶችን ማግኘታቸው በIJሚነት የሚቀጥል ጉዳይ ይሆናል። አዲስ ብርሃንን እየተቀበሉ ይሄዳሉ፤ የተቀደሱትን እውነቶች ውበትም የበለጠ

ያጤናሉ። ይህ በዘመናት መካከል በቤተክርስቲያን ታሪክ የታየ እውነት ሲሆን በዚህ ሁኔታም ይቀጥላል። «የጻድቃን መንገድ ግን እንደ ንጋት ብርሃን ነው፥ ሙሉ ቀን እስኪሆንም ድረስ እየተጨመረ ይበራል።» ምሳ. 4፡ 18።

እግዚአብሔር የቃሉን እውነታነት የተስፋውንም እርግጠኝነት ለራሳችን ሞክረን እንድናየው ያድመናል።

ወደፊት የምንወርሳትን ምድር በእምነት አሻግርን በማየት ከእውነት ምንጭ ጋር በመቆራኘት ልናገኝ የምችለውን የማስተዋል እድገት ከእግዚአብሔር እንጠይቅ። ዛሬ ግራ ያጋባን ነገር ሁሉ ያን ጊዜ በእግዚአብሔር እርዳታ ግልጽ ይሆንልናል። አሁን ለመረዳት ላስቸገሩን ነገሮች ያን ጊዜ መግለጫ

እናገኝላቸዋል። «ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።» 1 ቆሮ. 13፡12።

## ምዕራፍ 13 - በጌታ መደሰት

በእግዚአብሔር ልጆች የተጠሩት የክርስቶስ ወኪሎች በመሆን የጌታን በጎነት እና ቸርነት እንዲያሳዩ ነው:: ክርስቶስ እውነተኛውን የአብን ባሕርይ ለእኛ እንደገለፀልን እኛ ደግሞ ርህራሄውንና አዛኝ ፍቅሩን ለማያውቀው ዓለም ክርስቶስን ልንገልጽ ይገባናል። ኢየሱስ እንዲህ ብሎአል፦ «ወደ ዓለም እንደላክሽኝ እኔ ደግሞ እነርሱን ወደ ዓለም ልኬያቸዋለሁ» እንደዚሁም «እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን . . . በዚህም ዓለም አንተ እንደላክሽኝ ያውቃል።» (ዮሐ. 17፡18፣23)። ሐዋርያው ጳውሎስ ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት «ሰዎች ሁሉ የሚያውቁትና የሚያነቡት በልባችን የተጻፈ መልዕክታችን ናችሁ» «የክርስቶስ መልእክት እንደ ሆናችሁ የተገለጠ ነው» (2ኛ ቆሮ. 3:2-3) ይላል።

ኢየሱስ በእያንዳንዱ ልጁ በኩል ወደ ዓለም ደብዳቤ ልኳል። እናንተ የክርስቶስ ተከታዮች ከሆናችሁ በእናንተ ወደየቤተሰቦቻችሁ፣ መንደሮቻችሁ፣ ጎዳናዎች እና የምትኖሩበት ቦታ ሁሉ ደብዳቤ ልኳል ማለት ነው:: በእናንተ የሚኖረው ኢየሱስ፣ ከእርሱ ጋር ላልተዋወቁ ሰዎች ልብ በአኗኗራችሁ በኩል መናገር ይፈልጋል።ምናልባትም እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን አላነበቡም ይሆናል ወይም አንብበውትም እንኳን በየገፁ ለልባቸው የሚጮኸውን ድምፅ አልሰሙም ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ፍቅር ሲሰራም አላስተዋሉትም ይሆናል። እናንተ ግን የኢየሱስ እውነተኛ ወኪል ከሆናችሁ፣ እነዚህ ሰዎች የእርሱን በጎነት በእናንተ በኩል በመረዳት ለፍቅሩና ለአገልግሎቱ እጃቸውን ይሰጣሉ።

ክርስቲያኖች ለመንግስተ ሰማይ መንገድ ብርሃን አብሪዎች ናቸው። ከክርስቶስ የሚመነጨውና በእነርሱ ላይ የሚያበራው ብርሃን አንፀባራቂዎች ናቸው:: ሕይወታቸውና ባሕርያቸው ለሌሎች ስለክርስቶስና አገልግሎቱ ትክክለኛውን አመለካከት የሚያስጨብጡ ሊሆኑ ይገባል።

እኛ ክርስቶስን የምንወክል ከሆንን፣ አገልግሎቱን ማራኪ አድርገን ልናቀርበው ይገባል፤ በእርግጥም ማራኪ ነውና። ክርስቲያኖች ወደ ነፍሳቸው ጭጋግና ሀዘን፣ ማጉረምረም እና ምሬት የሚሰበስቡ ከሆነ ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር እና ስለ ክርስትና ሕይወት የተሳሳተ ስዕልን ያሳያሉ። ልጆቹ ደስተኞች በመሆናቸው እግዚአብሔር ደስ የማይሰኝ እንደሆነ በማስመሰል ለሰማያዊ አባታችንም አሉታዊ ምስክር ይሆናሉ።

ሰይጣን የእግዚአብሔር ልጆችን ከእምነታቸው ፈቀቅ ሲያደርጋቸውና በሐዘን ፊታቸውን ሲያጠቁረው ይከብራል። እንደዚሁም እግዚአብሔርን ስንክድ፣ የማዳን ኃይሉን እና ፈቃዱን ስንጠራጠረው ሰይጣን ይፈነድቃል።

ሰይጣን ጌታ በሚሰጠን ነገሮች እንደተጎዳን ስናስብ ደስ ይለዋል። ጌታን፣ፍቅር እና ርህራሄ እንደሌለው አድርጎ ማቅረብም የሰይጣን ሥራ ነው።ሰይጣን ስለ እግዚአብሔር የተጻፈውን እውነት ያጣምማል፣ አእምሮአችንንም በተሳሳተ ሃሳብ መሙላት ይፈልጋል። ስለ ሰማያዊው አባታችን እውነት የሆነውን ከማሰብ ይልቅ እኛም ብዙውን ጊዜ በሰይጣን ውሸት አእምሮአችንን እንሞላና እርሱን ባለማመን እና በእርሱም ላይ በማጉረምረም እግዚአብሔርን

እናዋርደዋለን። ሰይጣን ሁል ጊዜ የሚፈልገው ነገር የክርስትና ሕይወት የሃዘን ጥላ ያጠላበት እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ ነው። አድካሚና አሰልቺ እንዲመስልም ይጥራል።ክርስቲያንም በሕይወቱ እንዲህ ዓይነቱን የኃይማኖት ገጽታ የሚያሳይ ከሆነ እምነት በጎደለው ድርጊቱ ለሰይጣን ውሸት የድጋፍ እጁን ያወጣል።

በክርስትና ሕይወታቸው ብዙዎች ትኩረታቸውን በስህተታቸው፣ በውድቀታቸው፣ በሀዘናቸው፣ በልባቸው ውስጥ በሞላ ሀዘንና ተስፋ መቁረጥ ላይ ያኖራሉ። አንድ ጊዜ አውሮጳ ውስጥ እያለሁ በእንደዚህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ ትኖር የነበረችና ጥልቅ በሆነ ድብርት የተዋጠች እህት ጥቂት የማፅናኛ ቃል እንድልክላት ደብዳቤ ፃፈችልኝ።ያን ደብዳቤ ባነበብኩበት

ሌሊት በሕልሜ በአንድ የአትክልት ሥፍራ፣ የአትክልት ስፍራው ባለቤት ከሚመስል ሰው ጋር እመላለስ ነበር። አበቦችን እየሰበሰብኩ እና በመልካም መዓዛቸው እየተደሰትኩ ባለሁበት በዚያ ሌሊት ትኩረቴ ከጎኔ ስፍራው ባለቤት ከሚመስል ሰው ጋር እመላለስ ነበር። አበቦችን እየሰበሰብኩ እና በመልካም መዓዛቸው እየተደሰትኩ ባለሁበት በዚያ ሌሊት ትኩረቴ ከጎኔ ትጓዝ የነበረችውን ይህቺን እህት ወዳሰናከላት አንድ የማይታይ እንቅፋት ላይ አረፈ። በእዚያ ቦታ ላይ እርሷ ታዝንና ትተክዝም ነበር። በትክክለኛው መንገድ ይመራት የበረውን መሪ መከተሏን ትታ በእሾህ እና አሜኬላ መካከል ትጓዝ ነበር። እያለችም ታዝን ነበር። «ወይኔ ይህ የሚያምር የአትክልት ስፍራ በእሾሆች ሲበከል አያሳዝንም? » መንገድ ይመራ የነበረውም፡- «እሾሆቹ ስለሚያቆስሉሽ

እነርሱን ተያቸውና ጽጌሬዳዎቹን እና ሌሎቹን አበቦች ብቻ ሰብስቢ» አላት።

እንዲህ «እሸሆቹ ስስሚያቆስሉስ እነርሱን ተያቸውና ጽጌሬዳዎቹን አና ሌሎቹን አበቦች ብቻ ሰብስቢ»።

በሕይወታችሁ እጅግ የተደሰታችሁበት ጊዜ የለም? የብርሃን ፍንጣቂ የነበረበት ጊዜ የለምን? ለእግዚአብሔር መንፈስ መልስ በመስጠት ልባችሁ በደስታ የተፍለቀለቀበት ጊዜ አልነበረም? የሕይወታችሁን ምዕራፎች ዘወር ብላችሁ ባያችሁ ጊዜ ጥቂት አስደሳች ጊዜያት የሉምን? የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች በመንገዳችሁ ላይ በሁሉም አቅጣጫ እንደ አበባ መዓዛ አይደሉም? ውበታቸው እና ጣፋጭነታቸው ልባችሁን በደስታ እንዲሞላው አትፈቅዱላቸውምን?

እሾህ እና አሜኬላዎች ያቆስሏችሁና ያሳዝኗችሁ ይሆናል። እነዚህን ብቻ እየለቀማችሁ ለሌሎች የምትሰጧቸው ከሆነ የእግዚአብሔርን መልካምነት ዝቅ ከማድረጋችሁ ያለፈ በዙሪያችሁ ያሉትን ሰዎች በእውነተኛው የሕይወት ጎዳና እንዳይሄዱ መከልከላችሁ አይደለምን?

ያለፈ ሕይወታችንን ደስ የማያሰኙ የኃጢአትና የተስፋ መቁረጥ ትዝታ ዎች እያነሳን በሽንፈት እስክንዘረር ድረስ ስለ እነርሱ ደጋግሞ ማውራትና ማለቃቀስ ብልህነት አይደለም። ተስፋ የቆረጠች ነፍስ በጨለማ የተሞላች፣ለእግዚአብሔር ብርሃን ራሷን የዘጋችና በሌሎች ሕይወት ላይ ጥላን ያጠላች ናት።

እግዚአብሔር ለእኛ ስለገለፀው ብሩህ ምስል የተመሰገነ ይሁን።የእግዚአብሔር ፍቅር ማረጋገጫ የሆኑትን በረከቶች ካለማቋረጥ እናስታውሳቸው። እኛን ከሰይጣን ኃይል ለመታደግ ሲል የእግዚአብሔር ልጅ የአባቱን ዙፋን ለቅቆ መለኮታዊ ማንነቱን በሰብአዊነት ሸፈነ። በእኛ ምትክ ድልን በመቀዳጀት ሰማይን ከፈተልን፤ ክብሩንም አሳየን። ሰብአዊ ዘር ሁሉ ተወርውሮ ከነበረበት ከኃጢያት አዘቅት በማውጣት እንደገና ወደ ዘለዓለማዊ አምላክ ህብረት መለሰን። በአዳኛችን ላይ በመታመን ፈተናን በማሸነፍ፣ የክርስቶስን ጽድቅ በመልበስ ወደ ዙፋኑ ከፍ አደረገን።

እግዚአብሔር እንድናሰላስል የሚፈልገው እንደዚህ ያሉትን የተዋቡ ስዕሎች ነው። የእግዚአብሔርን ፍቅር ስንጠራጠርና ቃል

ኪዳኑን ሳናምን ስንቀር እርሱን እናዋርደዋለን፤ ቅዱስ መንፈሱን እናሳዝናለን። ሕይወቷን በሙሉ የልጆችዋን ፍላጎት ለማሟላትና ለእነርሱ ምቾት ለሰዋች አንዲት እናት፣ ልጆቿ ያደረገችውን ነገር ሁሉ ከምንም ሳይቆጥሩ ያለማቋረጥ ቢያማርራት ምን ይሰማታል? ፍቅሯን ተጠራጠሩት እንበል፣ ይህ ታዲያ መንፈሷን አይሰብረውምን? ልጆቹ ለአባታቸው ያለው ምላሽ እንደዚህ ከሆነ የአባታቸው ስሜት ምን አይነት ይሆን? ታዲያ ሰማያዊ አባታችን እኛ ሕይወት እንዲኖረን አንድያ ልጁን እስኪሰጠን ድረስ ያስገደደውን ፍቅሩን ስናጣጥል ምን ይሰማው ይሆን? (ሐዋርያው በሮሜ 8፡32 ላይ «ለገዛ የሰጠው፣ ከክርስቶስ ጋር ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለሁላችን ደግሞ ሁሉንም ነገር ደግሞ ሁሉንም ነገር እንዴት አይሰጠንም!» ሲል ፍቅሩን ስናጣጥል

ምን ይሰማው ይሆን?( ሐዋርያው በሮሜ 8፡32 ላይ «ለገዛ የሰጠው፣ ከክርስቶስ ጋር ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለሁላችን ደግሞ ሁሉንም ነገር ደግሞ ሁሉንም ነገር እንዴት አይሰጠንም!» ሲል ጽፏል። ይህ የተስፋ ቃል ቢሰጣቸውም ስንቶች ናቸው በድርጊታቸው አልፎም በቃላቸው «ለእኔ ጌታ እንዲህ አይደለም። ምናልባት ሌሎችን ይወድ ይሆናል። እኔን ግን አይወደኝም።» የሚሉ።

«ለገዛልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለሁላችን አሳልፎ አሳልፎ የሰጠው፣ ከክርስቶስ ጋር እንዴት አይሰጠንም?»

እንደዚህ አይነት ሃሳቦች ካሉን ራሳችንን ነው የምንጎዳው። ከአፋችን የሚወጣው እያንዳንዱ የጥርጣሬ ቃል ለሰይጣን ፈተና ይዳርገናል። ይህ ነገር የበለጠ ተጠራጣሪዎች

እንድንሆን ያደርገናል፣ አገልጋይ መላእክትንም ከእኛ በኃዘን እንዲለዩ ያደርጋል:: ሰይጣን በሚፈትናችሁ ጊዜ የጥርጣሬ ወይም የጭለማን ነገር ትንፍሽ አትበሉ:: የልባችሁ በር ለሰይጣን ምክር የተከፈተ ከሆነ አዕምሯችሁ በጥርጣሬና በአመፅ ጥያቄዎች ይሞላል። ስሜታችሁንና ጥርጣሬያችሁን አውጥታችሁ የምትናገሩ ከሆነ የተናገራችሁት ቃል በራሳችሁ ላይ ከመፍረዱም በላይ አቆጥቁጦ በሌሎች ሕይወት ላይ ፍሬ የሚያፈራና እንዲሁም ቃላችሁ የሚያመጣው ተፅእኖ ሊቀለበስ የማይችል ይሆናል። እናንተ ከሰይጣን ፈተና ትተርፉ ከወጥመዱም ታመልጡ ይሆናል፤ ሌሎች በእናንተ ቃል ተፅእኖ ምክንያት የዋዠቁ ሰዎች ግን እናንተ ከመራችኋቸው የዓለማመን አካሄድ ማምለጥ አይችሉም። መንፈሳዊ ጥንካሬና ሕይወት የሚሰጡ

ነገሮችን ብቻ መናገር ምንኛ ወሳኝ ነገር ነው!

ስለ ሰማያዊ አባታችን ለዓለም የምታቀርቡትን ዘገባ ለማድመጥ መላዕክት በዙሪያችሁ ይከብቧችኋል:: የምትናገሩት ንግግር በአብ ፊት ስለ እናንተ የሚማልደውን የሚያከብር መሆን አለበት:: የጓደኞችሁን እጅ ለሰላምታ በምትጨብጡበት ጊዜ በአፋችሁ እና በልባችሁ ለእግዚአብሔር ክብር ስጡ።ይህ የጓደኞችሁን ልብ ለኢየሱስ ይማርካል።

ሁሉም ሰው ይፈተናል። እያንዳንዱ ሰው ሊሸከመው ከባድ የሆነበት ሀዘን፣ ሊቋቋመው በብርቱ የበዛበት ፈተና አለበት:: የሚያስጨንቋችሁን ነገሮች እንደ እናንተ ጠፊ ለሆኑት ሰዎች አትንገሩ። ይልቁንም

በፀሎት ሁሉንም ነገር ወደ እግዚአብሔር አምጡት። ከአፋችሁ የጥርጣሬ እና የተስፋ መቁረጥ ቃል እንዳይወጣ የራሳችሁ ሕግ አድርጉት:: ይህን በማድረጋችሁና በተስፋ ቃል እንዲሁም በተቀደሰ ፈገግታ የሌሎችን ሕይወት ብሩህ ልታደርጉ እንዲሁም በሕይወት ተግዳሮት ላይ ላለባቸው ትግል ጥንካሬ ልትሆኗቸው ትችላላችሁ።

የብዙ ሰዎች ነፍስ ከራሳቸው ጋር በሚያደርጉት ግጭት እና ከኃጢአት ኃይል የተነሳ ፈፅሞ ለመውደቅ እየተፍገመገመች በአደገኛ ሁኔታ በፈተና ውስጥ አለች:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው በሚያደርገው ግብግብ ተስፋ አታስቆርጡት:: በማበረታቻና እርሱን በመንገዱ ሊያነቃቁት በሚችሉ በተስፋ ቃላት አስደስቱት:: በዚህም የክርስቶስ ብርሃን በእናንተ ያብረቀርቃል፤«ለራሳችን

አንኖርም እና» (ሮሜ 14፡7)።
ሳታስተውሉት በምታደርጉት ነገር ሌሎች ሊበረታቱ እና ሊጠነከሩ ወይም ደግሞ በአንጻሩ ተስፋ ሊቆርጡ እንዲሁም ከክርስቶስ እና ከእውነት ሊርቁ ይችላሉ።

ስለክርስቶስ ባህርይ እና ሕይወት ብዙዎች የተሳሳተ አስተሳሰብ አላቸው።እነዚህ ሰዎች፣ ክርስቶስ የደስታ ጸዳል የሌለው፣ ወና፣ ባዶ፣ ጎስቋላና ደስታ የራቀው እንደሆነ አድርገው ያስቡታል። በብዙ ሁኔታ፤ ሁሉም ሃይማኖቶች ማለት ይቻላል፤ የክርስቶስን የምድር ሕይወት በዚህ ዓይነት ጭጋጋማ ዕይታ ያዩታል።

ብዙ ጊዜ ኢየሱስ እንዳነባ ሲጠቀስ እንደሳቀ ፈፅሞ አይታወቅም:: እርግጥ ነው፣ አዳኛችን ልቡ በህዘን ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ

የተከፈተ በመሆኑ እና ሐዘናቸውን ይካፈል ስለነበር የሕማም ሰው ነበር። ምንም እንኳ ሕይወቱ እራስን በመካድ፣ በህመም እና ጥንቃቄ የተሞላ ቢሆንም መንፈሰ ሰባራ ግን አልነበረም።ገፅታው የሀዘንና የጉስቁልና አልነበረም። ነገር ግን የሰላም ድባብ ሽፍኖት ነበር።እርሱ መልካም የሕይወት ምንጭ ነበር። በሄደበት ሁሉ ሰላም፣ ዕረፍት፣ደስታና እርካታ ይዞ ይሄድ ነበር።

ሳታስታውሱ በምታደርጉት ነገር ሌሎች ሲበረታቱና ሲጠነክሩ ወይም ደግሞ በአንጻሩ ተስፋ ሲቆርጡ አንዲሁም ከጌታ እና ከእውነት ሲርቁ ይችላሉ።

አዳኛችን በእርግጥ ከልቡ በአቋሙ የጸና እና ታማኝ የነበረ እንጂ ጨፍጋጋ እና እምነት የጎደለው አልነበረም። የእርሱን ሕይወት

የሚጋሩ ሰዎች ሁሉ፣ በሙሉ ልባቸው የሚታመኑለት ዓላማ እና ሃላፊነት ይኖራቸዋል፤ አስመሳይነትና ኩራት አይታይባቸውም፤ በበላይነት የመኮፈስ ንግግርና አጉል ቀልድ ከአንደበታቸው አይደመጥም። ከዚህ ይልቅ በኢየሱስ ያላቸው እምነት እንደወንዝ የሚፈስ ሰላምን ይሰጣቸዋል። ይህ እምነት የደስታቸውን ብርሃን አያጠፋም:: ደስተኛነትንና የሚያሞቅ ፈገግተኛ ፊትን አያጨፈግግም። ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ሊገለገል ሳይሆን ሊያገለግል ነው:: የእርሱ ፍቅር በእኛ ልብ ውስጥ ሲነግስ የእርሱን ምሳሌ እንከተላለን።

የሌሎችን መልካም ያልሆኑና ትክክል ያልሆኑ ሥራዎች በአዕምሯችን ውስጥ ደብቀን የምንይዝ ከሆነ ክርስቶስ እኛን እንደወደደን

እነርሱን መውደድ ያቅተናል። ነገር ግን ክርስቶስ ለእኛ የሰጠው አስደናቂ እና የርህራሄ ፍቅር ገብቶን ከሆነ እኛም ለሌሎች ተመሳሳይ ፍቅር ይኖረናል። ምንም እንኳን የምንመለከታቸው ኃጢአትና በደሎች ቢኖሩም እነርሱን ከማሰብ ይልቅ እርስ በርሳችን መፈቃቀር እና መከባበር አለብን። ትህትናና ራስን ዝቅ ማድረግ፣ ለሌሎችም ከነበደላቸው ትዕግስት እና ርህራሄን ማሳየት ከእኛ ሊገኝ ይገባል። እንዲህ ዓይነቱ ልምምድ በእኛ ማንነት ውስጥ ጠባብነትንና እራስ ወዳድነትን ገድሎ ልበ-ሰፊነትንና ሩህሩህነትን ያነግሳል።

ዘማሪው «በእግዚአብሔር ታመን መልካምንም አድርግ» (መዝ. 37:3) ይላል። እያንዳንዱ ቀን የራሱ የሆነ ሸክም፣ ጣጣና ውጣውረዶች አሉት:: እኛም በተሰበሰብን

ጊዜ እነዚህን ችግሮችና ፈተናዎች ለማውራት ብዙ ጊዜ ይቃጣናል፡፡ ብዙ አላስፈላጊ መከራዎች ከበውናል ፤ ፍርሃት ሃሳባችንን አንቆታል ፤ እጅግ የከበደውን ጭንቀት ለመሸከም አልቻልንም። ይህንን ሁሉ በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚያይ ሰው የጸሎት ጥያቄዎችን ሊሰማ የተዘጋጀና በመከራ ጊዜም የቅርብ ረዳት የሆነ ሩህሩህና አፍቃሪ አዳኝ እንደሌለ ሊያስብ ይችላል።

አንዳንዶች በየዕለቱ በእግዚአብሔር የፍቅር ስጦታዎች እየተጎበኙ፣ በየዕለቱ በቸርነቱ ሙላቶች እየተደሰቱ እነዚህን ስጦታዎች ሁሉ ቸል በማለት ሁልጊዜም በፍርሀትና በአስጨናቂ ሁከት ውስጥ ናቸው፡፡ የእነዚህ ሰዎች አዕምሮ «ይመጣል» ብለው በሚፈሩት ነገር የተጠመደ ስለሆነ

ያለማቋረጥ ከሚያገኙት መልካም ነገር ጋር ሳይስማሙ ይኖራሉ። ወይም ሊያደንቋቸውና ሊያመሰግኑ ለሚገባቸው ትልልቅ ነገሮች ዓይናቸውን በመጨፈናቸው፣ ጥቃቅን በሆኑ ችግሮች ሁልጊዜ እንደተወጠሩ ይታያሉ። ከእነዚህ ከሚያጋጥሟቸው ጥቃቅን ችግሮች የተነሳ የረድኤታቸው ብቸኛ ምንጭ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ከመቅረብ ይልቅ ያለ ዕረፍት በመሆንና እርካታ በማጣት ውስጥ ተጠምደዋል።

ስለዚህ ዓለማመናችን ትክክል ነው? ለምን ምስጋና ቢስ እና እምነተ ቢስ እንሆናለን? ኢየሱስ ጓደኛችን ነው፤ መላው ሰማይ ደግሞ የእኛ ደህንነት የጠበቀ እንዲሆን ጽኑ ፍላጎት አለው። ስለዚህ የእለት ተእለት ሕይወት ጭንቀትና ችግር አዕምሮአችንን

እንዲያሸብረውና ግንባራችንንም እንዲያጨማድደው ልንፈቅድለት አይገባም። ለእነዚህ እራሳችንን ያስገዛን ከሆነ ሁልጊዜም የሚያበሳጨን እና የሚያናድደን ነገር አናጣም:: ፈተናዎችን ለመቋቋም የማይረዱን ሆኖ ሳለ ለእነዚህ እንደ እርካታ ማጣት እና ጭንቀት ላሉ ነገሮች እራሳችንን በመስጠት የራሳችንን ሕይወት ማጎሳቆል የለብንም።

ምናልባት በስራ ቦታችሁ ችግር ገጥሟችሁ ይሆናል ወይም የወደፊት ተስፋችሁ እየጨላለመባችሁ ሊሆን ይችላል ፤ የውድቀት ስጋት አድሮባችሁ ሊሆንም ይችላል። ይሁን እንጂ ተስፋ አትቁረጡ። የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ጣሉና ጉዳያችሁን እንዴት እንደምትፈቱና ጥበብም እንድታገኙ

በመፀለይ ውድቀት እና አደጋን ተከላከሉ። መልካም ውጤት ለማምጣት ልታደርጉ የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ። ኢየሱስ ሊያግዛችሁ ቃል ቢገባም የራሳችሁ ጥረትም ሊታከልበት ይገባል። በሰማዩ አባታችሁ በመታመን የምትችሉትን ሁሉ ካደረጋችሁ በኋላ ከዚያ በኋላ የሚመጣውን ውጤት ሁሉ በደስታ ተቀበሉት።

እግዚአብሔር ልጆቹ በችግር ብዛት እንዲጎሳቆሉ አይፈቅድም። ጌታችን ፈፅሞ አላታለለንም። እርሱ ለእኛ «መንገዳችሁ ምንም አደጋ ስለሌለበት አትፍሩ» አላለንም:: እርሱ ፈተናና ችግሮች እንዳሉ ያውቃልና በግልፅ ተናግሯል። እርሱ እኛን ኃጢአትና ጥፋት ካለበት ዓለም ለማውጣት ሳይሆን ዓላማው፤ ወደዘለዓለማዊና ብርቱ መጠጊያችን ወደሆነው ለመምራት ነው::

ስለደቀመዛሙርቱ የፀለየው የእርሱ ፀሎት ከዓለም እንድታወጣቸው አልልም፤ በዓለም ውስጥ ከዓለም ክፋት እንድትጠብቃቸው እንጂ» (ዮሐ. 17:15) ብሎ ነበር። «መከራ አለባችሁ:: ነገር ግን ዓለምን አሸንፌአለሁና በመከራ ደስ ይበላችሁ» ዮሐ 16:33)። በተራራው ስብከቱ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ በእግዚአብሔር ስለመታመን አስደናቂ ትምህርቶችን አስተምሯል። እነዚህ ትምህርቶች ማፅናኛ እንዲሆኑ በሁሉም ዕድሜ ክልል ለሚገኙ ለእግዚአብሔር ልጆች የተሰጡ ሲሆኑ፣ በዘመናችንም ሕያው ሆነው ይሰራሉ። አዳኛችን ተከታዮቹን ወደ ሰማይ ወፎች በመጠቆም ውዳሴያቸውን በዝማሬ እንደሚያቀርቡ እና ስለነገ ሮች በ መጨነቅ እንደማይዋጡ ሲያሳያቸው «አይዘሩም አያጭዱም» ይሁን እንጂ ትልቁ አባት

የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል ብሏል። አዳኛችን «ከእነዚህ በብዙ አትበልጡምን?» (ማቴ. 6:26) በማለትም ጠይቋል። ይህ ታላቅ እግዚአብሔር እጁን ለፍጥረቱ ሁሉ በመዘርጋት ለሰውና ለእንስሳ ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣል። እርሱ ለሰማይ ወፎች እንኳን ሳይቀር ይጠነቀቃል። የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ይሰጣቸዋል።በርግጥ ምንቃራቸውን በመያዝና አፋቸውን በማስከፈት ምግባቸውን አፋቸው ውስጥ አይጥልላቸውም:: የበተነላቸውን ጥራጥሬ ራሳቸው መለቃቀም አለባቸው:: ለትንሿ ጎጆአቸው ግንባታ የሚሆናቸውን ዕቃም ማዘጋጀት አለባቸው። ጫጩቶቻቸውን መመገብም ይጠበቅባቸዋል። ለስራ ሲሰማሩ የሰማይ አባታችሁ ስለሚመግባቸው» ይዘምራሉ። እናም «እናንተ ከእነርሱ በብዙ

አትበልጡም?» እናንተ ግን አስተዋዮችና መንፈሳዊ አምላኪ ዎች ስትሆኑ ከሰማይ ወፎች የበለጠ ዋጋ የላችሁም? እኛ በእርሱ ከታመንን፤ የማንነታችን ፈጣሪ፣ የሕይወታችን ጠባቂ እና በመለኮታዊ አምሳሉ የፈጠረን አምላክ የሚያስፈልገንን እንዴት አብልጦ አይሰጠንም?

የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእግዚአብሄር ላይ ጣሉና ጉዳያችሁን እንዴት እንደምትፈቱ ጥበብን ለማኘት ጸልዩ።

ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የሰማይ አባት ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር ለማሳየት ለአበቦች በቀላሉ እንዲያምሩ የሰጣቸውን ውበት እና ብልፅግና በማመላከት ወደ አበባዎች ጠቊሟቸዋል። እርሱ «የሜዳ አበቦችን እንዴት እንደሚያድጉ ተመልከቱ»

ብሏል:: የእነዚህ አበቦች የተፈጥሮ ጸጋና አንጸባራቂ የሆነ ውበት ሰለሞን በዛ ሁሉ ሀብቱ እንኳን እንደእነርሱ ሊለብስ እና ሊዋብ አልቻለም:: እጅግ በጣም ውብ የሆነ በእጅ ጥበብ ክህሎት የተሰራ ሥዕል የእግዚአብሔር ፍጥረት የሆኑ አበቦችን ውበት ሊያገኝ አይችልም።ኢየሱስ «እናንተ እምነት የጎደላችሁ እግዚአብሔር ዛሬ ታይቶ ነገ በእሳት የሚጠፋን ሳር እንዲህ ካለበሰ እናንተን የበለጠ እንዴት አያለብሳችሁም?» (ማቴ. 6:28 ና 30)። መለኮታዊ ጥበብ የተሞላው እግዚአብሔር ታይተው ለሚጠፉ አበቦች እንዲህ የሚያሳሳ እና የተለያዩ ቀለማት ሰጥቶ እንዲያምሩ ካደረጋቸው በእርሱ አምሳል ለተፈጠሩ እንዴት የበለጠ ክብካቤ አያደርግላቸውም? እንዲህ ዓይነቱን የክርስቶስ ትምህርት የማያምን ልብ

ያላቸውን፣ በተዘበራረቀ ሃሳብ እና በጥርጣሬ የተሞሉትን ክርስቶስ ይገስጻቸዋል።

ጌታ ሴቶችና ወንዶች ልጆቹን ደስተኛ፣ ሰላም የሞላቸው እና ታዛዥ እንዲሆኑለት ይፈልጋል። ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አለ፦ «ሰላምን እተውላችኋለሁ፣ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም።» «ደስታዬ በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈፀም ይህን ነግሬአችኋለሁ» ዮሐ 14:27 ና 15:11)።

ከራስ ወዳድነት ስሜትና ኃላፊነት የጎደለው ጎዳና የሚገኝ ደስታ ሚዛናዊነት የጎደለው፣ አጥፊ እና አላፊ ነው። ይህ ደስታ ባለፈ ጊዜ ነፍስ በብቸኝነትና በሀዘን ትሞላለች:: እግዚአብሔርን በማገልገል ግን ደስታና እርካታ አለ። ክርስቲያኖች ባልተረጋገጠ

መንገድ እንዲጓዙ አልተተውም፤ ለፀፀትና ለተስፋ መቁረጥ አልተተውም። አሁን ባለው ሕይወት ደስተኞች ባንሆን እንኳን ከዚህ ባሻገር በሚኖረው ሕይወት ደስታ እናገኛለን።

በዚህ ዓለምም ቢሆን ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር ባላቸው ህብረት ደስታ አላቸው:: የፍቅሩ ብርሃን በውስጣቸው ደስታን ይሰጣቸዋል። የእርሱ አብሮነት የማይቋረጥ መፅናናት ይሰጣቸዋል። ወደ ኢየሱስ የሚያቀርበን እያንዳንዱ የሕይወት እርምጃ የእርሱን ፍቅር በጥልቅ እንድንለማመድ እና ወደተባረከው የሰላም ቤት አንድ ደረጃ እንድንቀርብ ያደርገናል። ስለዚህ መተማመናችንን አንጣ ይልቁንም አብልጠን ዋስትናችንን ከበፊት ይልቅ እናፅና። «እስከአሁን ድረስ ጌታ እረድቶናል» እርሱ እስከፍፃሜም ይረዳናል (1ኛ ሣሙ.

7:12)። ከአጥፊው እጅ ሊያድነንና ሊያፅናናን ጌታ ለእኛ ያደረገልንን አስደናቂ ነገሮች ጌታ የሚያሳስቡንን ታላላቅ የመታሰቢያ ሃውልቶቻችንንና ማስታወሻዎቻችንን ድረስ እንይ። እግዚአብሔር ለእኛ ያሳየውን ርህራሄ፣ ያፈሰሰልንን እንባ፣የፈወሰንን ቁስል፣ የወሰደልንን ህዘን፣ ያስወገደልንን ፍርሃት፣ የሞላልንን ፍላጎት፣ ያበዛልንን በረከት፣ ሁልጊዜ በየዕለቱ እናስብ። ይህንን ማሰብ በሚቀረን መንፈሳዊ ጉዙአችን ሁሉ ለጥንካሬያችን ይረዳናል።

እስከ አሁን ድረስ እረድቶናል አስከፍጻሜም እርሱ ይረዳናል።

ከፊት ለፊታችን ባለን የሕይወት ዘመን ውስጥ የሚገጥመንን ውጣ ውረድ ከማሰብ

ይልቅ ያለፈውንና መጪውንም እያሰብን «እስከአሁን ድረስ ጌታ እረድቶናል» «እንደ እድሜህ እንዲሁ ጥንካሬህ ይሆናል» በማለት እናውጅ (ዘዳ. 33:25)። የሚገጥሙን ፈተናዎች እነርሱን ልንቋቋምበት ከሚሰጠን ጥንካሬ አይበልጡም:: ምንም ቢመጣ ከዚያ ተግዳሮት የበለጠ ጥንካሬ እንደሚሰጠን በማመን የተሰጠንን ስራ ባገኘንበት ሁሉ ለመስራት እንትጋ። የእግዚአብሔር ልጆች «እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ሳይፈጠር በፊት የተዘጋጀላችሁን የእግዚአብሔር መንግስት ውሰዱ» (ማቴ. 25:34 የሚሉ በጆሮአቸው የሚያስተጋቡ ፣ ሙዚቃዊ ቃና ያላቸው ፣ ከንጉሱ አፍ የሚፈሱ ክቡር የባርኮት ቃላትን እያደመጡ ሳለ የገነት ደጆች እነርሱን ለመቀበል ወለል ብለው ይከፈታሉ ።

በዚያን ጊዜ የተዋጁት ይገቡበት ዘንድ አስቀድሞ ለእነርሱ በኢየሱስ ወደተዘጋጀላቸው ስፍራ «እንኳን ደህና መጣችሁ!» ይባላል። በዚያ ስፍራ አብረዋቸው የሚሆኑት የምድር ከንቱነት የተጠናወታቸው፣ ውሸታሞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ እራሳቸውን ያላነፁና ያላመኑ ሳይሆኑ፤ አብረዋቸው የሚሆኑት ሰይጣንን አሸንፈው በመለኮታዊ ፀጋ ፍፁም የሆነውን ባህሪ ያገኙ ናቸው:: በዚህ ምድር ሲያጎሳቁላቸው የነበረው የኃጢአት ዝንባሌ ሁሉ ኃጢአትና ግሳንግሱ በክርስቶስ ደም ከእነርሱ ተወግዷልና የእርሱ ልሒቅነት እና ከፀሐይ ብርሃን የሚልቀው የክብሩ ብርሃን ይከብባቸዋል። የክርስቶስ ውበት፣ የባህሪው ፍፁምነት በእነርሱ ውስጥ ያበራል:: ይህ በእነርሱ ላይ በሚሆን ጊዜ በውጭ ከሚታይ ውበት በእጅጉ ይበልጣል። በታላቁ ነጭ ዙፋን

ፊት የመላዕክትን ክብርና በረከት በመጋራት ያለነቀፋ ይሆናሉ።

ከተዘጋጀልን ዘላለማዊና ባለ ታላቅ ግርማ ውርስ አንጻር ሲታይ «ሰው ስለነፍሱ ምን ዋጋ ሊከፍል ይችላል? ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?» (ማቴ. 16:26)። አንድ ሰው እጅግ ድሃ ቢሆንም ዓለም ፈፅሞ ሊያገኘው የማይችል ሃብትና ክብር ሊኖረው ይችላል:: ከኃጢአት ተዋጅቶ እና ነፅቶ በሙሉ ኃይሉ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሰጠ ሰው በእግዚአብሔር ዓይን ታላቅ ዋጋ አለው:: እንደዚሁም አንዲት ነፍስ በተዋጀች ጊዜ በላይ በሰማይ በእግዚአብሔር ማደሪያ እና በመላዕክት ዘንድ በቅዱስ የድል ዝማሬ የሚገለጽ ታላቅ ደስታ ይሆናል።